የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት
(በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች)

በ

የኔዓለም አረዶ

በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር
ኤምኤ.ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት
የቀረበ ጥናት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድኅረምረቃ መርኀግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት

ሐምሌ/2000ዓ.ም

የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት
(በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች)

በ

የኔዓለም አረዶ

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር
ኤምኤ.ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት
የቀረበ ጥናት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድኅረምረቃ መርኀግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት

ሐምሌ/2000 ዓ.ም

የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥናት

በ

የኔዓለም አረዶ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለትምህርት
የድኅረምረቃ መርሐግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ	ፊርማ
የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ
የውጭ ፈታኝ	ፊርማ

ምስጋና

በቅድሚያ በየጊዜው ጽሁፌን ደጋግመው በማረምና ማስተካከያ በመስጠት ጊዜና ሰዐት ሳይገድባቸው በትጋት በጊዜዬ እንድጠቀም የረዱኝን መምህሬን እና አማካሪዬን አቶ ዘሪሁን አስፋውን አመሰግናለሁ። የእሳቸው ትጋትና ቅንነት ባይታከልበት ይህ ስራ ለዚህ አይበቃም ነበር። ጊዜአቸውን ሰውተው በሁለቱም ወረዳዎች መረጃ አቀባዮችን በመምረጥ፣በዘዬ ልዩነት ከአቀባዮች ጋር ለመግባባት በተቸገርኩበት ወቅት በማስረዳትና መረጃውን እንዲሰጡኝ በማድረግ አብረውኝ ሲሰሩ ለነበሩት የምዕራብ አርሲ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የባህል ኤክስፐርት አቶ ቦንሰሞ ሚኤሶ ምስጋናዬ የላቀ ነው። ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼን በኮካሳ አቶ ከዲሮ ገነሞ፣አቶ ኢምሹ ኬቄ፣አቶ ገሼ ጢቃቆ፣ወ/ሮ ደሜ ቱፋ፣ወ/ሮ ፋጢማ ጃርሶ እና ወ/ሮ ፉሬ ቱራ እንዲሁም በሀሳሳ አቶ አብደላ ሉገማ፣ሼክ ከድር ሀያቶ፣አቶ ሀጂ አደም ሀጂ አምዳ እና ወ/ሮ አንዮ በቲሳ፣ ወ/ሮ አመሹ ሀጣቱ፣ወ/ሮ አያንቱ ዱቤን ከልብ አመሰግናቸዋለሁ።

የትምህርት ወጪዬን በመሸፈን እንድማር ያደረገኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለትምህርት መምህሮቼና የስራ ባልደረቦቼ በቁሳቁስም ሆነ በሞራል ላደረጋችሁልኝ ድጋፍ እግዚአብሄር መልካሙን ሁሉ ያድርግላችሁ እላለሁ። በተጨማሪም የክፍለትምህርቱ ሃላፊ አቶ ወንደሰን አዳነ የእውቀት አባትነት ምክርህና ቀናነትህ ለዚህች ቀን አብቅቶኛልና ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረስህ።

የመብራት አገልግሎት አስቸጋሪ በሆነበት አጋጣሚ ጊዜሽን ሰውተሽ ባልኩትና በፈለኩት ሰዐት ጽሁፌን በኮምፒውተር የጻፍሽልኝ ወ/ት ፊትለ ወርቅ፣ የኦሮምኛ ጽሁፉን በመጻፍ የረዳሽኝ ጓደኛዬ ኩሪ ባይሳ፣ፎቶዎችን ለማሳተም በተቸገርኩበት ጊዜ የረዳሽኝና አብረሽኝ የደከምሽው የክፍል ጓደኛዬ አዳነች አበራ፣ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ጥናቱ እስከዛሬ እስከሚደርስ ሁሌም አብረሽኝ የሆንሽው እህቴ ጽጌ አረዶ ሁላችሁንም አመሰግናችኋለሁ። በመስክ ቆይታም ሆነ በጥናቱ ወቅት በአካልም ሆነ በማበረታታት አብራችሁኝ የነበራችሁትን ሁሉ አመሰግናችኋለሁ።

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና i
ማውጫ ii
አጠቃሎ v
የምዕራብ አርሲ ዞን ካርታ
የገደብ ሀሳሳ ወረዳ ካርታ
በጥናቱ ውስጥ የቀረቡ የኦሮምኛ ጽሁፎችን ለማንበብ ያመች ዘንድ የአነባበባቸውን ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ

1.መግቢያ 1
1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 2
1.2 የጥናቱ ዓላማ 2
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ 3
1.4 የጥናቱ ወሰን 3
1.5 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሃሳቦች 3
1.5.1 ያገጠሙ ችግሮች 4
1.5.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች 4
1.6 የጥናቱ ዘዴ 5
1.7 የመረጃ አሰባሰብ 6
1.8 የመስክ ቆይታ 6
2. ክለሳ ድርሳን 9
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 9
2.2 የንድፈ ሀሳባዊ መነሻዎችና መሠረታዊ ፅንሰ ሃሳቦች ብያኔ 12
2.2.1 ቁሳዊ ባህል 13
2.2.1.1 ሃገረሰባዊ አልባሳት 15

2.2.1.2 ሃገረሰባዊ ጌጣጌጦች 17
2.2.2 አልባሳትና ሃገረሰባዊ ማንነት 19
3. የጥናት አካባቢው ማህበረ ባህላዊ ዳራ 20
3.1 የጥናት አካባቢዎቹ ስም አመጣጥ 20
3.2 ምጣኔ ሀብት 21
3.3 ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ሃብቶች 21
3.4 ቋንቋ 22
3.5 እምነት/ሃይማኖት 23
3.6 ማህበራዊ አገልግሎቶችና ባህላዊ መገለጫዎች 24
3.6.1 ማህበራዊ አገልግሎት 24
3.6.2 ባህላዊ ጉዳዮች 25
4. የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ 31
4.1 የኮኮሳ ሴቶች አልባሳት 31
4.1.1 የልጆች አልባሳት 31
4.1.2 የልጃገረዶች አልባሳት 33
4.1.3. ያገቡ ሴቶች አልባሳት 37
4.1.3.1 ልብሶቹና አገልግሎታቸው 44
4.1.3.2 የኮኮሳ ሴቶች አልባሳት የመለበሻ አጋጣሚዎች 45
4.2 የኮኮሳ ወረዳ ሴቶች ጌጣጌጦች 47
4.2.1 ያላገቡ ሴቶች የሚያደርጓቸው ጌጦች 48
4.2.2 ያገቡ የኮኮሳ ሴቶች የሚያደርጓቸው ጌጦች 50
4.3 የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ በገደብ ሀሳሳ 58
4.3.1 የሴቶች አልባሳትና ሰሪዎቻቸው በገደብ ሀሳሳ 58
4.3.1.1 በግል የሚሰሩ አልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎች 58
4.3.1.2 በማህበር የሚሰሩ የጌጣጌጥና የአልባሳት ሰሪዎች 59
4.3.2 ለገበያ የሚቀርቡ ቁሶችና መስሪያዎቻቸው 59
4.3.2.1 አልባሳት 59
4.3.2.2 ጌጣጌጦች 62

4.3.3 የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ይዞታና የህዝቡ አስተያየት 64
4.3.4 የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰራተኞች የለመዳ ሂደትና የጥበቡ እድገት 67
4.4 የሴቶቹ አልባሳትና ጌጣጌጦች ከማንነት ጋር ያላቸው ቁርኝት 69
4.5 የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ መቀነስ/መጥፋት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች 71
4.6 የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ባህላዊነትን ለመጠበቅ ምን መደረግ አለበት? 73
5. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች 76
5.1 ማጠቃለያ 76
5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች 78
ዋቢ ምንጮች
አባሪዎች
አባሪ 1 የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር
አባሪ 2 የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች
አባሪ 3 ፎቶዎች

አጠቃሎ

ይህ ጥናት የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ የተደረገ ነው። በጥናቱ በምዕራብ አርሲ ዞን ከሚገኙ 12 ወረዳዎች ውስጥ በአርሲ ሴቶች በተለያዩ የእድሜና የማህበራዊ ደረጃዎች የሚለበሱ ልብሶችና ጌጣጌጥ የቀድሞና የአሁን ይዞታን ለማጥናት ሲባል የኮኮሳ እና የገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል።መረጃዎች የተሰበሰቡት በቃለመጠይቅና በምልከታ ነው።

የጥናቱ አላማ በኮኮሳና በገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች የሚታዩትን አልባሳትና ጌጣጌጦች የቀድሞና የአሁን ይዞታ ከባህላዊ አገልግሎታቸው አንጻር መግለጽ ነው። ይህንን አቢይ አላማ ከግብ ለማድረስ ያስችል ዘንድ በእያንዳንዱ ወረዳ ያሉትን የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች በጠቀሜታቸው ለይቶ ማሳየት፣ አልባሳቱም ከማህበረሰቡ ህይወት ጋር ጥልቅ ትስስር ያላቸው መሆን አለመሆናቸውን መመርመር፣የአልባሳቱንና የጌጣጌጦችን ይዞታም ማሳየት ተተኩሮባቸዋል።

ከሁለቱ ወረዳዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች የሚያመለክቱት በኮኮሳ ያለው የአለባበስና የአጊያጌጥ ባህል የጥንቱ የአርሲ ማህበረሰብ ባህላዊ መገለጫ መሆኑን ነው። በሀሳሳ የኮኮሳ ሙስሊም ሴቶች ከሚያደርጉት የጸጉር መሸፈኛ (ጉፍታ) በስተቀር የቱም አይነት ባህላዊ ልብስ የለም። በዚሁ አካባቢ አልባሳቱም ሆኑ በጥቂቱ ጌጣጌጡ ባህላዊ ስማቸውንና የተወሰነ አገልግሎታቸውን ይዘው ተገኝተዋል። በሁለቱም ወረዳዎች የሚሰሩ ጌጣጌጦችም ሆኑ አልባሳት ከተለያዩ ቀለማት የሚሰሩ ይሁኑ እንጂ ቀለማቱ ለትዕምርታዊ ፋይዳ ሳይሆን ለውበት ሲባል አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሆነው ተገኝተዋል። በኮኮሳ በታሪክና በስም ያሉ ነገር ግን አገልግሎት ላይ የማይውሉ የልብስ አይነቶች አሉ። በባህላዊ መንገድ አልባሳቱ ከእናት ወደ ልጅ እንደሚተላለፉ ሁሉ በሀሳሳ የሚገኙ የአልባሳትና የጌጣጌጥ ሰሪዎች ለልጆቻቸው እያስተማሩ መሆኑ የጥበቡን የመወራረስ ባህል መኖር የሚያመለክት ነው። በሌላ በኩል ሰሪዎቹ በማየት፣ከቤተሰብ በመማር እንዲሁም የተሰሩትን በማየት የሚሰሩ መሆኑ የለመዳው ሂደት አንድ ብቻ እንዳልሆነ ያመለክታል።

በኮኮሳ የተወሰኑ ሴቶች ንብረት የሆኑት አልባሳትና ጌጣጌጥ ባህላዊ ይዘታቸውን ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፉ ተዘጋጅተው ሙዚየም እንዲገቡ ማድረግ በሚመለከታቸው አካላት ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በሀሳሳ ባህላዊው በዘመናዊ መንገድ እየሰሩ ያሉት ለጊዜያዊ ጠቀሜታ ብቻ ሳይሆን ባህል ከመጠበቅ አንጻርም መስራት እንዳለባቸው የሚያመለክት ትምህርትና ክትትል በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው።



የምዕራብ አርሲ ዞን ካርታ

* የኮኮሳ ወረዳ
* የገደብ ሀሳሳ ወረዳ



Aanaa Gadaab Hasaasaa

Furtuu
- ⊙ magaalota aanichaa
- - - - daandii Asfaltii Dodolaa
- —v daangaa gandootaa
- Kuolleejjii hojii Gamtaa Ardaa yitaa

በጥናቱ ውስጥ የቀረቡ የኦሮምኛ ጽሁፎችን ለማንበብ ያመች ዘንድ የቀረበ የአነባበባቸውን ሁኔታ የሚያሳይ መግለጫ

የኦሮምኛ ቋንቋ ተነባቢ ፊደላት /Dubbifamaa Qubee Guguddaa fi xixiqqaa

Bb	Cc	Dd	Ff	Gg	Hh	Jj	Kk	Ll	Mm	Nn	Pp	Qq	Rr	Ss	Tt
ባ	ጫ	ዳ	ፋ	ጋ	ሀ	ጃ	ካ	ላ	ማ	ና	ፓ	ቃ	ራ	ሳ	ታ

Vv	Ww	Xx	Yy	Zz
ቫ	ዋ	ጣ	ያ	ዛ

የኦሮምኛ ቋንቋ አናባቢ ፊደላት /Dubbachiftuu-Qubee Guguddaa Xixxiqqaa

Aa	Ee	Ii	Oo	Uu
አ	ኤ	ኢ	ኦ	ኡ

ድርብ ፊደላት/ Qubee Dachaa/

CH	DH	NY	PH	SH
ቻ	ዳ	ኛ	ጳ	ሻ

ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ

ላልተው ሲነበቡ

da = ደ

de = ዴ

di = ድ

do = ዶ

du = ዱ

ለምሳሌ፡-

sadii ሰዲ(ሶስት)

saddeet ሰዴት (ስምንት)

ጠብቀው ሲነበቡ

ddaa = ዳ

ddee = ዴ

ddii = ዲ

ddoo = ዶ

dduu =

አጭርና ረዥም ድምጾች

አጥረው ሲነበቡ

fa= በ

fe = ቤ

fi = ቢ

fo=ቦ

fu = ቡ

ለምሳሌ፡-

fayyaa ፊያ (ጤና)

faaya ፋየ (ጌጥ)

ረዝመው ሲነበቡ

faa= ባ

fee = ቤ

fii = ቢ

foo= ቦ

fuu= ቡ

1.መግቢያ

ቁሳዊ ባህል የአንድን ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚያንጸባርቁ ተጨባጭ የማህበረሰብ የጥበብ ውጤቶችን የሚያጠና የባህል ዘርፍ ነው። ከነዚህ መካከል አልባሳትና ጌጣጌጥ ይጠቀሳሉ። ሰዎች አካላቸውን ከብርድ፣ከነፋስና ከጸሃይ ለመከላከል ሲሉ በየዘመናቱ ለአካል መሸፈኛ የሚሆኑ ቁሶችን ሲሰሩ ኖረዋል፤ እነዚህን ቁሶች ከአካባቢአቸው በሚያገኟቸው የተፈጥሮ ሃብቶች ሲሰሩ ነበር፤አሁንም እየሰሩ እየተጠቀመባቸው ይገኛሉ።

እንደ የማህበረሰቡ የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ የአኗኗር ባህልና እንደ የሚኖርበት አካባቢ የአየር ሁኔታ አልባሳቱም ሆኑ ጌጣጌጡ ከተለያዩ ነገሮች ይሰራሉ። ኑሮው ከከብቶች ጋር በተቆራኘ ማህበረሰብ ውስጥ የከብቶች ቆዳ ለገላ ለልብስነት ይውላል፤ በደን ሃብት በበለጸገ አካባቢ በሚኖር ህዝብ ዘንድ የተለያዩ የቅጠል አይነቶች አገልግሎት ላይ ሲውሉ ይችላሉ። በዚህም ሆነ በዚያ የሚስተዋለው ግን የሰዎች የፈጠራ ችሎታ ነው። ይህም ችሎታ ከተራ ወደ ውስብስብና ምጡቅ የፈጠራ ጥበብ በየዘመናቱ ይለወጣል፤ በለውጥ ዘመን ውስጥ የሚደረገው ሽግግርም የተለያዩ የፈጠራ ጥበቦችን እያዳበረ፣ እያሻሻለና እያጠናከረ እንዲሄድ ያደርገዋል።

የአርሲ ህዝብ ቀደም ባሉት ጊዜያት ቀደም ባሉት ጊዜያት ኢኮኖሚው በከብት እርባታ ላይ የተመሰረተ ነበር፤አሁንም ከእርሻ ጎን ለጎን ከብት እርባታን እያካሄደ ይገኛል። በመሆኑ የከብቶች ቆዳ ከልጅ እስከ አዋቂ ለልብስነት ያገለግላል ። ይህም ከከብት ቆዳ የሚሰራ ልብስ በየዘመናቱ በተለያዩ የለውጥ ሂደቶች ውስጥ አልፏል። ከተራ የቆዳ መሸፈኛነት እስከ በተለያዩ ጌጦች ያማረ የበዓልና የዝግጅት ልብስነት። ከቆዳ ልብስ በተጨማሪ ከጥጥ የሚሰሩ ልብሶች ጥቅም ላይ ውለዋል። እንደየዘመኑና የማህበረሰቡ የኑሮ ደረጃ ከፋብሪካ የወጡ ጨርቆች በተለያዩ ጌጦችና ዲዛይኖች አምረው ማህበረሰቡ እየተጠቀመባቸው ናቸው። ማህበረሰቡ ለመዋቢያነት አገልግሎት ሲል በባህላዊ መንገድ የሚያበጃቸው የእጁ የጥበብ ውጤት የሆኑት ጌጣጌጡም እንዲሁ ናቸው፤የተለያዩ የእድገት ደረጃዎችን አልፈዋል፤በዚህ የዘመን ለውጥ ውስጥም የጠፉ፣በሌላመንገድ የተሰሩና አዲስ የተፈጠሩ የጌጥ አይነቶች አሉ።

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች ቀርቧል። የመጀመሪያው ምዕራፍ ይህንኑ መግቢያ ጨምሮ ዓላማ፣መንስኤ ጥናት፣የጥናቱ አስፈላጊነት የጥናቱን ዘዴ የመረጃ አሰባሰብ፣የመስክ ቆይታን፣ ያጋጠሙ ችግሮቻቸውንና መፍትሄዎችን ይዟል።

ሁለተኛው ምዕራፍ ክለሳ ድርሳንን የያዘ ሲሆን በተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ተዛማጅ ስራዎቹ ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት ተዳስሷል። ከጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ጋር ተዛምዶ

ያላቸው የንድፈሀሳብ ስራዎችም በዚህ ክፍል ተካተዋል። በሶስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ አካባቢ አጠቃላይ ባህላዊ እና ማህበራዊ ዳራ ተካቷል፤ የጥናቱ አካባቢ ማህበረሰብ የመሰረተ ልማትና የኢኮኖሚ ሁኔታ ቀርበዋል። አራተኛው ምዕራፍ በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች የተገኘው የመስክ መረጃ ትንተና በዋና እና በንዑስ ክፍሎች ተከፋፍሎ የቀረበበት ነው። አምስተኛው ደግሞ የጥናቱን ማጠቃለያና የመፍተሄ ሃሳቦችን ይዟል። በመጨረሻም ዋቢ ጽሁፎችና አባሪዎች ተያይዘው ቀርበዋል።

1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ርዕስ ለመምረጥ ምክንያት የሆነኝ በአርሲ ሴቶች የስራ ግጥሞች ላይ ያቀረብኩት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፌ ነው። በዚህ ጽሁፌ የአርሲ ሴቶች አልባሳትን በሚመለከት አልባሳትን የሚመለከቱ ባህላዊ መረጃዎችን በዳራነት አንስቼ ነበር፤ እነዚህንም ጉዳዮች በሚመለከት በሁለተኛ ዲግሪ የፎክሎር ትምህርት ባገኘሁት እውቀትና ተጨማሪ ንባብ ለብቻቸው ማጥናት እንደምችል ስለተረዳሁ ርዕሱን መረጥኩ።

1.2 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት በአርሲ ሁለት ወረዳዎች(ኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ) አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም የሚከተሉትን አቢይና ዝርዝር አላማዎች ይዟል።

የጥናቱ ዐቢይ አላማ፡- በምዕራብ አርሲ ዞን በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች ላይ የተደረገው ይህ ጥናት ዐቢይ አላማው በሁለቱ ወረዳዎች የሴቶች የባህል አልባሳትና ጌጣጌጥን የቀድሞ እና የአሁን ይዞታ መመርመርና ያሉበትን ደረጃ ማሳየት ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- አልባሳቱንና ጌጣጌጡን በጠቀሜታቸው ከፋፍሎ ማሳየት
- በሃይማኖት ምክንያት የሚከሰት የአጠቃቀም ልዩነት መኖር አለመኖሩን መፈተሽ፣ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹን ለይቶ መግለጽ እንዲሁም የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ያሉበትን ደረጃ መፈተሽ ምን እንደሚመስል መግለጽ ናቸው። እነዚህን አላማዎች በመያዝ ጥናቱ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።
- በሁለቱ ወረዳዎች የሚታዩት የአርሲ ሴቶች ባህላዊ አልባሳት ምን ምንድናቸው? ጌጣጌጦችስ?

- እነዚህ አልባሳትና ጌጣጌጦች በጊዜ ሂደት የተለወጡበት አጋጣሚ አለ? ከሆነስ ምክንያቱ ምንድነው?

- ሴቶቹ የሚለብሷቸው ልብሶችና የሚያደርጓቸው ጌጣጌጦች በዕድሜና በጋብቻ ሁኔታ የተለያዩ ናቸው?

- አልባሳቱም ሆኑ ጌጣጌጦቹ ከህገረሰባዊ ማንነት ጋር የሚያቆራኛቸው ጉዳይ አለ?

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በሀገራችን የቱሪዝም መስፋፋት በሰፊው እየተነገረ ባለበት ባሁኑ ወቅት በአርሲ በሁለቱ ወረዳዎች የአልባሳቱና የጌጣጌጡን የቱሪዝም መስህብነት መጠበቅና ማስተዋወቅ ለሚፈልግ አካል መረጃ ይሰጣል፡፡ የልማድ የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎችን ማሰልጠን ባህሉን ለማሳደግና ለማስፋፋት ለሚሰሩ አካላት ትኩረት እንዲያደርጉ ጥቆማ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

1.4 የጥናቱ ወሰን

አርሲ ሰፊ በመሆኑ ጥናቱን ለማድረግ ሁሉንም የአርሲ አካባቢዎች ማዳረስ አዳጋች ነው፤ተጨባጭ የሆነ ውጤት ለማግኘትም መምረጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ ምዕራብ አርሲ ዞን ላይ አተኩሯል፡፡ ከዞኑ 12 ወረዳዎችም ኮኮሳ እና ገደብ ሀሳሳ የሚባሉት ሁለት ወረዳዎች ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ወረዳዎች የተመረጡበት ምክንያት የአርሲ ኦሮሞ ባህላዊ ጉዳዮች በሰፊው የሚገኙባቸው በመሆናቸው እና የጥንቱ /የባህሉን በዘመናዊ መንገድ አስመስሎ የመስራትና የመጠቀም ሁኔታ ተስፋፍቶ የሚገኝባቸው በመሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም ሴቶቹንም ሆነ የአርሲ ማህበረሰብን የሚመለከቱ ሌሎች ባህላዊ ጉዳዮች በዚህ ጥናት አልተካተቱም፡፡

1.5 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ ሃሳቦች

ከዚህ በታች በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ቀርበዋል፡፡

1.5.1. ያገጠሙ ችግሮች

የጥናት ስራው ችግር በአብዛኛው የተከሰተው በመስክ ቆይታ ወቅት ነው፡፡ ጥናቱን ባደረግኩባቸው ሁለት ወረዳዎች ያጋጠሙኝ ችግሮች የሚከተሉት ነበሩ፡፡

በሀሳሳ፡- የሀገር ሽማግሌዎችን በተፈለገው ጊዜና ሰዐት ማግኘት ያለመቻል አንደኛው ችግር ነበር፡፡ ሽማግሌዎቹ የተለያዩ ቤቶች ያሏቸው በመሆናቸውና በየጊዜው በተለያዩ ቦታዎች የሚዘዋወሩ በመሆናቸው በተፈለገው ጊዜ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር፤

- የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎቹ በአብዛኛው የሚሰሩት በትዕዛዝ በመሆኑ የአሰራር ሂደቱን በመስክ ስራ ወቅት እንደተፈለገው ለማግኘት አልተቻለም ነበር፡፡
- ቃለ መጠይቅ በተደረገበት ወቅት የድምጽ መረጃ ከመስጠት ውጪ ፎቶ ለመነሳት ፈቃደኛ ያልሆኑ የመረጃ አቀባዮች ነበሩ፡፡
- በመስክ ቆይታ በተለያዩ ቢሮዎች የሚሰሩ ሰራተኞችን አግኝቶ ማነጋገር አስቸጋሪ ነበር፤

ኮኮሳ፡- በአካባቢው መረጃ አቀባዮች ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጉዳዮች በሰፊው ለመናገር የመሰላቸት ሁኔታ ይታይባቸው ነበር፡፡ በግል መረጃ እንዲሰጡኝ ያነጋገርኳቸው መረጃ አቀባዮች ፎቶ ለመነሳትም ሆነ መረጃ ለመስጠት ገንዘብ ይጠይቁ ነበር፤ገንዘብ በነፍስ ወከፍ ለመክፈል ብስማማም የሰዎቹ አፍ ከልብ አለመሆን አስቸጋሪው ጉዳይ ነበር፡፡

- በአካባቢው ዝናብ ይጥል ስለነበር በሚሊኒየም የበዐል አከባበር ላይ ሴቶቹ ሊያቀርቡት ታስቦ የነበረው ፕሮግራም ሳይቀርብ መቅረቱ አለባበሱን ከነአጋጣሚው ለመቅረጽ አልተቻለም ነበር፡፡
- ሴቶቹ ስለለበሱት ልብስና ጌጥ ለመናገር መፍራት፤ስለባህላችን ከተናገርን የቀድሞው አይነት ችግር ባህላችንን ይገጥመዋል የሚል ስጋት ያላቸው በመሆኑ ለመረጃ አሰባሰቡ አንድ መሰናክል ሆኖ ነበር፡፡

1.5.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

- በመጀመሪያው ዙር ያላገኘኋቸውን የሀገር ሽማግሌዎች የቤት አድራሻና ስም በመውሰድ ለሚቀጥለው ጊዜ ቀጠሮ ይዤ መረጃውን ለማሰባሰብ ችያለሁ፡፡

- በተለይ የማህበር የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎች ቁሶቹን በመጠኑ እየሰሩ ማስቀመጥ መጀመራቸው የአሰራር ሂደቱን ለመመልከትና በቪድዮ ለመቅረጽም ሆነ ፎቶ ለማንሳት ጥሩ አጋጣሚ ነበር፤እንዲሁም ፎቶ ለመነሳት ፈቃደኛ ያልሆኑትን የቃል መረጃውን ብቻ መውሰድን በአማራጭነት ተጠቅሜያለሁ።

- ከቁልፍ መረጃ አቀባዬ እንዲሁም የመረጃ ምንጮች ጠቋሚዬ ጋር በመሆን ከስራ ሰዐት ውጪ የሚመለከታቸውን የመንግስት ሰራተኞች ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ በማመቻቸት መረጃውን ለማግኘት ችያለሁ።

- በኮኮሳ የሀገር ሽማግሌዎቹ እንዳይሰለቹና በሚመቻቸው ጊዜ እንዲነግሩኝ በማድረግ ጊዜ በመስጠትና ጥያቄዎችንም በመደጋገም በተቻለ መጠን መረጃውን ሰብስቤያለሁ።

- የጥናቱ ዓላማ ባህሉን ማስተዋወቅ፣እንዲያድግ የበኩሉን ጥረት መሆኑን በመግለጽ ጥያቄዎችን በተለያየ መንገድ በማቅረብ በቂ መረጃ ያለማግኘት ችግሩን ያቃለልኩ ሲሆን ገንዘብ ለጠየቁኝ መረጃ አቀባዮች ተገቢውን በመክፈል መረጃ እንዲሰጡኝ አድርጌያለሁ፤ ብዙ ለመናገር ፈቃደኛ በማይሆኑበት ወቅት ሶስት እና አራት ሆነው ባሉበት ጥያቄዎችን በማንሳትና ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግም ችግሩን ማቃለል አንዱ መፍትሄ ነበር።

1.6. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምርን ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን ከዚህም የምርምር አይነት ገላጭን ተግባራዊ አድርጓል። በዚህም መሰረት ለጥናቱ አላማ መሳካት የሚጠቅሙ መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል። መረጃ አቀባዮቹም የተመረጡት በአመቺ/ግኝት ናሙና ነው። ያለው እንዳወቀ እንደሚሉት ይህ የናሙና አይነት ጥናቱን ለማካሄድ አመቺ በሆኑ ነገሮች ላይ ተመርኩዞ መረጃ አቀባይ የሚመረጥበት ነው።(1998፣135) በዚህም መሰረት ለጥናቱ የተመረጡት መረጃ አቀባዮች ባጠቃላይ 18 ሴቶች እና 12 ወንዶች ናቸው። ከነዚህ መሀከል ስድስቱ በባህልና ቱሪዝም እንዲሁም ተዛማጅነት ባላቸው መንግስት መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ ናቸው። መረጃ አቀባዮችን በመምረጥም ሆነ መረጃ በመስጠት የምዕራብ አርሲ ዞን የባህልና ቱሪዝም የባህል ኤክስፐርት የሆኑት አቶ ቦንሰሞ ሚኤሶ ከነዚሁ መሀል ተመርጠዋል። ከተቀሩት ውስጥ ከኮኮሳም ሆነ ከሀሳሳ ሶስት ሴቶችና ሶስት ወንዶች በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ተመርጠዋል። መረጃ ለማሰባሰብም ቃለመጠይቅንና ምልከታን ተጠቅሜያለሁ። የመረጃው

አተናተን ሂደትንም ያከናወንኳቸው ተግባራትንም በተመለከተ በተገለጹት ዘዴዎች መረጃዎችን ሰበሰብኩ፣ ወደጽሁፍ ለወጥኳቸው፤ ወደአማርኛም ተረጎምኩ፤ከዚያም በትንተናው ክፍል ተገቢ በሆነ ቦታ የኦሮምኛውን ከዚያም የአማርኛ ትርጉሙን በማቅረብ በዋናና ንዑስ ክፍሎች አቀረብኳቸው።

1.7 የመረጃ አሰባሰብ

በመስክ መረጃ አሰባሰብ ወቅት የተጠቀምኩባቸው መቼቶች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼት (artificial setting) ሲሆን ሁለተኛው ተፈጥሮአዊ መቼት(natural setting) ነው።(ፈቃደ 1991) በመጀመሪያ ዙር የመስክ ስራ ወቅት በሀሳሳ የአልባሳቱንና ጌጣጌጡን አሰራር ሂደት ለቪድዮ ቀረጻ በሚያመች መንገድ በግልም ሆነ በማህበር በሚሰሩ ሰዎች ቤት ተገኝቼ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለመቅዳት ችያለሁ። በኮኮሳም እንዲሁ አልባሳቱና ጌጣጌጡ በተወሰኑ ሴቶች ቤት የሚገኙ መሆናቸውን ከቁልፍ መረጃ አቀባዩ እና ከባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች በመረዳቴ የገበያ ቀንን ምክንያት በማድረግ በየአካባቢው መልዕክት በመላክና ልብሱን ለብሰው እንዲመጡ በማድረግ መረጃውን ሰብስቤአለሁ። በሀሳሳ በሚያዚያ ወር መጨረሻና በግንቦት ወር መጀመሪያ ባደረግኩት ቆይታ የአልባሳትና የጌጣጌጥ ሰራተኞቹ በተለይ የማህበር ሰራተኞቹ አዘጋጅተው ሰርተው ማስቀመጥ መጀመራቸው ጥሩ አጋጣሚ ነበር ።በዚህም መሰረት እየሰሩ በነበረበት ሁኔታ ቀረጻው ተካሂዷል። በኮኮሳም በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚሊኒየም በዐል የተከበረበት አጋጣሚ ከበፊቱ የበለጠ ቁጥር ያላቸው ተጠቃሚዎችን ለማግኘት አስችሎኛል።

1.8 የመስክ ቆይታ

ወደ መስክ ከመውጣቴ በፊት ስለአካባቢውም ከቤተመጻህፍት የተገኙ ጽሁፎችን በማንበብ፣ ከ"ቢፍቱ ኦሮሚያ የባህል ቡድን" የአርሲ ተወላጆችን በማነጋገርና ትኩረት የሚደረግባቸውን ቦታዎች በመለየት ቅድመ ዝግጅት አደረግኩ። ከዚያም ከክፍለትምህርቱ የትብብር ደብዳቤ በማጻፍ ወደ ሻሸመኔ ሄድኩ። ሻሸመኔ የምዕራብ አርሲ ዞን ዋና ከተማ ስትሆን ከአዲስ አበባ 250 ኪ.ሜ ትርቃለች። እዚያ እንደደረስኩ ያመራሁት ወደዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነበር። በዚህ ቢሮ ያከናወንኳቸው ተግባራትም በቅድሚያ ባህሉን በንጽጽር ለማጥናት ያመቸኝ ዘንድ የጥናት ወረዳዎቹን መወሰን ነበር። በዚህ መሰረት የኮኮሳና የገደብ ሀሳሳ ወረዳዎችን መረጡልኝ። በመረጣው ወቅት በተለይ ኮኮሳ የሚባለው አካባቢ አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል በመገመት ሌሎች ወረዳዎችን እንድመርጥ አማራጮች ቀርበውልኝ ነበር።

ነገር ግን እዚያው መሄዱ የተሻለ መሆኑን ስላመንኩበት ወደተመረጡት አካባቢዎች ለመሄድ ስለአካባቢው የሚያውቅ ሰው እንዲጠቁሙኝ አደረግኩ ። በቢሮው የባህል ኤክስፐርት ሆነው የሚሰሩት አቶ ቦንሰሞ ሚኤሶ ለብዙ አመታት በሁለቱም ወረዳዎች በመምህርነት ያገለገሉ በመሆናቸው መረጃ አቀባዮችን በመምረጥ በኩልና መረጃ በመስጠት ይተባበሩኛል ብዬ ስላመንኩ ወጪአቸውን ሸፍኜ አብረውኝ እንዲሄዱ ተስማማሁ። ከአቶ ቦንሰሞ ጋር ከተነጋገርኩና ቀጠሮ ከያዝኩ በኋላ በቀጥታ የሄድኩት ወደዞኑ የአስተዳደር ቢሮ ነበር። አቶ ታምራት ተካልኝ፣የእቅድና ፕላን ክፍል ሀላፊ ፣ የተለያዩ መረጃዎችን ሰጥተውኛል። የዞኑን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁኔታ የሚያመለክቱ ጽሁፋዊ መረጃዎችንም አግኝቻለሁ። አቶ ታምራት በጽሁፍ ብቻ ሳይሆን ቃላዊ መረጃም ሰጥተውኛል።

ከዚህ በኋላ ወደተመረጡት ወረዳዎች የመጀመሪያ ዙር ጉዞዬን አደረግኩ። ጉዞአችን በመጀመሪያ ወደ ሀሳሳ ከዚያም ወደ ኮኮሳ እንዲሆን ከአቶ ቦንሰሞ ጋር ተስማማን። በማግስቱም ጉዞው ወደዚያው ሆኖ በ26/07/00 ዓ.ም አሳሳ ደረስን።አሳሳ ከሻሸመኔ 84 ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኝ የወረዳ ከተማ ነች፤ አየሯም ሞቃታማ ነው። በቀጥታ ያመራሁት ወደ ወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነበር። በባህል ቢሮው የተለያዩ የባህል ቁሶች ይስተዋላሉ። የምግብ ፣የመጠጥ ማቅረቢያዎች፣ የተለያዩ የጌጥ አይነቶች በሃላፊው ጥረት በማህበረሰቡ ተሰብስበው ተቀምጠው ይታያሉ። ጌጣጌጦቹ ግማሹ ፊት ለፊት ሌላው የተስተካከለ ቦታ በማጣት በመሳቢያ ውስጥ ተቀምጠዋል፤ ከቢሮው መግቢያ በስተቀኝ በኩል ባህላዊ የምግብ ማስቀመጫዎችና የመጠጫ እቃዎች የድሮውና የአሁኑ ተቀላቅለው ተደርድረው ይታያሉ። በዚህ ወረዳ የመጀመሪያ ዙር ቆይታዬ የአልባሳትና ጌጣጌጦች ሰሪዎች ቤት ድረስ በመሄድ አልባሳቱን ወይም ጌጣጌጦቹን ሲሰሩ ለማየትና ቪድዮ ለመቅረጽም ችያለሁ።

በ3/08/00 ወደ ኮኮሳ ተጓዝኩ። ኮኮሳም ሆነ ሀሳሳ ለመሄድ ዶዶላ ከተማ መድረስ የግድ ነው። በዚያው ቀን ከዶዶላ ኮኮሳ ከተማ እንደገባሁ መጀመሪያ ከዞኑ የተጻፉልኝን ደብዳቤዎች ለየመስሪያ ቤቶቹ ሰጠሁ። የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊው አቶ ብርሃኑ በሪሶ መረጃ በመስጠትና የሀገር ሽማግሌዎችን በመምረጥ ተባብረውኛል። በዚህን ጊዜም ቃለመጠይቅን ተጠቅሜአለሁ። በተጨማሪም ቪድዮ፣የፎቶ ካሜራና ማስታወሻዬን ይገቤ በገበያው በመገኘት የሴቶችን የአለባበስ ሁኔታ ለመመልከት ችያለሁ።

ገበያው ውስጥ ሴቶቹ በተለይም እናቶቹ ከአንገታቸው ላይ ከአንድ እስከ ሶስትና ከዚያም በላይ ጌጥ አድርገው ይታያሉ። በለበሱት ልብስ ላይ ከቆዳ የተሰራ ከሎ(kal'oo) ደርበው የሚሄዱ ሴቶችን ተመልክቻለሁ። ጸጉራቸው ላይ ጉፍታ አድርገው የሚሄዱ ሴቶችም ነበሩ።

ከ24/9/2000 ዓ.ም እስከ 3/9/2000 ዓ.ም በቆየው የሁለተኛ ዙር የመስክ ቆይታም ምልከታንና ቃለመጠይቅን ተጠቅሜአለሁ፡፡ በነዚህ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ያገኘኋቸውን መረጃዎች ህያው ለማድረግም የፎቶ ማንሳት እና የቪድዮ ቀረጻ እንዲሁም የድምጽ ቀረጻ ሥራ አከናውኛለሁ፡፡ በሀሳሳ ትልቁ የገበያ ቀን ማክሰኞ ነው፡፡ በገበያ ውስጥ የሚታዩት ሴቶች በአብዛኛው የእስልምና ሃይማኖትን አለባበስ የሚያንጸባርቁ አልያም የፋብሪካ ጨርቆችን አልባሳት የለበሱ ናቸው፡፡ በገበያው ውስጥ በአልባሳትና ጌጣጌጥ ስራ በተሰማሩት ሴቶች ለሽያጭ የተዘጋጁ የወተት፣ የገንፎ፣ የቅቤ እቃዎች ይታያሉ፡፡ አልባሳቱም ሆኑ ጌጣጌጡ እቤት የሚሸጡትና ገበያ የሚወጡት የተለያዩ ናቸው፡፡

በኮኮሳ ሁለተኛ ዙር ቆይታ በ2/9/2000 ዓ.ም በኮኮሳ የሚሊኒየም በዓል በወረዳ ደረጃ የተከበረበት ቀን ስለነበር የአልባሳቱንና ጌጣጌጡን መለበሻ አጋጣሚ ተመልክቻለሁ፡፡ በዕለቱ በዓሉን በማስመልከት ወንዶቹም ሆኑ ሴቶቹ ባህላዊ አልባሳትን ለብሰው ለማየት ችያለሁ፡፡ ትኩረቴ የነበሩት ሴቶችም ከልጃገረድ እስከ አዋቂዎች የባህል አልባሳቱን ለብሰው በበዓሉ ላይ ተገኝተዋል፡፡ በዚህን ጊዜም የቪድዮ ቀረጻና የፎቶ ማንሳት ተግባራትን አከናውኛለሁ፡፡ ከበዓሉ ፍጻሜ በኋላም ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም የባህል ኤክስፐርት፣ አቶ ሀጂ ሀሰን ጋር በመሆን የሃገር ሽማግሌዎችን ለማነጋገርና መረጃ ለማግኘት ቻልኩ፡፡

2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ በቁሳዊ ባህል፣ በአልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ የተደረጉ ጥናቶችና ንድፈ ሃሳቦች ዳሰሳ ይደረጋል።

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በአርሲ በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ የአለባበስና የአጊያጌጥ ሁኔታ ላይ የተደረገ ጥናት አላገኘሁም። በመሆኑም ይህን ጥናት በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ቀርቧል። ቁሳዊ ባህል ከፎክሎር ዘሮች መካከል አንዱ ቢሆንም ትኩረት ተሰጥቶት ሲጠና አልቆየም። ይህ ሲባል በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ጭራሽ የሉም ማለት ሳይሆን ከሌሎች ዘሮች በተለይ ከስነቃል ጋር ሲነፃፀሩ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት የተደረጉ ጥናቶች በቁጥር አነስተኛ ናቸው። (Fekade:2001) በመሆኑም በዚህ ክፍል ለተዛማጅነት የተመረጡት ስራዎች ከጥቂቶቹ በስተቀር በቀጥታ ቁሳዊ ባህል ላይ የተሰሩ አይደሉም።

ውብሸት አሰፋ (1978) "የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ባህል" የሚለው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው የመጀመሪያው ጥናት ነው። አጥኚው በመግቢያው ጥናቱን ባደረገበት ወቅት መለበሳቸውና መደረጋቸው እየቀረ የመጣውን አልባሳትና ጌጣጌጦች ሰብስቦ ከነስማቸው በመቀረስ ለትውልድ ማስተላለፍ ዓላማው እንደሆነ ገልጿል። አልባሳቱና ጌጣጌጡ የሚጠሩባቸው ስያሜዎችም ከቋንቋው እየወጡና እየጠፉ መሄዳቸው ያሳሰበው በመሆኑ ስሞቹን ሰብስቦ ለማጥናት መነሳሳቱን ጠቁሟል። ስያሜዎቹን ከመፃህፍትና ከግለሰቦች በመሰብሰብና ከመፃህፍት የሰበሰባቸውን ስያሜዎች በሚመለከት በመጠየቅና በማረጋገጥ ትንተና ሰጥቶባቸዋል። ጥናቱን ያደረገው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርመር ኢንስቲቲዩት በመገኘትና በመጠየቅ ሲሆን ከዚያም ያገኛቸውን አልባሳትና ጌጣጌጥ ፎቶ በማንሳት ለጥናቱ ዓላማ አውሏቸዋል።

ውብሸት አልባሳትና ጌጣጌጥ የሚል ርዕስ ይዞ ይነሳ እንጂ በጥናቱ ቅባት፣ ሽቶና ኩል በማለት የመዋቢያ ቁሶችንም አካቷል። ለዚህም ምክንያቱ አንዲት ሴት አልባሳቱንና ጌጣጌጡን ስታደርግ መኳኳልም አብሮ ይመጣል የሚል ነው። አልባሳት መቼ፣ እንዴት መለበስ ጀመሩ? ለሚለው ታሪካዊ መረጃን መሠረት በማድረግ ማብራሪያ ሰጥቷል። ባጠናው ማህበረሰብ አልባሳትና ጌጣጌጥ ከእምነትና ልማድ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው ገልጿል።

ባጠቃላይ አጥኚው ከተነሳበት አላማ አኳያ አልባሳቱን ማን? መቼ? ይለብሳቸዋል የሚል መረጃ በመስጠት በፎቶግራፍ ማስደገፉ ጥናቱን ተጨባጭ አድርጎታል።

ሁለተኛው ጥናት Ezra Ayele(1987) "Object Language used in Arsi Oromo" የሚል ነው፡፡ ይህ በስነልሳን የትምህርት ክፍል የቀረበ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ሲሆን ቃላዊ ያልሆነ ተግባቦትን (Non verbal communication) መሠረት ያደረገ ነው፡፡ አጥኚው በዓላማው የአርሲን ማህበረሰብ ባህል ባጠቃላይ ማጥናት ሳይሆን ከባህሉ የተወሰኑትን በመምረጥ የቁሳዊ ተግባቦትን (Object Language) ፋይዳ ማመላከት መሆኑን ጠቁሟል፡፡ በጋብቻ ቀንና ከጋብቻ ጋር በተያያዙ ክንዋኔዎች፣ በክበራዎች፣ በሞትና በቀብር ወቅት የሚከናወኑ ባህላዊ ልማዶችንና ለዚያው ተግባር የሚውሉ ቁሳቁሶችን በመዘርዘር የማግባባት ሃይላቸውና ባህልን፣ እምነትንና ፍላጎትን የመግለፅ አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ገልጿል፡፡ በጥናቱ ቃላዊ ያልሆኑ የተግባቦት መንገዶች በማለት ከቀረቡት ውስጥ አልባሳትና ጌጣጌጥ ይገኙበታል፡፡ ከዕድሜና ከኑሮ ደረጃ ጋር እንዲሁም ከሃዘንና ከደስታ ጋር በተያያዘ የሚለበሱት አልባሳት የተለያየ ገፅታ እንዳላቸው ተገልጿል፡፡

ሶስተኛው ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳስሎ ያለው የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት የአያል አድማሱ(1992) "የጎጃም አካባቢ የአልባሳት ስያሜ" የሚል ነው፡፡ አጥኚው በጥናት አካባቢው ከዘመናዊ ፋሽን ጋር የተያያዙ ልብሶችን ስያሜዎች ነው ያጠናው፡፡ ስነቃልነት ያላቸውን ስያሜዎች ሳይጠፉ መዝግቦ በመዘክርነት ማስቀመጥ ጥናቱን ለማድረግ ካነሳሱት ምክንያቶች መካከል አንዱ መሆኑን ገልጿል፡፡ የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በአጥኚውና በጓደኞቹ አማካይነት ሲሆን የመረጃውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሴቶችና ነጋዴዎች ለመረጃ ሰጭነት ተመርጠዋል፡፡ የስያሜ ምንነት፣ የስያሜ ምንጮች፣ የስያሜ ማህበራዊ ሚና የሚሉትም ጉዳዮች ተካተዋል፡፡ ለልብሶች የሚሰጡ ስያሜዎች የሰያሚውን ውስጣዊና ትክክለኛ ስሜት እንደሚገልፁ፣ የተሰያሚውንም ውስጣዊና ውጫዊ ባህሪ እንደሚያንፀባርቁ ምሳሌዎችን በመስጠት ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በተጨማሪም ስያሜው ለልብሱ ከተገለፀው ባህሪይ ምንን መሠረት ያደረገ እንደሆነ በመጠቆም ዝምድናውን ከስነልሳናዊ ፍቺ ጋር በማጣመር አቀርቧል፡፡ ስያሜዎቹም ከነጋዴ፣ ከለባሽ እና ከተመልካች አንፃር መመሳሰልና መለያየት እንደሚንፀባረቅባቸው በጥናቱ ተገልጿል፡፡

የውብሸት ጥናት አልባሳትና ጌጣጌጡ የሚለበሱባቸውን አጋጣሚዎች ለመመልከት በመሞከሩ፣በጾታ ረገድም ሴቶች ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የመዋቢያ ቁሳቁስን ማካተቱ፣በአብዛኛው ትኩረቱን ማህበረሰቡ ላይ ሳይሆን ስያሜዎቹ ላይ በማድረጉ ደግሞ ይለያል፡፡

እዝራ የተነሳበት ዓላማ ይለይ እንጂ በአርሲ ማህበረሰብ የሴቶችን አልባሳትና ጌጣጌጥ ተግባቦታዊ ፋይዳ ለማሳየት መሞከሩ በተወሰነ መልኩ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ በእዝራ ጥናት አልባሳቱና ጌጣጌጡ ብቻ ሳይሆን ባህላዊ ልማዶችም ተካትተውበታል፡፡ በጥናቱም ተተኳሪ የሆኑት በባህላዊ ልማዱ፣ በከበራውና በመሳሰሉት ላይ የሚሳተፉት የማህበረሰቡ ክፍሎች ናቸው፡፡ የእኔ ጥናት ዋና ትኩረቱ የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ በመሆኑ ከእዝራ ጥናት ይለያል፡፡

አያል አድማሱ ለአልባሳት የቅድሚያ ሽፋን መስጠቱ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ከቋንቋ ፅንሰ ሃሳብ አኳያ የተመለከተ መሆኑ ደግሞ ከዚህ ጥናት ይለየዋል፤የፆታ ልዩነት የሌለው መሆኑ፣ ጉዳዩን ከቋንቋ ፅንሰ ሃሳብ አኳያ የተመለከተ መሆኑም ከዚህ ጥናት ይለየዋል፡፡አያል ትኩረቱን ያደረገው የፋሽን አልባሳት ላይ ነው፡፡ ዋና ጉዳዩም ስያሜን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለትምህርት የተሰሩ ሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች በቀጥታ ጉዳያቸው አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ ባይሆንም በእግረመንገድ ያነሷቸው ነጥቦች በመኖራቸው ተቃኝተዋል፡፡

የመጀመሪያው ጥናት የሄለን አላምረው(1999) "ባህላዊ ሽመናና ቆዳ ስራ በደንበጫና አካባቢዋ" የሚል ነው፡፡አጥኚዋ የሽመና እና የቆዳ ስራ ሰራተኞች የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎችና የአሰራር ሂደቶች ማሳየት የመጀመሪያው አላማዋ ሲሆን የባለሙያዎቹን ማህበራዊ ህይወት የሚያንፀባርቁ ስነቃሎችን መሰብሰብና መተንተን በቀጣይ አላማነት ያነሳቻቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ ጥናቷን ባካሄደችበት አካባቢ የተዘወተሩ የሽማ ስራ ውጤቶች ኩታ፣ ጋቢ እና ሃበሻ ቀሚስ መሆናቸውን ገልፃለች፡፡ እነዚህም አልባሳት በቀድሞ ጊዜ ከጥጥ ይሰሩ እንደነበርና በአሁኑ ወቅት በክር ልብሶችን የመስራቱ ሁኔታ እንዳለ አመልክታለች፡፡ በአካባቢው በተለይ "ጎጃም አዘነ" የሚባለው ልብስ ከክር የሚሰራ ሆኖ በአካባቢው እየተለመደ የመጣ መሆኑን በዚሁ ክፍል አንስታ ዋና ትኩረቷ ባህላዊው ላይ በመሆኑ የጥጥ አልባሳት ገለጻ ላይ አተኩራለች፡፡

አጥኚዋ አልባሳቱንም ከተጠቃሚዎቹ አንፃር (ፆታ፣ ዕድሜና ጋብቻ) ከመኖሪያ ስፍራቸው (ገጠር፣ ከተማ) እና የአሰራሩን ሂደትና ለስራው የሚያስፈልጉ ቁሶችን በመዘርዘር አቅርባለች፡፡ ባለሙያዎቹንም በተመለከተ በቀድሞ ጊዜያት ይደርስባቸው የነበረውን ያህል ባይሆንም በሌላው የማህበረሰብ ክፍል የመገለሉ ሁኔታ እንደሚስተዋል በተለይ ይህ በቆዳ ሰሪዎች ላይ የሚስተዋል መሆኑን የራሷን የመስክ ልምድ መሠረት በማድረግ አቅርባለች፡፡

የእነዚህን ባለሙያዎች የማህበራዊ ህይወት ደረጃ በሚገልፀው ክፍል በተለይ የሽመና ስራ ሰራተኞች በመንግስት ተደራጅተው እንዲሰሩ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ መኖሩን በትንታኔዋ ጠቅሳለች፡፡ ባለሙያዎቹ ከቤተሰቦቻቸው የወረሱትን ዕውቀት በመያዝ ያልተወሳሰቡ የጥበብ ውጤቶችን እንደሚያመርቱም በጥናቷ አመልክታለች፡፡

ዋልተንጉሥ መኮንን(2000) "የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም" በሚል ርዕስ ያቀረበው በአክሱም ጥናት የሽመና ሙያ አመጣጥና አሁን ያለበትን ሁኔታ የተመለከተ ነው፡፡ አጥኚው አላማው የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአካባቢው እንዲከሰትና እንዲስፋፋ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን መመርመር፣ ከሌሎች የማህበረሰቡ እሴቶች ጋር እንዲተሳሰሩና የማህበረሰቡ መገለጫ እንዲሆኑ ያስቻሏቸውን መሠረታዊ ጉዳዮች ጠቅሷል፡፡ በአካባቢው የተለመዱ የአሰራር ስልቶችንና ሂደቶችን ቀርሶ ማስቀመጥ ጉዳዩ እንደሆነም ገልጿል፡፡

ዋልተንጉሥ "የሽማ ውጤቶች አመዳደብ" በሚለው ክፍል ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ አልባሳትን ተንትኗል፡፡ የአልባሳቱን አይነት የሚያመለክቱ ስዕላዊ መግለጫዎችም አብረው ቀርበዋል፡፡ አጥኚው መረጃውን የሰበሰበው ከአካባቢው ታዋቂ ሰዎች፣ ከነጋዴዎች እና ከባለሙያዎቹ መሆኑን ገልጿል፡፡

ባጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ሁለት የድህረምረቃ የጥናት ወረቀቶች እያንዳንዳቸው ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸው ቅርበት የተለያየ ነው፡፡ የዋልተንጉስና የሄለን ጥናቶች በቁሳዊ ባህል የእጅ ጥበብ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ቁሳዊ ባህል በሚለው ርዕስ ስር የሚካተቱ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ በተጨማሪም አልባሳትን በሚመለከት ከሚሰሩባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች አንፃር ከአሰራር ሂደት ጋር የተያያዘ ቢሆንም የማህበረሰቡን የአለባበስ ባህል ከመግለፅ አኳያ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ የሄለንና የዋልተንጉሥ የጥናት ስራዎች ከእኔ ጥናት የሚለያቸው ደግሞ የእኔ ጥናት አልባሳትና ጌጣጌጥ ላይ ያተኮረ መሆኑ፣ በፆታ ረገድም ሴቶችን ብቻ የሚመለከት መሆኑ ነው፡፡

2.2 የንድፈ ሀሳባዊ መነሻዎችና መሠረታዊ ፅንሰ ሃሳቦች ብያኔ

በዚህ ክፍል በጥናቱ ውስጥ የሚካተቱ ፅንሰሃሳቦችን በሚመለከት በተለያዩ ምሁራን የተሰጡ የንድፈሃሳብ መረጃዎች ይቀርባሉ፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ የፎክሎር አንድ ዘርፍ የሆነውን ቁሳዊ ባህል በተመለከተ ጥቂት መረጃዎች ይሰጣሉ፡፡ በመቀጠል የጥናቱ ዋና ጉዳይ የሆኑትን ሃገረሰባዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ በሚመለከት ከቅርብ እስከ እሩቅ የተገኙ መረጃዎች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

2.2.1 ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህልን የተለያዩ ምሁራን ወጥ የሆነ ብያኔ ከመስጠት ይልቅ ልክ እንደፎክሎር በውስጡ የሚያካትታቸውን ጉዳዮች መዘርዘርን ይመርጣሉ፡፡ ቁሳዊ ባህል የተለያዩ ንዑሳን ዘሮችን በውስጡ የሚይዝ ሲሆን እነሱም እንደባህሪያቸው በተለያየ መንገድ ይጠናሉ፡፡

ፊቃደ ዶርሰንን በመጥቀስ ባቀረቡት የቁሳዊ ባህል ብያኔ በስሩ የሚካተቱትን ንዑስ ዘሮች እንደሚከተለው አቅርበዋቸዋል፡፡ "ቁሳዊ ባህል ... ሀገረሰባዊ እጅ ስራን (Folk crafts)፣ ሃገረሰባዊ ስዕልን (Folk-art)፣ ሃገረሰባዊ ምህንድስናን (Folk architecture)፣ ሃገረሰባዊ ልብስን (Folk costume) እና ሃገረሰባዊ የምግብ አሰራርን (Folk cookery)" ያጠቃልላል (ሰረዝ የራሴ) (1991፣ 15)፡፡

በዚህ መስክ የሚካተቱት እነዚህ ንዑሳን ዘሮች የየራሳቸው ባህሪይና መገለጫ ያላቸው እራሳቸውን ችለው የሚጠኑ ናቸው፡፡ ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ በስልጣኔ ሳይረቅ በፅሑፍ መግባባት ሳይጀምር የነበረ የማህበረሰብ የጥበብ ውጤት እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

> Material culture predates verbal culture by several thousand years, since tool making almost universal in all cultures, preceded the invention of writing in practically all of them. Material culture is, without question, human kind's oldest legacy of cultural expression. (Jstor፣2)

ቁሳዊ ባህል ከቃላዊ ተግባቦት ባህል በሺህ አመታት የቀደመ ክስተት ነው፡፡ ቁስን መስራት በማንኛውም ባህል ውስጥ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን በሁሉም ባህሎች ጽህፈት ከመፈጠሩ በፊት የነበረ ነው፡፡ ቁሳዊ ባህል ያለምንም ጥያቄ ከሁሉም የቀደመ የሰው ልጆች ባህላዊ መገለጫ ቅርስ/ውርስ ነው፡፡

ሰዎች ለእለት ተዕለት መገልገያ ቁሳቁስን ማበጀትና መገልገልን ከጀመሩበት ዘመን አንስቶ ከቁሳዊ ባህል ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው እንደነበረ ከጥቅሱ መረዳት ይቻላል፡፡

ይህ የጥናት ዘርፍ ከላይ እንደቀረበው የቀደመ ታሪክ ይኑረው እንጂ በሳይንሳዊ መልኩ የመጠናቱ ጉዳይ ትኩረት የተሰጠው አልነበረም፡፡ ከማህበረሰብ ህይወት ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያለው እና ቢሆንም ትኩረት ተሰጥቶት ሲጠና አልቆየም (Roberts, 1986, 433)፡፡

ቁሶችን ቀርሶ የማስቀመጡ ባህል ያስመዳበሩ ባህላዊውን ጉዳይ እየተዘነጋ በተለያየ መንገድ እየጠፋ እንዲሄድ ያደርገዋል። ለዚሁ ለባህላዊ ቁሶች መዳከም ብሎም መጥፋት ሁለት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። የመጀመሪያው የመቀረሱ ባህል ትኩረት አለመሰጠት ሲሆን ሌላው የቴክኖሎጂ መስፋፋት ነው።

ቁሳዊ ባህል የሚለው መጠሪያ በሁለት መንገድ አገልግሎት ላይ ይውላል። የመጀመሪያው የጥናት ዘርፉ መጠሪያ ሲሆን፣ ቀጣዩ ለሚጠናው ጉዳይ መጠሪያ ሆኖ መዋሉ ነው። “Material culture is the study through artifacts of the beliefs values, ideas, attitudes and assumptions of a particular community or society at a given time.” (Jstor,1) (ቁሳዊ ባህል በአንድ በተወሰነ ጊዜ የአንድን ማህበረሰብ አተያይ፣ እምነት፣ እሴት እና ሃሳብ በእጅ ጥበብ ውጤቱ አማካይነት የምናጠናበት የጥናት ዘርፍ ነው።)

በሌላም በኩል ይኸው ጽንሰ ሃሳብ ለሚጠናው ቁስ መጠሪያ እንደሚውል የቀረበው መረጃ ያመለክታል። በተጨማሪም “The term ‘material culture’ is also frequently used to refer to artifacts themselves to the body of material available for such study.” (Jstor,1) ቁሳዊ ባህል የሚለው መጠሪያ ተደጋግሞ ለሚጠኑት የጥበብ ውጤቶች መጠሪያ ይውላል በማለት ተገልጧል።

ይህ የፎክሎር ዘር በስሩ በርካታ ጉዳዮችን የሚይዝ መሆኑን ቀደም ሲል ለመግለፅ ተሞክሯል። እነዚህ ንዑሳን ዘሮችም የየራሳቸው ባህሪይ አላቸው። ይህም ባህሪያቸው እያንዳንዳቸውን ለማጥናት የሚያስችሉ መንገዶች ሊኖሩ እንደሚገባ ያመላክቱናል። እነዚህን ዘሮች የመመደቢያ መንገድም የተለያየ ሲሆን እንደሚችል ምሁራን ይገልጻሉ።

> “Sorting by physical materials does not work because of the multiplicity of substances used even at times in a single artifact. The same is true of methods of fabrication. The most promising mode of classification is by function. ”(Jstor,2)

አንድ የእደጥበብ ውጤት ከበርካታ ነገሮች ሊሰራ ስለሚችል ቁሶችን በአካላዊ ገጽታቸው ብቻ መመደብ አይቻልም። በሚመረቱበት ዘዴ ለይቶ መመደብም ያው ነው። በእጅጉ የተሻለ የሚሆነው በሚሰጡት አገልግሎት መመደብ ነው።

ቁሳዊ ባህል ቀደም ሲል እንደተገለፀው በአይነታቸው የተለያዩ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ነው። በመሆኑም የተዋጣለትና ተጨባጭ ጥናት ለማድረግ መምረጥ ተገቢ ይሆናል። ስለዚህ ቀጥሎ የዚህ ጥናት ዋና ጉዳይ ወደሆኑት አልባሳትና ጌጣጌጥ ብያኔያዊና ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት እናልፋለን።

2.2.1.1 ሃገረሰባዊ አልባሳት

ሃገረሰባዊ አልባሳት አብረዋቸው የሚሄዱ ጌጣጌጦችን የሚይዙ የቁሳዊ ባህል ንዑስ ዘር መገለጫ ናቸው። ሃገረሰባዊ አልባሳት የአንድ ማህበረሰብ መለያና የማንነት መገለጫ የጥበብ ውጤቶች ሲሆኑ በባህላዊ መንገድ በማህበረሰቡ ተሰርተው ለማህበረሰቡ የሚያገለግሉ ናቸው።

> Clothing in its wide sense includes a great range of materials that man wears or applied to his body. In addition, to garments made of woven fabrics, clothing is made from such varied materials as body paint, feathers, and sewers (The Encyclopedia Americana 1983: 99)

አለባበስን አስፍተን ስናየው የሰው ልጅ በሰውነቱ ላይ የሚያደርጋቸውንና የሚለብሳቸውን የተለያዩ ቁሶች ይገልጻል። በሽመና ከተሰሩ ጨርቆች በተጨማሪ ልብስ በአካል ላይ የሚደረግ ቅብን፣ላባዎችንና የተለያዩ በእጅ ስፌት የተዘጋጁ ልብሶችን ይይዛል።

ልብስ ከተለያዩ ቁሶች ሊሰራ የሚችልና የሰው ልጅ አካሉን ለመሸፈን የሚጠቀምበት የጥበቡ ውጤት ነው። ሰዎች ልብስን መቼ መልበስ እንደጀመረ በዘመንና በቁጥር ቀመር መግለፅ አይቻልም። ምክንያቱም የትኛው ልብስ ለመጀመሪያ ጊዜ ተለበሰ ለሚለው መረጃ ይሆኑ ዘንድ የቀደሙትን ቁሶች/አልባሳት/ ማግኘትና በእርግጠኝነት መናገር አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው። (The Encyclopedia Americana 1983)

የሰው ልጅ ልብስን መልበስ የጀመረበትን ጊዜ በትክክል መናገር ባይቻልም ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ባሉበት ዘመናት የመልበሻ ምክንያቶቹ የተለያዩ ናቸው።

ምሁራን ልብስ ለምን ይለበሳል? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ምክንያቶችን ይሰጣሉ። "We put on clothing for some of... reasons that we speak to make living and working easier and more comfortable, to proclaim (or disguise) or identities and

to attract erotic attention" (Lurie 1981: 27) (ልብስን የምንለብሰው ለተወሰኑ ምክንያቶች ነው። የስራ አካባቢያችንንና ኑሮአችንን የበለጠ ምቹና ቀለል ያለ ለማድረግ፣ማንነታችንን ለሌሎች ለማሳወቅ እና ተቃራኒ ጾታን ለመሳብ ናቸው።)

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ልብስን የምንለብሰው ። የስራ ሁኔታችንንና የኑሮ ሁኔታችንን ጤናማ ለማድረግ ፣ ሁለተኛው ማንነታችንን ለማሳየት እና ሌሎችን ለመሳብ ሲባል ነው።

ልብስ የሚለበስበት ሌላው ምክንያት ከማንነት ጋር የተያያዘ ነው። አልባሳት ያግባባሉ። ቁሳዊ ተግባቦት ከቃላዊው የበለጠ የማግባባት አቅም አለው። በመሆኑም የአለባበስ ሁኔታን በማየት የግለሰብን ብሎም የማህበረሰብን ማንነት መገመት እንዲሁም መናገር ይቻላል። ይኸውም ጉዳይ በርካታ አመታትን ያስቆጠረ ነው። For thousands of years human beings have communicated with one another first in the language of dress." (Lurie 1981፡ 3) (ለብዙ ሺህ አመታት ያህል ሰዎች አንዱ ከሌላው ጋር በልብስ ቋንቋ ሲግባቡ ኖረዋል)።

አንድ ሰው የለበሰውን ልብስ በማየት የወጣበትም ማህበረሰብ ባህል መናገር የሚቻልበት አጋጣሚ አለ። በተለይ በባህላዊ መንገድ የተዘጋጁ አልባሳትን የለበሰን ሰው በማየት ስለዚያ ግለሰብ መናገር ይቻላል። ይህም የልብስ የማግባባት ሃይል ከቤትና ከሌሎች ቁሶች የተሻለ ነው። (Lurie 1981፡ 5) በቤትም ሆነ ከልብስ ማስቀመጫ ቦታ ለመልበስ የምንመርጠው ልብስ ስለማንነታችን የሚያመላክተው ነገር አለው።

ልብስን የመልበሻ ምክንያት ተብሎ በሶስተኛነት የሚገለፀው የሰዎችን ትኩረት ከመሳብ ጋር የተያያዘ ነው። የሌሎችን ትኩረት ለመሳብ የሚደረግ የአለባበስ ሁኔታ ከመዋቢያ ቁሶች ጋር የተያያዘ ነው። ልብስን በተለያዩ ማስዋቢያዎች በማድረግ መልበስ በዚህ የመልበሻ ምክንያት ስር የሚካተት ነው። ይህም ልብሶችን የማስጌጥ ባህል ጥንታዊ ታሪክ ያለው ነው።

> ... Fully or scantily people cover their bodeis, almost every where they have same form of adornment. Among the adornments worn by many primitive peoples limited technological resources are seeds, teeth bones shells and leaves through which holes can be drilled for stringing on fiber strands (the encyclopedia Americana 1983, 102)

በየትም ቦታ ሰዎች በሙሉም ሆነ በከፊል አካላቸውን የሚሸፍኑባቸው ቁሶች በሁሉም ቦታ በአብዛኛው ተመሳሳይነት አላቸው። ጥንታዊ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው የነዚህ የመዋቢያ ቁሶች ምንጮች መካከልም የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ውጤት ሳይሆኑ በባህላዊ ጥበብ (የዛፍ ፍሬዎች)፣ጥርሶች፣አጥንቶች፣የእንስሳት ጠንካራ የቆዳ ሽፋኖች እና ቅጠላቅጠሎች ተበስተውና ተያይዘው የሚዘጋጁ ናቸው።

በአካባቢያቸው የሚያገኟቸውን የተፈጥሮ ሃብቶች በመጠቀም ለአልባሳቱ ተጨማሪ ውበትን የማላበሱ ባህል የቀደመ ታሪክ እንዳለው ከቀረበው ሃሳብ እንረዳለን። ይህም የማስጌጥ ባህል/ልምድ አሁን ባለንበት ዘመንም ከተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር ተደማምሮ አገልግሎት ላይ እየዋለ ይገኛል።

የልብስ መለበሻ ምክንያት በመሆን በአራተኛነት የሚነሳው ከሰዎች የኢኮኖሚ/የኑሮ ደረጃ/ ጋር የተያያዘ ነው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው አልባሳት የማግባባት አቅማቸው ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የአንድን ሰው የኑሮ ደረጃ እና ማህበራዊ ስፍራ በአልባሳት አማካይነት መረዳት ይቻላል። “An important function of clothing is that of defining a person’s status and position in his society” (The Encyclopedia Americana 1983: 102).በጣም ጠቃሚው የልብስ አገልግሎት በማህበረሰቡ ውስጥ የአንድን ግለሰብ ማህበራዊ ደረጃ/እርከን ማሳየቱ ነው።

2.2.1.2 ሃገረሰባዊ ጌጣጌጦች

ሃገረሰባዊ ጌጣጌጦች ሰዎች እንዲያስውቧቸው የሚያበጇቸውና በባህላዊ መንገድ ተሰርተው የሚጠቀሙባቸው የጥበብ ውጤቶች ናቸው። ይህም ጥበብ ቀደም ያለ ታሪክ ያለው የጥበብ አይነት መሆኑን Evans እንዲህ በማለት አቅርበውታል።

> Jewelry is one of the oldest of the decorative arts. It answers to the deep human love of intrinsically beautiful materials, to the deep human wish for bodily beautification and to the superstitious need for reinforcing human powers by things that seem to a savage more lasting and more mysterious than man. (1970, 39)

ጌጣጌጥ ከጥንት/ከቆዩ የመዋቢያ ጥበቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህም ጥበብ የሰው ልጅ ለውብ ቁሶች ያለውን ጥልቅ ፍቅር፣አካልን ለማቆንጀት ያለውን ጥልቅ ምኞትና ከሰው የበለጠ ብዙ ለቆዩና ምስጢራዊነት ያላቸውን ነገሮች የሰው ልጅ ሀይልን ከማጠናከር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚገልጽባቸው ናቸው፡፡

ጌጣጌጦች ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ጥንታዊ የጥበብ አካላት ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ለውበትና ነገሮች ያለውን ፍላጎት ለመግለፅ በተለያየ መንገድ የሚጠቀምባቸው መረጃው ያመለክታል፡፡

ጌጣጌጦች እንደየማህበረሰቡ ባህል የተለያየ ቅርፅና ተፈጥሮ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የተፈጥሮ መዋቢያዎች እንደፍሬ፣ አበባ የመሳሰሉት በአንድ አካባቢ ጌጣጌጥ ሲሆኑ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ የተለያየ የማዕድን አይነቶች ለጌጣጌጥነት ይውላሉ፡፡ ባጠቃላይ ግን አንድ የሚያደርጋቸው ጉዳይ ለጌጣጌጥነት ለመዋቢያነት የሚያገለግሉ መሆናቸው ነው፡፡ “Decorative objects made for the adornment of the body usually but not always of materials such as gold and precious stones that have a highly intrinsic value.” (The New Encyclopedia Britannica 1993፡ 345) (ለሰውነት ማስዋቢያዎች መስሪያነት የሚያገለግሉ ቁሶች ሁልጊዜም ባይሆን በአብዛኛው ወርቅና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የከበሩ ድንጋዮች ናቸው፡፡)

ጌጣጌጦች እንደአልባሳት ሁሉ የሚጠቀምባቸውን ግለሰብ እንዲሁም ማህበረሰብ ማንነትና የኑሮ ደረጃ ያመለክታሉ፡፡ በተለይ ከዘመናዊው ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ ከተለያዩ ማዕድናት የሚሰሩ ውድ ጌጦችን መልበስ የሚችሉት የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደሆኑ ጥናቶቹ ያመለክታሉ፡፡ በሮማ ዘመን በልዑላን ብቻ ይደረጉ የነበሩ ጌጦች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ባሉ የማህበረሰብ ክፍሎች መለበስ ጀምረው ነበር፡፡ (The New Encyclopedia Britannica 1993፡ 545) ለዚህም የሚጠቀሰው ምክንያት የ19ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ መስፋፋት ነው፡፡ በፊት ወርቅ ብቻ የነበሩ ጌጦች በወርቅ መሰል ቅብ ጌጣጌጥ መስሪያዎች መተካታቸው አብዛኛውን ማህበረሰብ እንዲያሳትፉ አድርጓቸዋል፡፡

ጌጣጌጦችን ከሚገኙባቸው መንገዶች በመነሳት ለሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ እነርሱም ባህላዊና የፈጠራ የሚባሉት ናቸው፡፡ አንደኛው የተፈጥሮውን ቅርፅና ቁስ መሰረት በማድረግ ያንኑ የመቅዳት ጥበብን የሚመለከተው ነው፡፡ በዚህ መንገድ የሚገኙ ጌጦችም ባህላዊ መንገድን የተከተሉ ናቸው፡፡

የግለሰብን የፈጠራ ጥበብ መሠረት አድርገው የሚሰሩት የጌጣጌጥ አይነቶች ደግሞ “የፈጠራ” ይባላሉ። ባለሙያው ወይም ማህበረሰቡ ቀድሞ ከነበረው ጌጥ በተለየ የተለያዩ የፈጠራ ጥበቦችን ተጠቅሞ የሚፈጥራቸው ናቸው። እነዚህም ከባህላዊነታቸው ይልቅ ዘመናዊነታቸው ያመዝናል።

2.2.2 አልባሳትና ሃገረሰባዊ ማንነት

አልባሳት ከሚለሱባቸው ምክንያቶች አንዱ ማንነትን ለማመልከት መሆኑ ቀደም ሲል ተወስቷል። እንደጌጣጌጦቹ አልባሳቱም ሁለት ገጽታዎች አሏቸው። አንደኛው አንድ ማህበረሰብ ባህሉንና ማንነቱን ለመጠበቅ ሲል በሚያደርገው ነገር እራሱን የሚገልፅበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ያ ግለሰብ ወይም የማህበረሰብ ክፍል በሚለብሰው ልብስ ሌላው አካል እሱን የሚረዳበት ሁኔታ ነው።

Mathisen “Folklore and Cultural Identity” በሚለው መጣጥፉ ማንነት (identity) በሁለት አይነት መንገድ ሊታይ እንደሚችል ይገልፃል። “The concept of identity has two main connotations. From one point of view, it has to do with the feeling that something is and remains the same; the feeling of continuity … having an identity also means being different from others” (በፈቃደ 2003፣ 355 ውስጥ)

እንደ Mathisen ገለፃ የመጀመሪያው የማንነት ፅንሰ ሃሳብ የነገሮች በተመሳሳይ መልኩ መቀጠል ወይም የቀጣይነት ስሜት ነው። ሌላው ደግሞ ከሌሎች ተለይቶ መታየት ነው። ማንነት በግለሰብ አልያም በማህበረሰብ ደረጃ ሊገለፅ ይችላል። በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች በሚጋሯቸው የጋራ ጉዳዮች መኖር ምክንያት ሃገረሰባዊ ማንነት ይፈጠራል። ይኸውም ከሌላው አካል እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋቸዋል። (Johnson in Dundes 1965፡43) የአንድ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ልብስ ነው። ልብሶችም የአንድን ሰው ሴትም ሆነ ወንድ ሀገራዊ፣ ጎሣዊና ክልላዊ ከየት መጣ ሊነግሩን ይችላሉ።

3. የጥናት አካባቢው ማህበረ ባህላዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የኮኮሳ እና የገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች ማህበረ ባህላዊ ዳራ ይቀርባል። ሁለቱ ወረዳዎችም በምዕራብ አርሲ ዞን የሚገኙ ናቸው።

3.1 የጥናት አካባቢዎቹ ስም አመጣጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጡትን የገደብ ሀሳሳና የኮኮሳ ወረዳዎችን የስም አመጣጥ በተመለከተ የተለያዩ ምክንያቶች ይነገራሉ።ሀሳሳ የገደብ ሀሳሳ ወረዳ ከተማ ነች። ስሟን ያገኘችባቸው እየተባሉ የሚነገሩ ምክንያቶችም ሶስት ናቸው። የመጀመሪያው በጥንት ጊዜ በአካባቢው የሚኖር ሀሳሳ የሚባል ታዋቂ ሰው ነበር። ከተማዋም ስትቆረቆር ይህንን ስያሜ ተሰጣት የሚል ነው። ሼክ ከድር ሀያቶ እንደነገሩኝ "Hasaasa wanna jedhaniif hasaasa afaan tokkoon ammo warri abbaan lafa kanaa maqaan isaa hasaasa jedhan." (ሃሣሣ ያሉበት ምክንያት ሃሳሳ በአንድ በኩል የዚህ አካባቢ ባላባት ስም ሃሳሳ ነበር።) (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 29፣2000)

ሁለተኛው ምክንያት አካባቢው በፊት እንዲህ እንደዛሬው ቤቶች ሳይበዙ በርካታ የመቃ ዛፍ የበዛበት ነበር። አካባቢው ነፋሻማ በመሆኑ በተለይ ከሰዓት ወደ 10፡00 በንፋሱ ምክንያት የመቃው ዛፍ የሚያሰማው ድምፅ የሹክሹክታ ስለሆነ በዚያ ስሙን አገኘ ይላሉ። "ሀሳሳ" ማለት ሹክሹክታ ማለት ነው።ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ ፣ሚያዚያ 6፣2000)

ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ በአካባቢው ሀሳሳ በመባል ከሚታወቀው ወንዝ ጋር የተያያዘ ነው። ወንዙ በተለይም ወደምንጩ አካባቢ በጣም ሃይለኛ ነው። ከታች ተነስቶ ወደ ላይ ወጥቶ ሲመለስ የሚያሰማው ድምፅ ሀሳሳ የሚል ስም እንዲኖረው እንዳደረገውና አካባቢውም በዚህ መጠራት እንደጀመረ ይነገራል።ሀጂ ሞሀመድ ጃርሶ (ቃለመጠይቅ መጋቢት 29፣2000)

ፎቶ 1 ሀሳሳ ስሟን አገኘች የሚባልበት ወንዝ

ሁለተኛው የዚህ ጥናት ወረዳ ኮኮሳ ነው። ኮኮሳ ስያሜውን እንዴት አገኘ? ለሚለው ጥያቄ የሃገር ሽማግሌዎች የሚሰጧቸው መልሶች አሉ። አቶ ኢምሹ ኬቄ በአካባቢው ኮኮሳ የሚባልና በትልቅነቱ የሚታወቅ ጋራ ስለነበር በዚያ ተሰየመ ሲሉ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 5፣2000) አቶ ከዲሮ ገነሞ ደግሞ አካባቢውን ያስተዳድሩ የነበሩ የመንግስት ባለስልጣናት በኮኮሳ ጠሯት ይላሉ። (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 5፣2000)

3.2 ምጣኔ ሀብት

በምዕራብ አርሲ ዞን ከሚገኙት ወረዳዎች ውስጥ ገደብ ሀሳሳ አንዷ ነች። ወረዳዋ በአሁኑ ጊዜ በግብርና የሚተዳደር ህዝብ እንደሚኖርባት ቀጥሎ የቀረበው ፅሑፍ ያመለክታል። "Diingdem guddaan aanaa Gadab Hasaasaa misooma qonnaati oomisha misooma qonnaa aanaa kanaa keessaa gurguddoon qamadii yoo ta'u ..." /ለወረዳው የሚሊኒየም አከባበር የተዘጋጀ በራሪ ወረቀት/

(የገደብ ሀሳሳ ኢኮኖሚ ትልቁ የእርሻ ልማት ነው። ግብርና ነው። ከግብርናው ምርት ትልቁን ቦታ የሚይዘው ስንዴ ነው።)

እንግዲህ ከላይ ከቀረበው ሃሳብ የምንመለከተው በገደብ ሀሳሳ የህዝብ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በግብርና ላይ መሆኑንና ከምርቶቹም ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው ስንዴ መሆኑን ነው።

የኮኮሳ ወረዳ ህዝብ እንዲሁ በአሁኑ ወቅት መተዳደሪያው ግብርና ነው። አቶ ታምራት ገመዳ የኮኮሳን ህዝብ መተዳደሪያ ከጥንት ወደ አሁን ያለትን ደረጃ ሲገልፁ በፊት ህዝቡ በከብት ማርባት ይተዳደር እንደነበር ይላሉ። በአሁኑ ወቅት ግን ከብት ማርባትና የእንሰት እርሻ ጎን ለጎን ይካሄዳሉ ። (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

የአቶ ታምራት ገመዳ መረጃ እንደሚያመለክተው በቀድሞ በሁለቱም የግብርና ዘርፎች በብዛት ህዝቡ ተጠቃሚ ነበር። ይህ ግን አሁን እንደቀድሞ አይደለም። የእንሰት ምርትም ሆነ የከብት እርዳታ የአካባቢው መተዳደሪያ ናቸው።

3.3 ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ሃብቶች

አቶ ታምራት ተካልኝ እንደነገሩኝ በዞኑ በሚገኙ ወረዳዎች የተለያዩ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሃብቶች ይገኛሉ። ደን፣ አእዋፍና አራዊት፣ ወንዞች፣ ሃይቆች ወዘተ. የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ ዞን ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ደኖች አሉ። ከነዚህም የተፈጥሮ ደኖች ሙኔሳ የተባለው

በሻሸመኔ የሚገኝ ሲሆን ሀራና በኮኮሳ የሚገኝ ነው። እንዲሁም በአዳባ-ዶዶላ የሚገኘውን ሰው ሰራሽ ደን ብዙ ገበሬዎች ተደራጅተው እየተንከባከቡት ይገኛሉ። (ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 25፣2000)

ለዞኑ ኢኮኖሚ ድርሻ ካላቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሃብቶች ውስጥ ሃይቆች፣ ወንዞችና ፖርኮች ይጠቀሳሉ። የቱሪዝም መስህብ የሆኑት የስምጥ ሸለቆ ሃይቆች የሚገኙት በዚሁ ዞን ነው። አቢያታ፣ ሻላና ላንጋኖ በዚሁ ዞን በአርሲ ነጌሌ ወረዳ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ሻላና አቢያታ ብሔራዊ ፖርኮች፣ የባሌ ተራራ ብሔራዊ ፖርክ ከብርቅዬ አራዊቶች አዕዋፋታቸው ጋር ሃገራዊና የውጭ ሃገር ጎብኚዎችን በማስተናገድ የሚታወቁ የዚህ ዞን ሃብቶች ናቸው። የሰንቀሌ የአራዊት ማቆያ፣ የሌዲስ ፏፏቴ፣ የሄና ፏፏቴ (ቂልጠረኤ) የዞኑ የቱሪዝም መስህብ ቦታዎች ናቸው። ወደ 35 የሚሆኑ ወንዞችም በዚህ ዞን ይገኛሉ።

3.4 ቋንቋ

በምዕራብ አርሲ ዞን ከሚኖሩ ህዝቦች በገጠር አካባቢዎች አብዛኛውን ቁጥር የሚይዘው ኦሮምኛ ተናጋሪ ነው። ቋንቋው የአብዛኛው ህዝብ የዕለት ተዕለት መግባቢያ ከመሆን አልፎ የዞኑ የስራ ቋንቋ ነው። በተለያዩ መስሪያ ቤቶች በስራ ቋንቋነት ፣ በትምህርት ቤቶች ደግሞ እንደ አንድ ትምህርት እንዲሁም የሁሉም የትምህርት አይነቶች ትምህርት መስጫ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል።

በዞኑ ከኦሮምኛ በመቀጠል የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ የማህበረሰብ ክፍሎች እንደመኖራቸው መጠን ሌሎች ቋንቋዎችም ይነገራሉ። ይህንኑ በማስመልከት ከዞኑ እቅድና ፕላን ቢሮ የተገኘው የፅሑፍ መረጃ የተወሰደው ሀሳብ እንደሚከተለው ቀርቧል። “Oromifa is the most common and official language in the zone and followed by Amharic, Wolayta, Gurage, Kambata, and Hadiya languages which are in West Arsi zone.”(2000፣ 6-7)

(ኦሮምኛ በብዛት የሚነገርና የዞኑ የስራ ቋንቋ የሆነ ነው። ይህም ቋንቋ በአማርኛ፣ ወላይትኛ፣ ጉራግኛ ከንባታና ሃድያ ቋንቋዎች የሚከተል ሲሆን እነዚህም በዞኑ የሚነገሩ ቋንቋዎች ናቸው።)

3.5 እምነት/ሃይማኖት

በዞኑ የሚኖረው አብዛኛው ህዝብ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነው። ይህ በዞኑ አሁን ያለውን ሁኔታ የሚያመለክት ሲሆን በተለይ የአርሲን ህዝብ የሃይማኖት/እምነት ሁኔታ በሚመለከት የተለያዩ ጥናቶች የተለያዩ መረጃዎችን ያቀርባሉ።

የአርሲ ህዝብ የእስልምናም ሆነ የክርስትና ሃይማኖትን ከመቀበሉ በፊት በአንድ አምላክ "ዋቃ" በሚባለው ያምን እንደነበር በኮኮሳ ህዝብ ላይ የዲግሪ ማሟያውን የሰራው ማሞን ጠቅሳ ሂሩት እንዲህ አቅርባዋለች።

> Both Christianity and Islam are not the original or indigenous religions of the Oromo. Both are the 19th century phenomena among hem before the introduction of Islam and Christianity the Oromo had their own indigenous religion. They worshipped Waqa (2001፡108)

> ክርስትናም ሆኑ እስልምና የአርሲ ህዝብ የቀድሞ ሃይማኖቶች አይደሉም። ሁለቱም ለህዝቡ የ19ኛው ክፍለዘመን ክስተቶች ናቸው። ክርስትናና እስልምና ከመታወቃቸው በፊት ኦሮሞዎች የራሳቸው ጥንታዊ ሃይማኖት ነበራቸው። እነሱም በዋቃ ያመልኩ ነበር።

ክርስትና እና እስልምና ለአርሲ ህዝብ የቅርብ ጊዜ ክስተቶች መሆናቸውን ነው። ይህንንም (ኃሮ ቢያንሣ 1985 እና Abas፣ 1982) ያረጋግጣሉ።

በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የአርሲ ህዝብ በሚኖርባቸው አካባቢዎች የእስልምና ሃይማኖት ተስፋፍቶ ይገኛል። ከዞኑ መስተዳድር ቢሮ የተገኘው ፅሑፋዊ መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኛውን ቁጥር የሚሸፍነው የዞኑ ህዝብ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ነው። በመቀጠል የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክና በየወረዳው በስፋት እየስፋፋ ያለው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት እንደየደረጃው ህዝቡ የሚከተላቸው ሃይማኖቶች ናቸው።

በመስክ ስራ ወቅት እንዳየሁትና ጠይቄም እንደተረዳሁት ከሁለቱ ወረዳዎች በተለይ በገደብ ሀሳሳ ወረዳ በከተማው በየእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በብዛት ይገኛሉ። በመቀጠል የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታዮች ሲሆኑ የኦርቶዶክስና የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች በቁጥር ዝቅተኛውን ደረጃ ይይዛሉ።ቁራ ከድር (ቃለመጠይቅ ሚያዚያ 2፣2000 ዓ.ም) ከሀሳሳ ጋር ሲነፃፀር በኮኮሳ የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮች ስብጥር የሚታይበት ነው።

3.6 ማህበራዊ አገልግሎቶችና ባህላዊ መገለጫዎች

በዚህ ክፍል በዞኑ የሚኖረው ህዝብ ማህበራዊ ጉዳዮችና ባህላዊ ጉዳዮች ላይ ዳሰሳ ይደረጋል፡፡

3.6.1 ማህበራዊ አገልግሎት

በዞኑ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን በሚመለከት የመስተዳድር መስሪያ ቤቱ "ፕሮፋይል" እንደሚያመለክተው ግምታዊ በሆነ ቀመር 60% በከተማ እና 23% በገጠር የሚሆነው ህዝብ ጥራት ያለው ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ ነው፡፡ በሁለቱ ወረዳዎች ማለትም በሀሳሳ 98% የሚሆነው በከተማና 5% በገጠር የሚኖረው ህዝብ የንፁህ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ እንደሆኑ መረጃው ያመለክታል፡፡ በኮኮሳ በቅርቡ የቧንቧ ውሃ ለማስራጨት ሙከራ ቢደረግም በነበረበት የቴክኒክ ችግር አስፈላጊውን አገልግሎት እየሰጠ አይደለም፡፡ ታምራት ተካልኝ (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 25፣2000ዓ.ም)

የመብራት ሽፋንንም በሚመለከት በዞኑ በርካታ ወረዳዎች በተለይ ከተማዎች የ24 ሰዓት የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ከሆኑት ሁለት ወረዳዎች ገደብ ሀሳሳ የ24 ሰዓት የመብራት አገልግሎት ማግኘት ከጀመረ በርካታ አመታትን አሳልፏል፡፡ የመብራት ሃይሉን የሚያገኘውም ከመልካ ዋከና የሃይል ምንጭ ነው፡፡ የኮኮሳ ወረዳ ከተማው የመብራት አገልግሎት ያገኘው በ1999 ዓ.ም ክረምት ውስጥ ሲሆን አገልግሎቱም የ24 ሰዓት ነው፡፡

የዞኑ የጤና አገልግሎት መስጫ አካላት በሶስት ደረጃዎች ይከፈላሉ፡፡ አንደኛው የዞኑ የጤና ክፍል የሚመራው፣ ሁለተኛ የወረዳ የጤና ቢሮዎች የሚመሩት እና ሶስተኛው በቀበሌ የጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ የሚመራው ነው፡፡ በአጠቃላይ በዞኑ 2 ሆስፒታሎች፣ 9 ከፍተኛ ክሊኒኮች፣ 56 ክሊኒኮች እና 84 የጤና ኬላዎች ይገኛሉ፡፡ ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትም አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

ከዞኑ አስተዳደር ቢሮ የተገኘው ጽሁፋዊ መረጃ በምዕራብ አርሲ ዞን እንደሚያመለክተው በርካታ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ ከዞኑ አስተዳደር ቢሮ የተገኘው የፅሑፍ መረጃ እንደሚያመለክተው 27 መዋዕለ ህፃናት፣ 514 የመጀመሪያ ደረጃ (1-8) 16 ሁለተኛ ደረጃ ሳይክል (9-10)፣ 6 ፕሪፓራቶሪ፣ 2 የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች እና 3 ኮሌጆች ይገኛሉ፡፡ የትምህርት አገልግሎት በከተማው ብቻ ሳይሆን በገጠሩም የወረዳዎቹ

ክፍሎች እየተስፋፉ እንደሆነም አቶ ታምራት ተካልኝ (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 25፣2000ዓ.ም) ገልፀውልኛል፡፡

3.6.2 ባህላዊ ጉዳዮች

አንድ ማህበረሰብ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት የራሱ የሆነ ባህላዊ እሴት አለው፡፡ ይኸውም ባህላዊ ጉዳይ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ በመባል ለሁለት ይከፈላል፡፡

የአርሲ ኦሮሞዎች የራሳቸው የሆነ የቁሳዊም ሆነ የመንፈሳዊ ባህል መገለጫ አላቸው፡፡ የዚህ ክፍል ትኩረት በነዚህ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ትንታኔ መስጠት ሳይሆን ማህበረሰቡን በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ ድርሻ አላቸው የሚባሉና ከአልባሳቱና ጌጣጌጡ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ባህላዊ ጉዳዮችን ለመጥቀስ ነው፡፡

ሀ. ባህላዊ ጋብቻ (Cidha/gaayilaa)

ጋብቻ በህይወት ከሚያጋጥሙ ተፈጥሮኣዊ ክስተቶች ውስጥ አንዱ ነው፤ ውልደት፣ ጋብቻና ሞት ተፈጥሮኣዊ የሽግግር ክስተቶች ናቸው፡፡ (ዳንኤል 2001፣ 67) በአርሲ ህዝብ ዘንድ የተለያዩ የጋብቻ አይነቶች አሉ፡፡ እነዚህ የጋብቻ አይነቶች በብዛት የሚሰራባቸው እና አልፎ አልፎ የሚታዩ በመጥፋት ላይ ያሉም ይገኙባቸዋል፡፡ እነዚህን የጋብቻ አይነቶች አንድ በአንድ እንመልከት፡፡

ገበራ/ከደታ/ጥሎሽ/ልመና (Gabbara (kadhata) - የሚባለው የጋብቻ አይነት በማህበረሰቡ ዘንድ በብዛት ተግባራዊ የሚደረግ ነው፡፡ ይህ የጋብቻ ስርዓት ቅደም ተከተላዊ ክዋኔ አለው፡፡ ቅድመ ዝግጅቱ የሚጀምረው ተጓዳኝን በመምረጥ ይሆናል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ሃለንግቻ(halangichaa) የተባለ የሁለቱንም ቤተሰብ ሁኔታ ያውቃል ተብሎ የሚታሰብ ሰው ነው፡፡ሀለንግቻ በቀጥታ ትርጉሙ አለንጋ እንደማለት ሲሆን በዚህ አገባቡ ግን አዋቂ እንደማለት ነው፡፡ የሃለንግቻው ጉዳይ የሚያስተካክለው የወንዱ አባት ነው፡፡ ከዚያም ሽማግሌዎች ይላካሉ፤ ይህም ወደ የዕጣ ፈንታ ማያ ዝግጅት ያመራል፡፡ ይህ የዕጣ ፈንታ/milki/ ጉዳይ ለሰርጉ ቀን ብቻ ሳይሆን ለተጓዳኞቹ የወደፊት ህይወት በሚል የሚታይ ነው፡፡ ለዚህም የሚመረጡ ቀናት ሃሙስ፣ እሁድና አርብ ናቸው፡፡ (ሀገሬ፣ 2000) እነዚህ በማህበረሰቡ ዘንድ የገድ ቀናት የሚባሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ የሚደረገው ዝግጅት የቀለበት ስነስርዓት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ላይ ወንዱ ለሴቷ ቁቤ የተባለች ቀለበት በአንገቷ ላይ በክር/በድሪ ያጠልቅላታል፤ ያም መታጨቷን ሲያመለክት ሌላ ሰው ለጋብቻ አይጠይቃትም፡፡

ከቀለበት ስነስርዓቱ በኋላ የግርዘት ስርዓት ይከናወናል። ቱስሉ ሲድን የጋብቻ ቀን ተቀጥሮ የጋብቻው ስርዓት ይከናወናል።

ወልገራ/ልውውጥ(walgera) - ይህ የጋብቻ አይነት አንዲትን ሴት ልጅ ለጋብቻ የጠየቀ ወንድ ለተጠያቂዋ ወንድም እህቱን የመስጠትን ግዴታ የሚጠይቅ ነው፡ ይህ የጋብቻ አይነት ገደብ ሀሳሳ በተባለው አካባቢ እንደተጀመረ ይነገራል። "... obboo Daatuu saqaqoo ... Gadabima ka'ee waabee gama ce'ee intala sii kenna atis naa kenni jedhe faantu (hinjirre) baase" (2000: 20) (ከገደብ ተነስቶ ወደ ዋቤ ከተሻገረ በኋላ ሴት ልጅ እስጥሃለሁ አንተም ስጠኝ ብሎ የሌለ ባህል አመጣ።)

ይህ ሰው ዳቱ ሰቀቆ የሚባል ሲሆን ወደዋቤ ሲሄድ አንዱን አግኝቶት ልጅህን ስጠኝ እኔም እሰጥሃለሁ እንዳለው ተገልጿል። ይህ ተግባር ከመቶ አመታት በፊት የተከናወነ ቢሆንም በማህበረሰቡ ዘንድ ጋብቻው አሁንም እየተተገበረ ይገኛል።

በዚህ የጋብቻ አይነት አንዱ ወንድ ሴቷን ከወደደና ከጠየቀ እህቱን ወይም የቅርብ ዘመዱን (የአጎቱን) ሴት ልጅ በልዋጭነት መስጠት ይኖርበታል። ያ ማለት እሱ በፍላጎቱ ቢያገባም ሌሎቹ ያለፍላጎት ለጋብቻው ይታጫሉ ማለት ነው።በሌላ በኩል ከእነዚህ ከተጋቡት ውስጥ በአንዳቸው ቅራኔ ቢፈጠር ሌሎቹም ሰላም ሊደፈርስ ይችላል። በእድሜ ሲገፉ ያለመፈላለግ፣ በእድሜ ትልቅ ልዩነት መኖር ይህንን የጋብቻ አይነት በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተና ጤናማ እንዳይሆን ሊያደርጉት ይችላሉ።

ጠለፋ(Butta)- ወንዱ ሴቷን ወደ ልመናውን በመፍራት፣ ለምኖ ቤተሰቦቿ ከከለከሉት፣ አስፈላጊውን የጥሎሽ ዋጋ ለመክፈል አቅሙ ሳይኖረው ሲቀር መውጫ መግቢያዋን አጥንቶ ከጓደኛው ጋር በመሆን የሚፈፅመው የመውሰድ ተግባር ነው። እንደዚህ የተጀመረው የጋብቻ ሁኔታ በመጨረሻ በእርቅ መፈፀሙ የማይቀር ነው። ነገር ግን ብዙ ልፋትና ድካምን ይጠይቃል።" Ifaajee guddaa fi baasii guddaan kan argaman ta'ee garu intalti sun bifa raawwii fuudhaa fi heeruma gabbaraan ykn walgaraatiin gaa'illi raawwata." (የዞኑን ባህል የሚያመለክት ጽሁፋዊ መረጃ)

"ከብዙ ልፋትና ድካም በኋላ የሚጠናቀቅ ሲሆን ነገር ግን ልጅቷ ጋብቻውን የምትፈፅመው በገበራ (ጥሎሽ ወይም ወልገራ/ልውውጥ) ይሆናል።"

መተማመን/ምኞታዊ ጋብቻ (Hawwatani fuudhuu (hawwataa) :- ይህ የጋብቻ አይነት በሁለቱ ተጓዳኞች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ሴቷና ወንዱ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይተዋወቃሉ፤ ይዋደዳሉ፤ እርስ በርሳቸው አልያም በጓደኞቻቸው በኩል ከተመካከሩ በኋላ ወደ

ወንዱ ቤተሰብ አብረው ይሄዳሉ። ወንዱም ቤተሰቡ ቤት ወስዶ ክብት ካረደላት በኋላ ቤተሰቦቹ "ልጃችሁ እቤታችን ገብታለችና ልመናችንን አትቃወሙ" በማለት ሽማግሌ ወደ ልጅቷ ይልካሉ። ሽማግሌዎቹም የሴቷ ቤተሰብ ጋ ሄደው ቤተሰቧ እሺ ሲል በሌላ ቀን ጠጅ ተጠምቆ፣ ልጅቷን ልብስ አልብሰው የቅጣት ብርም ይዘው መጥተው ስርዓቱ ይጠናቀቃል። ለዚህ የጋብቻ አይነት ምክንያት ሴቷና ወንዱ ትውውቅ አጋጣሚ የሚሆኑት የገበያ ስፍራ፣ የባህላዊ ጭፈራና ሰርግ እንዲሁም የግርዛት በዓላት ናቸው።

በአርሲ ማህበረሰብ ዘንድ የታወቀው ሌላው የጋብቻ አይነት Dhaala (ውርስ) የሚባለው ነው። ባል የሞተባት ሴት በሞተው ባሏ ምትክ ወንድሙን እንድታገባ የሚደረግበት ነው። ባሏ የሞተባትን ሴት የሚወርሰው የሟች ወንድም ነው፤ ሟች ወንድም ከሌለው እንኳን የአጎት ልጅ እንዲያገባት ይደረጋል።

ማህበረሰቡ ለምን እንዲወርስ እንደሚደረግ የሚያቀርባቸው ምክንያቶች አሉ። አንደኛው ሴቷ ብቻዋን ሆና የባል ንብረት እንዳይዘረፍ ልጆቹም እንዳይጎሳቆሉ የሚል ነው። ሌላው ሴቷ ሌላ ባል ከሌላ ጎሳ ካገባች አካባቢውን ጥላ ልትሄድ ትችላለች። ይህ ደግሞ ልጆቹ እንዲጎሳቆሉና ጎሳቸውንም እንዲረሱ ያደርጋቸዋል የሚል ፍራቻ በመኖሩ ነው። ሼክ ከድር ሀያቶ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 29፣ 2000)

የሟች ወንድም ሴቷን ሲወርስ ልጆች ቢወልድ እንኳን ልጆቹ የሚጠሩት በሱ ስም ሳይሆን በሟች ስም ነው። ይህም ሟች እንዳይረሳ በሚል ነው።

ተለያየን/መግባት (Aaddabaana/Aseennaa) ፦ ይህም የጋብቻ አይነት ከወንዱ ይልቅ በሴቷ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው።

> Addabaanni sirna fuudhaa heerumaa kan intalti yoo gurbaa dhiiraa jaalattee siinqee fi sardoo qabatte warra mucaa dhufte balbala geettee "addabaana shifaa, xabboo mana citaa warra afaan golaa na jalaa goraa" jechuun gola haadha mucaa seentee teetti. (የዞኑን ባህል የሚያመለክት የጽሁፍ መረጃ)

አደባና የጋብቻ ስርዓት ሴቷ ወንዱን ወዳ ሲንቄና እርጥብ ሳር ይዛ ወደ ወንዱ ቤተሰብ ቤት በመሄድ በር ላይ ቆማ "አደባና(እንለያያለን) የሳር ቤት ቤቱን ከፈቱልኝ" በማለት ወደ ቤት ገብታ ትቀመጣለች።

እቤት ከገባች በኋላ ከየት ጎሳ እንደመጣች፣ ቅርብ ዝምድና እንደሌላትና የቤተሰቧ የኑሮ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተጠይቃና ተጣርቶ ልጁ እንዲያገባት ይደረጋል። በዚህ የጋብቻ ስርዓት ከቤተሰቡ ካልመጣ ወንዱ እምቢ የማለት አማራጭ አይሰጠውም። ቤተሰቦቹ ፈቃደኛ ከሆኑ ሽማግሌ ይላክና የሴቷ ቤተሰብ ተጠይቆ የጋብቻው ስርዓት ይከናወናል። በተለያዩ ምክንያቶች በጋብቻው የወንድ ቤተሰብ ካልተስማማ በማግስቱ ቅቤ ቀብተው ወደ ቤተሰቦቿ ይመልሷታል። (ዳንኤል 2001፣ 85)

ሚልቤቶ፣ሂርጰ፣ሶሮረተ፣ሜምቤቶ (Milbettoo/Hirpha/sororata/membeeto) የሚባለው ስድስተኛው የጋብቻ አይነት ነው። በሴቷ ሞት ምክንያት ለወንዱ የሴቷን እህት አልያም የአጎቷ ልጅ ለባሏ የማበርከት/የመስጠትን ሁኔታ የሚመለከት ነው። የዚህ የጋብቻ አፈፃፀም አይነተኛ ምክንያቶች ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ዝምድናን ለማጠናከር ሲባል ነው። በማህበረሰቡ ዘንድ "Intala duute soddoomni hinjiru" የሚባል አባባል አለ። ይህም ሴት ከሞተች ዝምድና የጋብቻ የለም ማለት ነው።

ይህ ፍራቻ/እምነት በማህበረሰቡ ዘንድ ስላለ ዝምድናውን ለማጠናከር ሲባል የሴት ቤተሰቦች ልጃቸው በሞተችበት ወቅት እህቷን፣ እህት ከሌላትም የአጎቷን ሴት ልጅ ለወንዱ ከሃዘንህ አገግም ብለው ይሰጡታል። በለቅሶ ጊዜ የባል ወገኖች "ሴቷ ሞታለችና ዝምድናችንን ጠግኑልን" የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ። ቤተሰቦቿም እህቷን እህት ከሌላትና ዝምድናውን በጣም የሚፈልጉት ከሆነ አጎቷን ሴት ልጅ ይሰጡታል።

እህቷን ወይም የአጎቷን ልጅ መተካቱ የሟችን ልጅ እንደራስ ልጅ አድርጎ ለማሳደግ አክስት የበለጠ የለም በሚል እምነት ምክንያት የሚከወን ነው።

የወዲያው ውሳኔ (Biidha) የአጋጣሚ ጋብቻ፡- ይህ ደግሞ በወንዱና በሴቷ ቤተሰቦች መካከል የጋብቻ ቀን ተቀጥሮ ወንዱ ሴቷን ለመውሰድ ሲሄድ በተለያዩ ምክንያቶች ሳያገኛት ቢቀር "ሰርገኛ ባዶ እጁን አይገባም" ስለሚባል ያገኛትን ሴት ይዞ ወደቤቱ የሚመለስበት ነው። ያገኛት ሴት ሲባል በመንገድ ስትሄድ ጠልፎ አልይም ምኗንም ሳያውቅ አይደለም። ለትዳር ያሰባትን ሴት አለማግኘቱን ሲያረጋግጥ በደረሰበት አካባቢ በአካባቢው ሰዎች ሴቷ የስጋ ዝምድና እንደሌላት ከተረጋገጠ በኋላ ነው። ይህም የጋብቻ አይነት አብዛኛውን ጊዜ አይስተዋልም።

ጉማን ፊጠቹ (Gumaan Fixachuun fuudhuu)፡- ይህ የጋብቻ ስርዓት በቀድሞ ጊዜ አልፎ አልፎ የሚከወን በአሁኑ ወቅት ግን በአብዛኛው እየጠፋ ያለ ነው። የመፈጠሪያ አጋጣሚውም በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ከተገዳደሉ እና የሞተውም ሰው የታወቀ/የተወደደ

ከሆነ ሴት ልጅ የምትሰጥበት ነው። የሞተው ሰው የታወቀና የተወደደ ከሆነ በካሳ ቂሙ አይሽርም ተብሎ ይታመናል። ቂሙን ለማስቀረት ሲባልም ያንን የመሰለ ጀግና የምትወልድላችሁ ሴት እነሆ በማለት የሟች ቤተሰብ ለጋብቻ ይሰጡታል። ይህም አንድ የእርቅ ማብረጃ መንገድ ይሆናል።

ራስ መቀባት (Mataa diba) ፡- ይህ የጋብቻ አይነት በሁለቱ ቤተሰቦች ስምምነት የሚፈፀም የጋብቻ አይነት ነው። የዚህ የጋብቻ መፈጠሪያ አጋጣሚም ሁለቱ ቤተሰቦች ቅርርብ ካላቸውና እንደባህሉ አስፈላጊውን የጥሎሽ ብርም ሆነ ከብት የማሟላት አቅሙ ከሌላቸው በስምምነት የሁለቱን ተጓዳኞች የጋብቻ ስርዓት የሚፈፅሙበት ነው። ብዙ ድግስና የጥሎሽ ወጪ የለውም ሴቷ ቅቤ እራሷን ተቀብታ ለልጁ ትሰጣለች።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት በዞኑ በአርሲ ኦሮሞዎች ዘንድ የሚስተዋሉ የጋብቻ አይነቶች ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ስርዓታዊ ተብለው የሚጠሩት ጥሎሽና ገበራ ሲሆኑ የራሳቸው ስርዓት አላቸው። ሌሎቹ የጋብቻ አይነቶች ግን ከ(Mataa dibachuu) በቀር የሚጠናቀቁት ከሁለቱ በአንዳቸው የጋብቻ ስርዓቶች ነው። በእነዚህ የጋብቻ ስርዓቶች ላይ የሚገኙ ሴቶች እንደእድሜያቸውና በበዐሉ ላይ እንደ ሚኖራቸው ተሳትፎ የተለያዩ ጌጦችና ልብሶችን ይለብሳሉ።

ለ. ለቅሶ (Booyicha)

በሞት ምክንያት የሚከሰት የሃዘን መግለጫ ነው። ጋብቻ ባህላዊ መገለጫዎች እንዳሉት ሁሉ ለቅሶም ባህላዊ መገለጫ አለው። በአርሲ ማህበረሰብ ዘንድ የለቅሶ ስርዓት በተለያዩ መንገዶች ይከናወናል።

በአርሲ ማህበረሰብ እንደየዝምድናው ቅርበት ለሟች ያለ ፅኑ ፍቅርና ሃዘን በተለያየ መንገድ ይገለፃል። ሟች ጀግና ከሆነ በቤቱ ውስጥ ያሉ ጀግንነቱን የሚገልፁ ቁሶች በፈረስ ተጭነው ከለቀስተኛው እንዲያያቸው ይደረጋሉ። ሴቷ/የሟች ሚስት በማህበረሰቡ ዘንድ የጥንቱ የባህል ልብስ የሆነውን ከሎ/ከቆዳ የሚሰራ/ ገልብጣ ትለብሳለች። ሌሎቹም ሴቶች እንዲሁ ያደርጋሉ። ባሏ የሞተባት ሴት ከሎዋን ገልብጣ ከማዘን ሌላ እጇንና እግሯን አትታጠብም፤ ከመኝታዋ ወርዳ አመድ ካለበት ክፍል ቁርበት አንጥፋ ትተኛለች። ቅቤ አትቀባም፤ የተለያዩ ጌጦችንም አታደርግም። ይህም የሚቆየው እስከ አንድ አመት ነው። (ኢያንቱ ዱቤ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 1፣ 2000)

ሚች ልጆች ካሉት ፀጉራቸውን ይቆረጣሉ። የቅርብ ዝምድና ያላቸው የአንበሳ ወይም የነበር ቆዳ ይለብሳሉ፤ ይህንንም የሚያደርጉት የሟችን ጀግንነት ለማመልከት ነው።"Abbaan warraa yoo irraa du'ee dubartiin haga waggaattillee dhadhaallee hindibannee jagrii mormrratti maratani deeman malee harkatillee mi'a hin qaban."(ባለቤቷ የሞተባት ሴት እስከ አመት ድረስ ቅቤ አትቀባም። አንገት ላይ ጨርቅ ጠምጥመው ይሄዳሉ እንጂ እጃቸው ላይ እንኳን ምንም እቃ/ጌጥ የላቸውም)። ቦንሶሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣ 2000ዓ.ም)

ይህ መረጃ እንደሚያመለክተው ባል የሞተባት ሴት ለአመት ያህል ቅቤ ከመቀባት ከመቆጠብና ከማዘን በተጨማሪ የእጅም ሆነ የአንገት ጌጥ እንደማታደርግ ነው።

4. የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ

በዚህ ምዕራፍ በአርሲ በቅድሚያ የኮኮሳን፣ ከዚያም የገደብ ሀሳሳ ከተማ የሆነችው የሀሳሳን አልባሳትና ጌጣጌጥ እንመለከታለን፡፡

4.1 የኮኮሳ ሴቶች አልባሳት

በኮኮሳ በተለይ ሴቶች የሚለብሷቸው ልብሶች በየደረጃው የተለያዩ ናቸው፡፡ የተለያየ የአለባበስ ስርዓትና የመለበሻ አጋጣሚም አላቸው፡፡ እነዚህ አልባሳት በአብዛኛው በተለይ በቀደሙት ጊዜያት ከቆዳ የተሰሩ ነበሩ፡፡ አቶ ቦንሰሞ ሚኤሶ በማህበረሰቡ ዘንድ የቆዳ ልብስ የቀደመ ታሪክ እንዳለው ሲገልጹ፡-

> Durammoo kan beekamuu kan jalqabee ummanni waa gogaarraa hojjatamee uffata. Odoo jirbiin hin eegalamii durattii haga dhiyoo kanatti ummanni kenna horsiisa horitiin beekama.walqunnamtii ykn jaalala horii wajjiin ,horsiisa horii bal'inaan waan adeemsisuuf gara guddina gogaa horirraa kan hojjatamee kan isaan itti fayyadamaa turan. (ሚያዚያ 6፣2000ዓ.ም)

ድሮ ደግሞ የሚታወቀው የቀደመው ህዝቡ ከቆዳ የተሰራ ልብስ ይለብስ ነበር፡፡ የጥጥ ልብስ ከመጀመሩ በፊት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም ህዝባችን በከብት እርባታ ይታወቃል፡፡ ለከብቶች ቅርበትና ፍቅር ስላለው፣እርባታውንም በሰፊው የሚያካሂድ በመሆኑ በብዛት ከቆዳ በሚሰሩ ነገሮች ይጠቀም ነበር፡፡

የኮኮሳ ሴቶችም ከቆዳ የተሰሩ ልብሶችን ይለብሳሉ፡፡ እነዚህም ልብሶች ከልጆች እስከ እናቶች ባለው እርከን ውስጥ ቁጥራቸው እየጨመረ ይሄዳል፤ ከአንድ እስከ ሶስትና አራት አይነት ልብሶች ይለበሳሉ፡፡ እነዚህን ልብሶች በሶስት ከፍለን እናያቸዋለን፡፡ የመጀመሪያው የትንንሽ ሴት ልጆች፣ሁለተኛው የልጃገረዶች እና ሶስተኛው የአዋቂ ሴቶች ልብሶች ናቸው፡፡

4.1.1 የልጆች አልባሳት

በኮኮሳ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ለአቅመ አዳምና ሄዋን እስከሚደርሱ ድረስ ተመሳሳይ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ ይኸውም አንድ ብቻ ሲሆን ከቆዳ የሚሰራ ነው፡፡ ልብሱም ከሎ(kal'oo) ይባላል፡፡ ሀጂ ሞሀመድ ጃርሶ ይህንን ሁኔታ ሲገልጹ "Ijoolleen didiqqaan haga kunoo rifeensi bahu jammarutti kal'ooma uffatani deeman. Gaafa saalfatte 'saalfatte'

jedhaniin marahuu kana hin jammarti."(ልጆች ለአቅመ ሄዋን ደርሰው ፀጉር ማብቀል እስከጀመሩበት ጊዜ ድረስ ከሎ ነው የሚለብሱት። "ማፈር ጀመሩ" (Ni saalfatte) ይባላል ያንን ጊዜ መጠምጠም ይጀምራሉ።(ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት 29፣2000 ዓ.ም)

ትንንሾቹ ሴት ልጆች እቤት በሚውሉበትና እንደአቅማቸው የተለያዩ የቤት ውስጥ ተግባራትን በሚያከናውኑበት ወቅት ወይም ከብቶችን ሲያግዱ ከሎውን ይለብሳሉ። በዚህን ጊዜ ሌላ ተጨማሪ የሚለብሱት ልብስ የለም። ይህ ከሎ ከጥጃ ወይም ከትንንሽ የዱር አራዊት ቆዳ የሚዘጋጅ ነው። ለልብሱ የሚታረደው ከብትም ሆነ የዱር እንስሳ አስተራረድ የተለየ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። መደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ እና የአዘገጃጀቱን ሂደት ለከሎ የሚፈለግ ከብት ሲታረድ ከቆዳ ገፈፋ ጀምሮ እስከ መጨረሻው የመለበሻ ጊዜ ድረስ የራሱ የሆነ ስርዓት አለው። ይታረዳል፤ ከታረደ በኋላ ይለፋል፣ የሚዘጋጀውም በባለሙያዎች ነው።

ከሎ(kal'oo) በአርሲ ማህበረሰብ ዘንድ በተለያዩ የዕድሜና የኑሮ ደረጃዎች ላይ ያሉ ሴቶች ይለብሱታል። በስም አንድ ሆኖ በጠቀሜታና በመጠን የተለያየ ነው። ልጆች፤ልጃገረዶችና እናቶች የሚለብሱት ከሎ አለ። ይህንን በሚመለከት አቶ ቦንሰሞ የሚከተለውን ብለዋል።

> Kal'oon bakka lamatti qoodamti. Kal'oon ijoollee shamaran ka uffattan kal'oon da'imaa jira...kal'oon lammaffaa ammoo kal'oon handaaraa bareedamee suufamee horii bifa arawaa ykn gurraacha ykn bifa bareedaa ta'ee jira. (ቃለመጠይቅ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

ከሎ በሁለት ይከፈላል። የልጆች ከሎ ልጆች፣ የልጃገረዶች እና ህፃናት የሚለብሱት የልጆች ከሎ አለ። ሁለተኛው ደግሞ ከሎ ሀንዳራ ይባላል፤አምሮ ተሰርቶ ቀይ ወይም ጥቁር ቀለም ካለው ከብት ቆዳ ይዘጋጃል።

ከእነዚህ ልብሶች በተለይ የልጆች እና የልጃገረዶቹ አሰራራቸውና ስማቸው አንድ ይሁን እንጂ በመጠን ይለያያሉ። በተጨማሪም ለገላ መሸፈኛነት ከመዋል በቀር ሌላ ማስዋቢያ አይደረግባቸውም።በትንንሽ ልጆች የሚለበሰው ከሎ አሁን በብዛት አይስተዋልም። ልጆች ትምህርት ቤት እየገቡ ትምህርት ቤቶችም እየተስፋፉ በመሆኑ ከገበያ የሚገዙ የጨርቅ ልብሶችን መልበስ በአካባቢው የተለመደ ሆኗል።

4.1.2 የልጃገረዶች አልባሳት

በዚህ ክፍል ለአቅመሄዋን የደረሱ ያልታጩና የታጩ ልጃገረዶችን የአለባበስ ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ በልጆች የልብስ ክፍል እንደተገለጸው ለአቅመሄዋን የደረሱ ሰውነታቸውን መሸፈን ይጀምራሉ፡፡ ይህ ጊዜ ልጃገረዶች እራሳቸውን የሚጠብቁበት፣ለጋብቻ መታጫ ወቅት በመሆኑ እራሳቸውን እንዲጠብቁ ይፈለጋል፡፡ ይህንንም ከታላላቅ እህቶቻቸው፣ከእናቶቻቸውና በአቅራቢያቸው ከሚገኟቸው ሰዎች ይማሩታል፡፡ ተፈጥሮአዊ የሆነ የራሳቸው ንቃትም የራሱ ድርሻ አለው፡፡ ልጃገረዶቹ ከጸጉር አሰራር ጀምሮ እስከ ልብስ አለባበስ ድረስ የራሳቸው መለያ አላቸው፡፡ እያንዳንዱ ሁኔታና ድርጊታቸውም በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደ ባህላዊ ገጽታ አለው፡፡ በመሆኑም አንዲትን ልጃገረድ በመንገድ ላይ ያያት ሰው ተፈጥሮአዊ ከሆነው መገለጫ በተጨማሪ በነዚህ ሁኔታዎች ለይቶ ያውቃታል፡፡ በዚህን ጊዜ የሚለበሱት ልብሶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው ከጥጥ የሚሰራ ሲሆን ሁለተኛው ከቆዳ የሚሰራ ነው፡፡እነሱም ቆሎ(qoloo) እና ከሎ(kal'oo) ይባላሉ፡፡

ቆሎ (Qoloo)፡- ቆሎ በሽመና ጥበብ የሚሰራ የልጃገረዶች የጥጥ ልብስ ነው፡፡ ከላይ ወደታች የሚወርድ በሙሉ ቀሚስ ቅርጽ የሚሰራ ሲሆን ባታቸው ጋ ሲደርስ በጎንና በጎን ወደታች የሚወርድ ቅድ ይደረግለታል፡፡ ልብሱ መደቡ ነጭ ሆኖ የተለያዩ ቀለማት ሰረዝ ሰረዝ ቅርጽ ይዘው ይገኙበታል፡፡ የሰረዙ መጠንም ሰፊና ጠባብ ነው፡፡ እነዚህም ሰረዞች ከጥቁር፣ቀይና ሰማያዊ የተሰሩ ናቸው፡፡ ከፊት በኩል ከታች ያለው የልብሱ ክፍል የተለያዩ ቅርጾች ያላቸው ዲዛይኖች አሉት፡፡ በተጨማሪም ከታች ጫፉ ላይ ቀይና ሰማያዊ ባላቸው ክሮች ዘርፍ ይሰራበታል፡፡



ፎቶ 2 የልጃገረዶች ቆሎ

ይህ የልብስ አይነት ቆሎ የሚል ስም የተሰጠው በውስጡ ያሉት የተለያዩ ቀለማት ተሰባጥረው የሚገኙት በመሆኑ ነው። “qoloo wanti jedhameef bifti isii hedduun diimaa gurraacha adii walkeessa qabuu jechuu dha.” ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም) (ቆሎ የተባለበት ምክንያት አብዛኛው ቀለም ቀይ፣ ጥቁር ነጭ የተሰባጠሩበት በመሆኑ ነው።)

ይህ የልብስ አይነት እጅጌ ጉርድ ሲሆን ወደታች ሲወርድ ስንጥቅ እንዲኖር የሚደረግበትን ምክንያት የመታያ፣ ብዙ ስራ የመስሪያ ጊዜያቸው በመሆኑ እንደልብ እንዲንቀሳቀሱ፣አካላዊ ውበታቸውም እንዲታይ ስለሚያደርግ ነው። አቶ ቦንሰሞ ይህንን ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጸውታል።

Qoloon dubaraa amma ka kokkoossatti argitan kan ijollee durbaati.dubarat godhata. Hawwotaaf baayyee hin heeyyamamuu. Qoloon dubarartii igir Yoo deemtu gamaa gamanaa kan baqaffamuu qaba.ka dubaraa haga sarbaa dubartiin yoo hojiif walii gadii deeman sarbaa isaani kana agarsiisa. ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

ኮኮሳ ያያችሁት ቆሎ የልጃገረዶች ነው። ለአዋቂዎች ብዙም አይፈቀድም። የልጃገረዶቹ የሆነ ቦታ ሲሄዱ ከጎንና ከጎን ስንጥቅ አለው። የልጅገረዱ እስከ ባት ድረስ ሆኖ ለስራ ሲንቀሳቀሱ ባታቸውን ያሳያል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህ ዕድሜ አንዲት ልጃገረድ ለጋብቻ የምትታጭበት ነው። በመሆኑም ይህ ልብስ አንዱ የሴቷን ውበት አጉልቶ ማሳያ ነው ማለት ይቻላል።

ይህ የልብስ ዓይነት ከሌሎች አጎራባች ከተማዎች በግዢ የሚመጣ እንጂ የማህበረሰቡ የዕደ ጥበብ ውጤት አይደለም። ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም፤ከድሮ ገነሞ ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 5፣2000 ዓ.ም፤ ኢምሹ ኬቂ ቃለመጠይቅ ሚያዚያ 5፣2000 ዓ.ም) ልጃገረዶች የሚለብሱትን ልብስ በሚመለከት አቶ ከድሮ ገነሞ እንዲህ ይላሉ። «ልጃገረድ ቆሎ ብቻ ታደርጋለች እንጂ አታስርም፤ትልልቆቹ ሌላ ይለብሳሉ። ልጃገረድ ቆሎ ለብሳ በላዩ ላይ ከሎ ታደርጋለች። ትልልቆቹ ቦንኮ፣ቆሎ ያደርጋሉ።»(ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 5፣2000 ዓ.ም)

ከሎ(kal'oo)፦ ከቆሎ በመቀጠል በልጃገረዶች የሚለበሰው ልብስ ከሎ ይባላል። ከሎ በልጆች የልብስ ክፍል እንደተገለጸው ከትንንሽ ከብቶች፣ ከጥጃ ቆዳ የሚዘጋጅ ነው።ይህ አብዛኛውን ጊዜ ልጃገረዶቹ በቤት ውስጥና በቤታቸው አካባቢ ሲውሉ የሚለብሱት ነው። ቅርጹና ስራው ከልጆች ከሎ ጋር አንድ ነው።

ፎቶ 3 የልጃገረዶች ልብስና የጸጉር አሰራር

ከዚህ ሌላ በልጃገረዶች የሚለበስ አንድ ልብስ አለ። ይህም ቦኬ ይባላል። ከከሎ የሚለየው ለውበት ተጠንቅቀው የሚያዘጋጁት በመሆኑ ነው። ይህም ልጃገረዶቹ የሚለብሱት እንደ ፍላጎታቸውና ባህላዊ የእውቀት ደረጃቸው በተለያዩ ጌጦች አምሮ ሊሰራ ይችላል። ከሎው በካባ ቅርጽ የሚዘጋጅ ሲሆን ትከሻ ላይ በሚውለው የቆዳው ክፍል በረድፍ ቀሪሳ የሚባል ከዝሆን ጥርስ የሚሰራ ቁልፍ መሳይ ጌጥ ይሰፋበታል። ዶቃም ለከሎው ውበት በቀሪሳዎቹ መሃል መሀል እየተደረገ ቆዳው ላይ ይሰፋበታል። ይህንን የሚለብሱት የታጩ ልጃገረዶች ናቸው።ከጋብቻቸው እስከወጣትነታቸው ጊዜ ድረስ ይለብሱታል። አሁን ግን ባካባቢው አይለበስም።

በኮኮሳ በአሁኑ ወቅት ባህላዊው አለባበስ በብዛት አይታይም። በየገጠር ቀበሌው ትምህርት እየተስፋፋ በመሆኑ ልጃገረዶች ከገበያ የሚገዙ ልብሶችን ይለብሳሉ። “Shamarrii amma mana barumsatti deebitee jirti. Barumsatti deebite. Kana baqqaa dhifte.

Tokko kan mana barumsaatti hingalin hin godhatti.seerrii hin kennaaf." ነጌሶ ዲዶ (ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 2፣2000 ዓ.ም) (ልጃገረዶች አሁን ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰዋል። ይህንን/ባህሉን/ ትተዋል። አንዳንድ ትምህርት ቤት ያልገቡ ያደርጋሉ፤ ስርኣቱ ይፈቅድላቸዋል።)

ልጃገረዶቹ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ባህላዊውን ሳይሆን ዘመናዊውን ልብስ መልበስ መጀመራቸውን የቀረበው መረጃ ያመለክታል።

4.1.3. ያገቡ ሴቶች አልባሳት

ያገቡ ሴቶች ከጋብቻቸው እለት ጀምሮ የሚለብሷቸው ልብሶች ጉፍታ (guftaa) ቦኬ(boke)፣ከሎ(kal'oo)፣ከሎሀንዳራ(kal'oohandaraa)፣ቆሎ(qoloo)፣ቦንኮ(bonkoo)፣ቁጣ (qexxaa)ና ሀርሰማ (harsamaa) የሚባሉት ናቸው። እነዚህ ልብሶች ከቆሎና ጉፍታ በስተቀር ሁሉም የቆዳ ውጤቶች ናቸው።

ጉፍታ(Guftaa)፡- የአርሲ ሴቶች አለባበስ ከጸጉራቸው ይጀምራል፤ ፀጉራቸው ላይ ጉፍታ(ጥቁር ሻሽ) የሚባለውን አስረው ከላይ ነጭ ሻሽ ያስሩበታል። የነጩ ሻሽ አገልግሎት ጉፍታው እንዳይንሸራተት አጥብቆ መያዝ ነው። Guftaa/ጉፍታ/ ጥቁር ሻሽ ነው።ይህን ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ወደ ህዝቡ የገባ ነው።በመሆኑም ይህን ጉፍታ የሚያስሩት የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ሴቶች ናቸው።

ቆሎ (Qoloo)፡- አንዲት ያገባች ሴት በተለይ በቀደሙ ጊዜያት በምትለብሰው ልብስ ትታወቅ ነበር። ከምትለብሳቸው ልብሶች መካከልም አንዱ ቆሎ ነው። ቆሎ ከጥጥ የሚሰራ የሸመና ውጤት የሆነ ከላይ የሚለበስ ነው። ይህ የቆሎ አይነት የተለያዩ ቀለማት ያሉት ሲሆን እንደ ልጃገረዶቹ ወደታች የማይረዝምና ከሽንጥ በላይ የሚቀር ነው። ይህንን ልብስ አንዲት ልጃገረድ በጋብቻዋ ቀን እና ከጋብቻዋ በኋላ በቤት ውስጥም ሆነ ከቤት ውጪ የምትለብሰው ነው። በአሁኑ ጊዜ ይህ የቆሎ አይነት በሴቶቹ ሲለበስ አይታይም፤ከሱ ይልቅ በኮኮሳ የሚገኘው የቆሎ አይነት ቆሎ ፋጢሜ የሚባለው ነው። ይኸውም በልጃገረዶች ቆሎ የታችኛው(ከሽንጥ በታች) አይነት ዲዛይን የሚሰራ ነው። ይህንን የሚያደርጉ ሴቶች የአቴቴን በአል የሚደግሱና በአቴቴ በአል ላይ የሚገኙ ናቸው።



ፎቶ 4 ያገቡ ሴቶች ቆሎ አቴቴ

ቄጣ(Qeexxaa)፡- ቄጣ ከለሰለሰ ቆዳ በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጅ ከጉልበት በታች ግን በጣም ያልረዘመ የቀሚስ አይነት ነው። ይህንን ልብስ የምትለብሰው ሙሽሪት በጋብቻዋ ዕለትና በትዳር ህይወቷ ከ1-3 ልጆች እስከወለደችበት ጊዜ ድረስ ነው። አብደላ ሉገማ (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 30፣2000 ዓ.ም)

አቶ ቦንሰሞ እንደነገሩኝ ቄጣ ልብስ የራሱ የሆነ የቆዳ አመራረጥና የአዘገጃጀት ሂደት አለው።

> akka amma gurdii ammaa kanaan walfakkaataa gabaabdudha. Bareedduu dha. Kan hojjatamullee gogaa loonirraa odoo hin taane gogaa re'ee ta borofaa kanneen ni luqqisan,luqqisanii sirritti hojjatamaa waltti dachaasanii hodhan. Ogeessatu hodha. Yoo akka kanaatti hodhamuu kan afoo jiruu fi kaan garaagarummaan isaa hin mullata. Maalif bineensotsa lama ykn beelladoota lama irraa hojjatamee waan jiruuf. ... hodhaa fi kan akka hanfala fudhata. Jalatti mi'a dachaasan. (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

አሁን ጉርድ እንደሚባለው አይነት ነች፣አጭር ነች። የምትሰራው እንኳን ከከብት ቆዳ ሳይሆን ከፍየል፣ ከጎሽና ከሌሎች የዱር አራዊቶች ነው። ቆዳው ይለያል። በደንብ ታሽቶ ይፋቃል፣ይለሰልሳል። በአንድ ላይም ይሰፋል።ከዚያ የላዩ እና የውስጡ በደንብ ይለያል። ከተለያዩ አራዊቶች ቆዳ ስለሚሰራ ነው። አንዱ ሲደምቅ ሌላው ይደበዝዛል። ይንን ባለሙያ በአንድ ይሰፋዋል። ሀንፈላ ይዘጋጅለታል። ከስር ደግሞ የተለያዩ የማጌጫ ቁሶች ይደረጉበታል።

ፎቶ ቁ. 5 አሁን የለም የሚባለው ቁጣ ከፎቶግራፍ ላይ የተነሳ

ለዚህ የልብስ አይነት የሚመረጠው ቆዳ በተፈጥሮ የለሰለሰ መሆን አለበት። ምክንያቱም በስራው ወቅት ከሚጨማመርበት ማለስለሻ በተጨማሪ ለሰውነት የቀረበ በመሆኑ እንዲለሰልስ ይፈለጋል። አቶ ቦንሰሞ እንደነገሩኝ ይህ ልብስ ቁጣ የሚለውን ስም ያገኘው ሴቶቹ ለብሰውት ሲሄዱ ከታች ባሉት የጌጥ ዘርፎች የተነሳ ጣ! ጣ! የሚል ድምጽ ያሰማ ስለነበር ነው። ቁጣ በርካታ የዶቃ ጌጦች ይደረጉበታል። ከላይ ጠቦ ወደታች እየሰፋ የመሄድ በጌጦቹ ዘርፍ የተነሳም ብትን የሚል ቅርጽ የሚይዝ ነው። ይህ ልብስ መቀነት አለው። መቀነቱም ከቆዳ የሚዘጋጅ ሲሆን ተሰነጣጥቆ ለማሰር በሚመች መልኩ ይዘጋጃል። ይህም ሀንፈላ(hanfalaa) በመባል ይታወቃል።

ከሎ ሀንዳራ (Kal'oo handaaraa)፦ ይህ የልብስ አይነት ከቆዳ የሚዘጋጅ ሲሆን ከከሎ የሚለየው በቁመት ረጅም የሆነ ከትልልቅ ከብቶች ቆዳ የሚዘጋጅ በመሆኑ ነው። ከዚህም በላይ የተለያዩ ጌጦች ተሰርተውበት በበዐላት ጊዜ የሚለበስ ልብስ ነው። ለከሎ ሀንዳራ የሚዘጋጅ ቆዳ የአሰራር ሂደቱ ከከሎ ጋር ይመሳሰላል። ልዩነቱ ሁሉም ዝግጅት አልቆ ጌጣጌጥና ዘርፍ የሚደረግበት ደረጃ ላይ ሲደርስ እንዲሁም የቆዳው መጠን ከፍ ማለት ነው።ይህንንም ጉዳይ አቶ ቦንሰሞ ሚኤሶ እንደሚከተለው ገልጸውታል።

> ለከሎ ተብሎ የሚታረድ ከብት አለ ማለት ነው። ይታረዳል፤ ከታረደ በኋላ ይለፋል። አርዝመው አሳጥረው ያዘጋጁታል። እንዲረዝም ወደታች የሚለቁትም አሉ። ከዚያም ይፋቃል የሚፍቁት ሙያው ያላቸው አሉ። እንጨት ላይ ሰቅለው እንዲፍታታ ያደርጉታል ከዚያ በኋላ ያሹታል። ሲለሰልስ የሚጠመጥሙበት ነገር አለ። ጠምጥመው እንዲለሰልስ ያደርጉታል። ከለሰለሰ በኋላ ደግሞ በቅቤና በሚሽት ነገር ይጠቀልሉትና ልብስ ይሆናል። ከዚያም ሽታውን ካጠፉ በኋላ ከላይ ይለበሳል። በከሎ ላይ በሁለቱ ጫፎች ዘርፍ ያደርጉበታል፤ ወደ አንገት በሚውለው በኩል ደግሞ ከጨሌ ጥለት ይሰሩበታል። (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

ፎቶ ቁ.6 በኮከሳ ዘርፍ የሚሰራበት ከሎ ሀንዳራ

ያገቡት ሴቶች ከሎ የጥለት/ዘርፍ/ የተባለበት ምክንያትም ከላይ ጫፉ ላይ የተለያዩ ቀለማት ካኗቸው ክሮችና ጥጦች ዘርፍ ስለሚሰራበት ነው። ይህን ልብስ የታጨች ሴትም እንደምትለብሰው የአካባቢው ተወላጆች ይናገራሉ።

ቦኬ(bokee)፡- መጠነኛ ቁመት ያለው ከቆሎ በላይ የሚለበስ ልብስ ነው። ቦኬን የሚለብሱ ሴቶች በትዳር ህይወት ብዙም ያልቆዩ ናቸው። በአብዛኛው ሴቶቹ ባገቡ በጥቂት አመት ውስጥ ልጅ ይወልዳሉ ተብሎ ስለሚታመንና እስከሶስት ልጆች ሴት ወጣት ስለምትሆን ይህንን የልብስ አይነት ትለብሳለች። “eegasii bokee jedhama. bokeen tunnin takka dhaleetti haga sadii dhaleetti ta uffattuu jechuu dha.”(ከዚያም ቦኬ ይባላል፤ይህንን ከአንድ እስከ ሶስት የወለደች ሴት የምትለብሰው ነው) አብደላ ሉገማ (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 30፣2000 ዓ.ም)።

ሴቶቹ በልጅነታቸው ስለሚዳሩ ሶስት ልጆችን እስከሚወልዱበት ጊዜ ድረስ እራሳቸውን ሊጠብቁ በተለያዩ ጌጦች ያማረ ልብስን ሊለብሱ ይችላሉ።

ቦንኮ(bonkoo)፡- ቦንኮ በእድሜ የገፉ እናቶች የሚለብሱት ልብስ ነው። እንደ ከሎና ቦኬ የካባ ቅርጽ ያለው ሲሆን በቆሎ ላይ ተደርቦ ይለበሳል። ከከሎ የሚለየው ከሎ ሲዘጋጅ የሚተወው የሚታረደው ከብት የእግር ቅርጽ ለዚህ አይተውም፤ በሁለቱ ጎኖች ወጥ የሆነ ቅርጽ አለ። ቦንኮ በቁመትም ሆነ በመጠን ከቦኬና ከሎ ይበልጣል። ይህንንም የሚለብሱት አቶ አብደላ እንደሚሉት ከሶስት ልጆች በላይ የወለዱ ናቸው። ቦንኮ የእናቶች ነው። ትልቅ ነው። ላም፣እንቦሳ እና ወይፈን ከሚባሉት ቆዳ የሚሰራ ነው። ለውበት ብዙም አይጨነቁም። ለማስዋብም ብዙም አይተኮርበትም፤ከዛ ይልቅ በተለይ ለተለያዩ በአላት ሲለበስ ጥሩ ሽታ እንዲኖርና እንዳይጨማደድ ይጠነቀቁለታል።

> Gogaa lowwanii kana illee ka ta’uuf bonkoo kana kan isaan irraa hojjataniitin jedhan Kan uffatuu danda’an horii ykn gosa sangaa irraa qalamuun hin da hojjatan.bonkoo horii dhaltirraa hojjatan bu’uura mataa ofii danada’ee qaba. Gosa dhalti kessaa kanneenirraa hojjatama. Bonkoon dubartii …sogoof sorgoo qaba dubbiin.አብደላ ፣ሉገማ(ቃለመጠይቅ መጋቢት 30፣2000 ዓ.ም)

የከብቶች ቆዳ የሚሆንበት (ምክንያት እነሱ የሚለብሱት ቦንኮ ሊሰራ የሚችለው ከብት አልያም የእርድ ሰንጋ ቆዳ አይደለም። ቦንኮ ከወላድ ከብት ቆዳ ይሰራል። ይህም የራሱ የሆነ ስረመሰረት አለው። የወላድ ዘር ከሆኑት ይሰራል። ሰምና ወርቅ አለው ነገሩ።

ቅኔ የተባለውም ለሴቶቹ ቦንኮ የላም ቆዳ ተመራጭ መሆኑ ነው። ለልብሱ የላም ቆዳ መመረጡ ምክንያት ወላድ መሆኗን ለማመልከት ነው። ልጆች ወልዳ አራትና አምስት ልጆች ሲኖሯት ይህንን ልብስ መልበስ ትጀምራለች። ቦኬውም ሆነ ቄጣው ለልጆቿ ይቀመጣል። ሀርሰማ(Harsama)፡- የኮኮሳ ሴቶች በተለይ በቀድሞ ጊዜ የሚለብሱት የታች ልብስ ሀርሰማ በመባል ይታወቃል። ይህ ከቄጣ በቁመትም ሆነ በውበት የተለየ ነው። ይህንንም የሚለብሱት እናቶች ናቸው። ረጅም ከቆዳ የሚዘጋጅና የጉርድ ቀሚስ ዘር የሆነ ነው። ሀርሰማ የሚለው ስያሜ ከታች የሚለበስ በመሆኑ የተሰጠው ነው ይላሉ አቶ ከድሮ ገነሞ(ቃለመጠይቅ፣ግንቦት 5፣2000 ዓ.ም) አቶ አብደላ ደግሞ ቃሉ የተለያዩ ትርጉም ያላቸው ቃላት ስብጥር ነው ይላሉ። “harsamaa jedhaniin harsama jechi jedhu ammoo horsa’aa namooomaa jechuu dha.sa’aallee horuu namallee horuu.”(ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 30፣2000 ዓ.ም) ይህ ሆራ/ክበሩ፣አፍሩ፤ሰአ/ላም ከብት፤ነመ/ሰው የሚሉ የሶስት ቃላት ውጤት ነው። ባጠቃላይ በከብትም በሰውም ክበሩ ብዙ እንደማለት ነው። በዚህን ጊዜ እናቶች ልጆች ወልደው ልጆቻቸው ለጋብቻ፣ለቤት ውስጥ ስራ፣ለግብርና ወዘተ የሚደርሱበት ወቅት ነው። በመሆኑም ልጆች ደርሰው ሀብትና ንብረት በሚደረጅበት ወቅት እናቶች የሚለብሱት ልብስ በመሆኑ ሀርሰማ የሚል ስያሜ ለልብሱ ተሰጥቶታል። ሀርሰማ ልክ እንደ ቄጣ በሀንፈላ(hanfalaa) ይታሰራል። ይህም መቀነት በመሆን ያገለግላል።

እስካሁን ያየናቸው ያገቡም ሆኑ ያላገቡ ሴቶች አልባሳት ውስጥ በኮኮሳ የሚገኙት ጥቂቶቹ ናቸው። በተለይ ከታች የሚለበሱት ሀርሰማና ቄጣ ታሪክና ስማቸው እንጂ ለምሳሌነት እንኳን በአካባቢው አይገኙም። ከላይ ከሚለበሱት ውስጥ ቦኬ አሁን አይስተዋልም። ባጠቃላይ ካሉት ውስጥ ቦንኮ በብዛት የሚለበስ የልብስ አይነት ነው። ለእነዚህ የቆዳ ልብሶች መጥፋት ምክንያት በማለት የማህበረሰቡ ተወላጆች የሚጠቅሱት ሁኔታ አለ። መረጃ አቀባዮቼ እንደነገሩኝ በዘመነ ኃይለሥላሤ እና በደርግ ጊዜ በአካባቢው ባጠቃላይ ልብሱ በሚለበስባቸው የአርሲ ማህበረሰብ መኖሪያ አካባቢዎች አዋጅ ታውጆ ነበር። ይህንን የቆዳ ልብስ መልበስ የለባችሁም የሚል ነበር።

Zabana Haayilasillaasee keessa awaajii jedhanii awaajii kana erbe gurraattii qabatanii gabaa keessa deemanii awaajii!awaajii! jedhan. Biyya achii illaalaa itti bayaan. Gabaa keessati hin caqasan.gizee san bonkoo ka katamaatillee uffate dhufullee haa mummuramuu jedhanii akkasiin badee bonkoon.qeexxaan ammoo haga bullukkoon,huccuun argamtee.
ሼክ ከድር ሀያቶ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 29፣2000ዓ.ም)

(በኃይለሥላሴ ዘመን አዋጅ አሉ። ይህንን አዋጅ ጥቁር ትንሽ ቁርበት ይዘው ገበያ ውስጥ በመሄድ አዋጅ አዋጅ አሉ። ወደ ሀገሩ አያዩ ዘመቱበት።ገበያ ውስጥ ህዝቡን ተከታተሉት። በዚያን ጊዜ ቦንኮ ከተማ ውስጥ እንኳን ለብሶ የሚመጣ በላዩ ላይ እንዲቀዳደድ ተባለ። በዚያ ምክንያት ጠፋ። ቁጣም ወጩ ከመጣ በኋላ አልተገኘም።)

በተጨማሪም ለሀርሰማም ሆነ ለቁጣ እንዲሁም ሌሎች የልብስ አይነቶች መጥፋት ባለፉት ሁለት መንግስታት የነበረው ህዝቡ ልብሱን እንዳይለብስ የተደረገበት እገዳ ነው የሚሉት ደግሞ አቶ ቦንሰሞ (ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም) እና ወ/ሮ ደሜ ቱፋ(ሚያዚያ 4፣2000 ዓ.ም) ናቸው። በጊዜው ልብሱን በታወጀው መሰረት ማውለቅ ያልቻለ በላዩ ላይ ልብሱን ከመቅደድ እስከ እስር የሚደርስ ቅጣት ይደርስበት ነበር። ሌላው የልብስ አይነት ደግሞ ቆሎ የሚባለው ነው። በመስክ ቆይታዬም እንደተመለከትኩት ካላይ የሚለበሰው የቆሎ አይነት አሁን በኮኮሳ የለም ይህ ልብስ መቼ መለበስ እንዳቆመ በትክክል የሚያስታውስም አላገኘሁም። በዚህ አካባቢ የሚለበሰው የቆሎ አይነት ቆሎ ፋጢሜ የሚባለው ነው። ቆሎ ፋጢሜ ባለ አንድ ገጽታ ነጠላ ከስር የሚለበስ የልብስ አይነት ሲሆን በአቴቴ በአል ላይ የሚገኙ እንዲሁም በአሉን የሚደግሱ ሴቶች ይለብሱታል።

በዚህ አካባቢ በተለይ በገጠራማዎቹ ቀበሌዎችና በከተማውም ባህሉን አጠንክረው በያዙ ሴቶች ይኸው ወጩ ይለበሳል። ሌሎቹም ወጩ የሚባለውን ነጩን የጥጥ ውጤት ልብስ አይሁን እንጂ ጎጃም አዘነ የሚባለውን ከክር የሚሰራ ብትን ልብስ በወጩ ቅርፅ አድርገው ይለብሱታል። ይህንን ወጩ ለመያዝ ወይም ለማሰሪያ የሚያገለግለው ከጥጥ የሚሰራ ቀጭን ባለጥለት ወይም ጥለት አልባ መቀነት ነው። ይህም (Sabbata) ሰበተ ይባላል።

4.1.3.1 ልብሶቹና አገልግሎታቸው

ልብሶች እንደተጠቃሚው ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላሉ፡፡ ሰውነትን ከብርድ ለመከላከል፡፡ ለጌጥነት ለተለያዩ ዝግጅቶች የሚለበሱ እንዲሁም ለስራ አመቺነት የሚመረጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እነዚህን አልባሳት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መክፈል ይቻላል፡፡ እነዚህም የክትና የአዘቦት ቀን የሚባሉት ናቸው፡፡

> ...uffanni bakka lamatti qoodama;maqaa lama qaba. Uffata lafaafi uffata gaafa ayyaanaa jedhama. uffannii kan gaafa ayyaanaa uffatan fakkenyaaf dubartiin yoo ateetee baatu...qulqullinni isaa akka eegamuu... mana keessatti yoo jennu kan tajaajila addaatif mana keessati ufatamuu akka qorri nama hin dhofne qaama ofirraa ittisuuf ka mana keessatti uffatan.(ብርሀኑ በሪሶ ሚያዚያ 4፤2000 ዓ.ም)

አልባሳት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ የክት ልብስና የአዘቦት ልብስ ናቸው፡፡ የክት ልብስ ለተለያዩ በዓላት የሚለበሱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በአቴቴ ጊዜ የሚለበሱት ንፅህናው የተጠበቀ ነው፡፡ እቤት ውስጥ ስትሰራም የምትለብሰው ይለያል፡፡ የቤቱ ለብርድ እና ለስራ ተብሎ የሚለበሰው ነው፡፡ ነገር ግን ከጌጣጌጥ ጋር የሚለበሰው ለክብር ዘመድ ለመጠየቅ ሲሄዱ የሚለብሱት ነው፡፡

በኮኮሳ ሴቶች የሚለበሱ ልብሶች በአብዛኛው ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የልብሱ ዘር አንድ ሆኖ እቤት ውስጥ ስራ ስትሰራ ከላይ ቆሎ ከስር ደግሞ በቀድሞ ጊዜ ቂጣ ወይም ሀርሰማ ታደርጋለች፡፡ አሁን ደግሞ ወጨ ትለብሳለች፡፡ ያገቡ ሴቶች እቤት ውስጥ የሚለብሷቸው ልብሶች ለስራው እንደሚያመቻቸው ቆሎ እና ወጨ ቦንኮም ሊደርቡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የአዘቦት ቀን የመለበሻ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የክት ልብሶች የመለበሻ አጋጣሚዎችን እንመለከታለን፡፡

ሴቶች አሁንም ሆነ በድሮ ጊዜ ከቤት ሲወጡባቸው የሚችሉባቸው የተለያዩ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ዘመድን ለመጠየቅ ከሚደረግ ጉዞ ጀምሮ በተለያዩ ክብረ በዓላትና መድረኮች ላይ እስከመገኘት ያሉትን ጉዳዮች ያካትታል፡፡

የአርሲ ሴት ወደ ውጭ የምትወጣበት ጉዳይ አንዱ ቤተሰብ ለመጠየቅ ስትሄድ ሁለት ገበያ ስትወጣ፣ ሶስት ሰርግ ስትሄድ፣ አራተኛው ለቅሶ ሲሄዱ፣ አምስተኛው የወለደችን ሴት ለመጠየቅ ሲሄዱ፣ አንድ ሰው ችግር ሲደርስበት አንድ ጀግና ገድሎ ሲገባ፣ ከቤት ሲወጡ ልብሳቸው እቤት ሲውሉ የሚያደርጉትና እላይ የተጠቀሱት ቦታዎች ሲሄዱ የሚያደርጉት ይለያያል። አብዱልቃድር ገልሞ (ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 29፣2000 ዓ.ም)

እንግዲህ እቤት ሲውሉ የሚለብሱትና ከቤት ውጭ ባሉ እላይ ከተጠቀሱት ቦታዎች ሲሄዱ የሚለብሱት የተለያዩ መሆናቸውን ተመልክተናል። እነዚህ ከላይ የቀረቡት ምክንያቶች የአልባሳቱን አይነት፣ የአለባበስ ሁኔታና የመለበሻ አጋጣሚ ለይተን ወደምንመለከትባቸው ክፍሎች ይመሩናል።

4.1.3.2 የኮኮሳ ሴቶች አልባሳት የመለበሻ አጋጣሚዎች

ሴቶች ከውጭ ሲወጡ የሚችሉባቸው የተለያዩ ጉዳዮች አሏቸው። በማህበረሰቡ ሴቶች አደባባይ የሚወጡባቸው አጋጣሚዎች ሰርግ፣ አቴቴ፣ ለቅሶ ዘመድ ጥየቃ ገበያ ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ በማህበራዊ ህይወትና በግለሰብ ህይወት ውስጥ የሚታለፍባቸው ደረጃዎች ናቸው።

ሰርግ(cidha)፡-በዚህ ወቅት በተለያየ ዕድሜ ያሉ ሴቶች በዚህ በዓል ላይ ይሳተፋሉ፤ የሚለብሷቸው ልብሶችም እንደዚሁ የተለያዩ ናቸው። ልጃገረዶች ከጥጃ ቆዳ የተሰራችውን ከሎ ለብሰው፣ ልጃገረዶቹም ፀጉራቸውን ከሶስት በላይ በሚሆን ዲዛይን ተሰርተውና /ሄቆ/ ይሉታል። ከክርና ከጥጥ በተሰራ የጸጉር ማስዋቢያ ፀጉራቸውን ተሰርተው ወደታች ይለቁታል። ከከሎው በታች ቆሎ ለብሰው ከምታገባው ጓደኛቸው ቤተሰብ ቤት በመሄድ በተለየሽን ስሜት ዘፈን ይዘፍናሉ። በዚህን ወቅት ሙሽራዋ ከሌሎቹ ልጃገረዶች የተለየ የፀጉር አሰራር ትሰራለች፤ ልብሷም በተለይ ካባው ከከሎ ወደ ቦኬ/ያማረችና ልዩ ልዩ ጌጥ ያለባት ትዘዋወራለች። ከስር የምትለብሰው ወጨ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ የጌጥ አይነቶችን ታደርጋለች። በስርጉ ላይ የሚታደሙት ያገቡት ሴቶችም ረጅሙን ቦንኮ ከላይ፣ ከስር ቆሎ ከዚያም ወጨ ይለብሳሉ።

አቴቴ (Ateetee) ፡- ይህ የኮኮሳ ሴቶች ሌላው የልብስ መልበሻ አጋጣሚ ነው። አቴቴ የከብቶችንና የልጆችንም ጤና ትጠብቃለች ተብላ የሚታመንባት ሴት ዛር ናት። የተለያዩ የአቴቴ አይነቶችም አሉ። እዚህም እናት(ayyoolee)፣ሰብሳቢ(saboleee)፣የጦርነት(duulaa) ወይም የጭንቅ ቀን እናት እና የየቀኑ(guyyaatuu) እናት በመባል ይታወቃሉ።(ከተማ ጅማ 1963፣97) በእያንዳንዱ የአቴቴ ስያሜም እናት የሚል ይታከበታል። ይህም ቅርበቷንና

ጠባቂነቷን ለመግለጽ ነው፡፡ አቴቴ በአካባቢያቸው ዝናብ ሲጠፋ፣ በሽታ ሲገባና የመሳሰሉት አደጋዎች ሲከሰቱ አምላካቸውን ለመለማመን ወደወንዝ ወይም ለም ቦታ የሚወጡበት አጋጣሚ ነው፡፡ "በአቴቴ ወቅት ሰዎች የሚወጡበት ምክንያት የአምላክን ፈቃድ ለመለመን ነው፤ ታረቀን ለማለት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ልብሱን ለብሰው ይወጣሉ፡፡"(ብርሀኑ በሪሶ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 4፣2000 ዓ.ም) በዚህን ጊዜ ከሚለብሷቸው ልብሶች በተጨማሪ የቤተሰብ ለቂያቸው ለከብቶቻቸው ጠባቂ በየጊዜው ያደረጉትን ዕርድ የሚያመላክት የተቆራረጠ ቆዳ አናቷ ላይ የተደረገባትን ቀጭን ረጅም እንጨት ይይዛሉ፡፡ ይህቺ እንጨትም በአካባቢው አጠራር ሲንቄ(siinqee) ትባላለች፡፡

ለቅሶ (Booyicha)፡- ለቅሶ ከኮኮሳ ሴቶች የልብስ አጋጣሚዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ "በለቅሶ ጊዜ ባል የሞተባት ሴት ቦንኮውን ገልብጣ ትለብሳለች፡፡ ጌጣጌጥ አታደርግም፤ ሌሎቹም ቢሆኑ እንደዚሁ ነው፡፡ በድሮ ጊዜ ጫማ የላቸውም፤ በእግራቸው ይሄዱ ነበር፡፡" ሼክ ከድር (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 28፣2000 ዓ.ም) ያገቡ ሴቶች ለለቅሶ ሲወጡም የሚለብሷቸው ልብሶች አሏቸው፡፡ በመሠረቱ ልብሱ በሌላውም ጊዜ የሚለበሰው ሆኖ ልዩነቱ ተገልብጦ የሚለበስ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ወቅት በሴቷ ላይ የሚስተዋለው አጠቃላይ ሁኔታ እንደሚከተለው ነው፡፡ "ባሏ የሞተባት ሴት ቦንኮና ቁጣ/ሃርሰማ/ ትለብሳለች፡፡ ሌላ ጌጥ አታደርግም፡፡ እግሯን መቼም አትታጠብም፤ እጃቸውን የማይታጠቡ አሉ፤ እግሯ ላይ ጫማ የላትም፡፡ በጣም ታዝናለች፡፡ እስከ አንድ አመት ተደላድላ አትተኛም፡፡ እሱንም አመድ ውስጥ ቁርበት አንጥፋ ትተኛለት፤ፊት ለፊት አትተኛም፡፡" አያንቱ ዱቤ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 1፣2000ዓ.ም) ይህ በቀድሞ ጊዜ የነበረው ሲሆን ቦንኮው እንዳለ ሆኖ ቁጣው/ሃርሰማው/ በወጩ (ነጭ የጥጥ፣ ጣቃ ልብስ) ተተክቷል፡፡

በቅርቡ በመስክ ወቅት በወረዳው የሚሊኒየም የበዓል አከባበር ላይ ሴቶቹ በተለያየ የዕድሜ ደረጃ ላይ ያሉት የተለያዩ አልባሳትና ጌጣጌጥን አድርገው በበዓሉ ላይ እንደተገኙ ተመልክቻለሁ፡፡ በዚህ በዓልና በተለያዩ መድረኮች የሚለበሱት የልብስ አይነቶች ባብዛኛው አንድ ናቸው፡፡

ፎቶ ቁ.7 ያገቡ ሴቶች አለባበስ በኮኮሳ የሚሊኒየም በዐል ላይ

በኮኮሳ ሴቶች በቤትና በውጭ የሚለብሷቸው ልብሶች አሉ። እነዚህ አልባሳት የጥራት ልዩነት ካልሆነ በስተቀር የስም ልዩነት የላቸውም። "እቤት ውስጥ ሁል ጊዜ ሲሆኑ አሮጊቶች የሚለብሱት ሃርሰማ ይባላል። ከቤት የማይወጡ ከሆነ እሱኑ ለብሰው ይውላሉ ማለት ነው። ቆሎውንም ከላያቸው አያወርዱትም ቆሎ የትልልቆች አለ። ልጃገረድ ግን ሃርሰማ አትለብስም ሁኔታቸውና ዘራቸው አንድ ነው። ነገር ግን የቤትና የውጭው ልብስ ልዩነት አለው።" አብደላ ሉገማ (ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 30 ፣2000 ዓ.ም)

አሮጊቶችም ሆኑ ወጣቶቹ እቤት ውስጥ የሚለብሱት ስሙና ዘሩ አንድ ነው። ነገር ግን እቤት ሲውሉ የሚለብሱት አሮጌ፣ በተለያዩ ጌጦች ያላሸበረቀ ነው። በልዩ ልዩ በዓላት የሚለበሱት ግን የተለያዩ ጌጦች ጨሌ፣ ዶቃ እና ቀሪሳ /ነጭ ቁልፍ መሳይ/ ተንጠልጣይና ተጣባቂ ሆነው የሚሰሩበት ነው፡:

4.2 የኮኮሳ ወረዳ ሴቶች ጌጣጌጦች

የኮኮሳ አርሲ ሴቶች ከአልባሳት ይልቅ ብዙ ጌጦች አላቸው። እነዚህ ጌጦች በተለያዩ ቦታዎች የሚሰሩ፣ የተለያዩ ቀለማትና የተለያዩ ስሞች ያሏቸው ናቸው። ከእነዚህ ጌጦች አብዛኛውን ቁጥር የሚያደርጉት ያገቡ ሴቶች ናቸው። ቁጥሩ ይነስ እንጂ ልጆችም ሆኑ ኮረዳዎች የሚያደርጓቸው ጌጦች አሏቸው። "ጌጥ ስንል ጌጥ ማለት ውበት ማለት ነው።

ለውበት የሚያደርጉት ማለት ነው።"ቦንሰሞ ሚኤሶ(ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም) ባህላዊ ጌጦች ተጠቃሚው ማህበረሰብ በአካባቢው በሚያገኛቸው ቁሶች በመታገዝ ለመዋቢያነት የሚያበጃቸው የእጁ የጥበብ ውጤት ናቸው። የኮኮሳ ሴቶችም ከተለያዩ ቁሶች የተሰሩ ጌጦችን ያደርጋሉ። እነዚህም ጌጦች በሁለት ተከፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

4.2.1 ያላገቡ ሴቶች የሚያደርጓቸው ጌጦች

በዚህ ክፍል የሚካተቱት ሴቶች ልጆች፣ ለጋብቻ የደረሱና ለትዳር የታጩት ናቸው። ልጆቹ ወይም ልጃገረዶቹ ከራስ ጀምሮ በየደረጃው የሚደረጉ የተወሰኑ ጌጦች አሏቸው። ትንንሽ ሴት ልጆች ፀጉራቸውን ከፊትና ከመሃል አስቀርተው ይላጫሉ። ይህ የሚሆነው ለአቅመሄዋን እስኪደርሱ ነው። በዚህን ጊዜ የፊቱ ጸጉራቸው አንድ ቦታ ተሰርቶ የኋላው ከተለያዩ የክር እና የጥጥ አይነቶች ጋር ተቀላቅሎ ወደታች ረዝሞ ይሰራል። ከዚህ ሌላ በራሳቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ የለም።

ጆሮዋቸው ላይ ቀሾ (Qashoo gurraa) የሚባል ልጥፍ የጆሮ ጌጥ ያደርጋሉ። በአንገታቸው ደግሞ ከተለያዩ የጨሌ አይነቶች ዶቃ ታክሎባቸው የተሰሩ የአንገት ጌጦችን ያደርጋሉ። በዚህን ጊዜ እጃቸው ላይ ቢቶ(bitoo) የሚባል የሽቦ ወይም ከብረት የተሰራ ነጠላ ብረት ያደርጋሉ። በእግራቸው ላይ የሚያደርጉት አልቡ የሚባል በአንድ በኩል ክፍተት ያለው ክብ ብረት ነው። አንዲት ልጃገረድ የምታደርጋቸው ጌጦች ትንንሾቹ ከሚያደርጓቸው በቁጥር ይበልጣሉ። እነዚህንም የራስ፣የጆሮ፣ የአንገት፣የእጅ በማለት ከፋፍለን ቀጥሎ እንመለከታለን።

- የራስ ጌጥ

አንዲት ሴት ለአቅመሄዋን ስትደርስ ከፊትም ሆነ በመሃል ያለው ፀጉሯን ታሳድጋለች። ፀጉሯን የምትሰራበት ሁኔታ እንደሚከተለው ነው። "ፀጉሯን ተሰርታ ትሄዳለች። በሄቆ ፀጉሯን ትሰራለች።" ገሼ ጢቃቆ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 5፣2000 ዓ.ም፣ብርሀኑ በሪሶ ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 4፣2000 ዓ.ም) ሄቆ ከጥጥና ከክር በወፍራሙ እንደ ጸጉር እንዲያገለግል ተደርጎ የሚዘጋጅ ነው።

ይህም ከመሃል ያደገው ፀጉር በቀጭኑ እየተሰነጠቀ ከፀጉሩ ቅንጣት ጋር የሚሰራ ነው። ይህ ስራ ዋናው ጠቀሜታው ሴቷ በምትዘፍንበት ጊዜ ስትንቀሳቀስ ውበትን እንዲፈጥር በማለት ነው።

> የጆሮ ጌጥ

አንዲት ልጃገረድ በጆሮዋ ላይም ቢልቄ (billiqqee) የሚባል የጆሮ ጌጥ ታደርጋለች፡፡ይህም ጌጥ ወደታች የሚንጠለጠል ነው፡፡ "tunnin baxxee qaccen kinoo gad dheerata hin ballata." ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም) ይህ የጆሮ ጌጥ ብዙውን ጊዜ ከመዳብ የሚሰራ ሆኖ ወደታች የሚንጠለጠል ጫፉ የጦር ቅርጽ ያለው ነው፡፡

> የአንገት ጌጥ

ወረድ ብላ በአንገቷ ላይ ጨሌ ሁዶ (Callee hudhoo) የሚባል ጌጥ ታደርጋለች፡፡ ትርጉሙም አንገትን የሚያጣብቅ/የሚያንቅ ማለት ነው፡፡ ጌጧም በትንንሽ ጨሌ ተሰርታ አንገትን አጣብቃ ስለምትይዝ ይህ ስያሜ ተሰጥቷታል፡፡ ይህንን ጌጥ የምታደርገው ከመታጫቷ በፊት ነው፡፡ አንዲት ኮረዳ ለጋብቻ ስትታጭ የምታደርገው የአንገት ጌጥም አለ፡፡

> በኦሮሞ ባህል አንድ ወንድ ሴቷን ለጋብቻ ሲጠይቅ ቢቶ ይይዛሉ፤ እናም ያንን ቢቶ እጇ ላይ ታደርጋለች፡፡ ይህንን በባሏ ቤት ሳለችም ታደርገዋለች፡፡ ... ወንድም ሲያገባት ሜጣ ያደርግላታል፡፡ ሜታውን ከቁቤ ጋር ያደርግላታል፡፡ እሷም የጋብቻው ዕለት ሜታውንና ቁቤውን አብራ ይዛ ትሄዳለች፡፡ ከድሮ ገነሞ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 5፣2000 ዓ.ም)

እነዚህ ከወንዱ የሚሰጧት ጌጦች በማህበረሰቡ ዘንድ ውጫዊ ተግባቦት ስላላቸው ለጋብቻ ሌላ ወንድ አይጠይቃትም፡፡ በተለይ በአንገቷ ላይ የምታጠልቀው ቁቤ/ቀለበት መታጨቷን የሚያመለክት ነው፡፡

> የእጅ ጌጥ

አንዲት ልጃገረድ በምተታጭበት ወቅት በእጇ ላይ የምታደርገው አንድ ጌጥ ነው፡፡ ይህም ከወደፊት ባሏ የሚበረከትላትና በጋብቻዋ ወቅትም አድርጋ የምትሄደው ነው፤ ቢቶ(bitoo) ይባላል፡፡ ቢቶ የሚባለውና በግራ እጇ ላይ የምታደርገው ይህ አንባር ጌጥ ከልጆቹ የሚለየው በመጠን ነው፡፡ ሁለቱም ከብረት አልያም ከሸቦ የሚሰሩ ናቸው፡፡ቢቶ ማለት ግራ ማለት ነው፡፡ ይህንንም ስም ያገኘው ከሚደረግበት የግራ እጅ ላይ ስለሆነ ነው፡፡

4.2.2 ያገቡ የኮኮሳ ሴቶች የሚያደርጓቸው ጌጦች

የኮኮሳ ሴቶች እንደየኑሮ ደረጃቸውና ዕድሜያቸው የተለያዩ ጌጦችን ለውበት አልያም ለመለያነት ያደርጋሉ። እድሜያቸው ለጋብቻ ሲቀርብ ወይም በጋብቻ ውስጥ ባሉበት ወቅት የሚያደርጓቸው ጌጦች መጠንና አይነታቸው በዛ ያለ ነው። እናቶችና ወደትዳር አለም በቅርቡ የገቡት ሴቶች ከራስ ፀጉራቸው እስከ እግር ጣታቸው ድረስ የተለያዩ ጌጦችን ያደርጋሉ። እነዚህን ጌጦች አንድ በአንድ ቀጥሎ እንመለከታለን።

❖ በራስ ላይ የሚደረጉ ጌጦች

ያገቡሴቶችየሚያደርጓቸውየራስጌጦችጨሌአዳ፣ቆለ/ደርበተ፣ሎቱ፣ሰንዳበ፣ቀነፋ፣ፎሮረ፣የ ሚባሉት ሲሆኑ ከነዚህ ጌጦች ውስጥ ለጌጥነት ብቻ የሚውሉ እና ተጨማሪ አገልግሎት ያላቸው አሉ።

ሎቱ(Lootuu)፡- ሎቱ የከብት ቆዳ በቀጭኑ ተሰንጥቆ ተዘጋጅቶ በላዩ ላይ ሽቦ የሚደረግበት የጌጥ አይነት ነው። ይህ የጌጥ አይነት መሃል ለመሃል ቀሪሳ የሚባል ቁልፍ መሳይና ሴቶቹ ለጆሮ ጌጥነት የሚጠቀሙት ማስዋቢያ ተሰፍቶበት ለጎፍታው መያዣነት በተጨማሪ ያገለግላል። ይህ የጌጥ አይነት ከሽቦ ሰርተው ቆዳ ላይ የሚያጣብቁት በጎንና ጎን ዘርፍ ያለው ነው።

ጨሌ አደጀሌ (Callee adda jalee)፡-ይህ የጌጥ አይነት ከቀይና ነጭ ጨሌዎች የሚሰራ ነው። ከሎቱ በመቀጠል ጉፍታ በሚያስሩት ሙስሊሞች ጉፍታው እንዳይንሸራተት ከሚያስሩት ነጭ ሻሽ ቀድሞ የሚታሰር ዘርፍ ያለው የግንባር ጌጥ ነው።አደጀሌ የአማርኛ ፍችው ከግንባር ስር ማለት ነው።

ቆለ(qola)፡- ይህ የጌጥ አይነት በአንዳንድ አካባቢዎች ደርበተ(darbata) በመባል ይታወቃል። ጉፍታ የሚያስሩት በጉፍታቸው ላይ የሚያስሩት ደግሞ ከጫፉ የማይሰራውን ጸጉራቸውን እንደዘመናዊው የጨርቅ የጸጉር ማስያዣ በአንድ ላይ ይዞ ከኋላ የሚንጠለጠል ነው። ቀይና ነጭ ቀለማት ያላቸው ጨሌዎች ይህን ጌጥ ለመስራት ያገለግላሉ።

ፎቶ ቁ. 8 ያገቡ የኮከሳ ሴቶች የሚያደርጉት የራስ ጌጥ

ሰንዳበ (Sandaaba) ፡- ይህ በሙስሊም ሴቶች ብቻ የሚደረግ ሰንዳበ የተባለ ጌጥ ሲሆን ግንባር ላይ የሚለጠፍ፣ የልብ ቅርጽ ያለውና ሙሉ በሙሉ ቀይ ቀለም ያለው ጌጥ ነው፡፡"sandaaba warra islaamatu godhata. Kan guftaa godhatuus warra islaamaati." ፋጢማ ጃርሶ (ቃለመጠይቅ፣ግንቦት 2፣2000 ዓ.ም) ሰንዳበ የሚያደርገው ሙስሊም የሆነ ነው፡፡ ጉፍታም የሚያደርገው ሙስሊም ነው፡፡

ቀነፋ(qanafa)፡- ሴቶቹ የሚያደርጉት አንድ ጌጥ አለ፡፡ ይህ እንደጌጥም እንደመለያም የሚያገለግል ነው፡፡ ቀነፋ ያደረገች ሴት ገና ወልዳ የተነሳች ናት፡፡ በምታደርገው የቀነፋ ብዛት የወለደችው ልጅ ቁጥር ይታወቃል፡፡ ጌጡ በብዛት ከእንጨትና ከሽቦ የሚሰራ ሲሆን ቁቤ የሚባል ቀለበትም ይደረግበታል፡፡ ይህንን ጌጥ የሚሰራላት ባለቤቷ ሲሆን አንድ ከወለደች አንድ ሁለት ከወለደች ደግሞ ሁለት ይሰራላታል፡፡ እንጨቱ በቅርጽ ይሰራና የከብት ቆዳ ላይ ይሰፋል፤ግንባር ላይ እንዳይንሸራተት ለማስሪያነት ሽቦ ይደረግበታል፡፡

ፎሮረ(Forora)፡-ብዙውን ጊዜ ቀይ ጨሌ በብዛት ያለው ሆኖ በሁለቱ ጆሮዎች በኋላ በኩል የሚንጠለጠል ባለ ብዙ ዘርፍ ጌጥ ነው፡፡ ከሎቱ የሚለየው ሎቱ ከሽቦና ከዶቃ የሚሰራ መሆኑና ከፎሮረ በላይ የሚውል በመሆኑ ነው፡፡ ይህንንም ጌጥ ሴቶቹ ሙስሊም ከሆኑ በጉፍታቸው ላይ የሚያስሩት ሲሆን ሌሎቹ ግን ወደላይ ከፍ ብሎ ጫፉ ሳይሰራ በተተወው ጸጉራቸው ላይ የሚያስሩት ነው፡፡ ከእስልምና ውጭ የሆኑትም ቢሆኑ ጉፍታ ካልሆነ

በስተቀር ሁሉንም ጌጦች ያደርጋሉ። ከሎቱ፣ጨሌ አደጀሌና ፎሮራ፣እንዲሁም ከሰንዳበ በስተቀር የሙስሊም ሴቶች የሚያደርጉት ጌጥ የለም። ሌሎቹ ግን ሆቃ የተባለውንና ከጥጥ የሚሰራውን ክር በጸጉራቸው ቅንጣት ጋር እየቀላቀሉ ይሰሩበታል። “ka dudda duubaa sun hooqaa heeqoo kirrii heeqoo, haabareeduf aadaa tenna.” (የኋላው ሆቃ ነው ጥጥ ክር ለውበት የሚደረግ ነው ባህላችን ነው።) ሄለሜ ነጋሶ (ቃለመጠይቅ፣ግንቦት 2፣2000ዓ.ም)

- የጆሮ ጌጦች

በዚህን ጊዜ የሚደረጉት የጌጥ አይነቶች ቁጥራቸው ከፍ ይላል። አቶ ቦንሰሞ እንደሚሉትም “ammoo amma waa sadii, qarrisa,billiqqee ykn ballaqee fi maaldayaa. Ijollummaarraa jalqabee. Dubartiin kan godhatan maaldayaa, qarrisaa. (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም) “ይህ ጌጥ ሶስት አይነት ነው። ጆሮ ላይ የሚያደርጉት አሁን ሶስት ናቸው ማለት ነው። ቀሪሳ፣ ቢለቄ/በልቂ እና ማልደያ ናቸው። ማልደያና ቀሪሳ የሚያደርጉት አዋቂ ሴቶች ናቸው።

ቢልቄ (billiqqee)፡- ይህ የጌጥ አይነት ሶስት ማዕዘን ያለውና ልጃገረዶች የሚያደርጉት የጆሮ ጌጥ ነው።

Qarrisaa(ቀሪሳ)፡-ቀሪሳ የሚባለው ክብ የጆሮ ጌጥ ሲሆን አዝራር መሳይ የሆነ ከዝሆን ጥርስ የሚሰራ ነው። አሁንም ድረስ ሴቶች የሚያደርጉት ሲሆን ቀለሙ የማይለቅ ጠንካራ ጌጥ ነው።

ማልደያ(Maaldayaa)፡-የሚባለው በእናቶች የሚደረገውና እቤት ውስጥ የሚዘወተረው ነው።ይህም ክብ ሲሆን መሃል ላይ የቢልቄ የተባለችው የጌጥ ዘር ይደረግበታል። ይህን የእስልምናም ሆነ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ሴቶች ያደርጉታል።

- የአንገት ጌጦች

ከሴቶቹ ጌጦች ውስጥ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዘው የአንገት ጌጣቸው ነው። ይህም አንገትን ከሚያጣብቅ እስከ ከወገብ በታች የሚንጠለጠል ጌጥን ያጠቃልላል። አንዲት ሴት ባጠቃላይ ከአምስት በላይ የሚሆኑ ጌጦችን ታደርጋለች።

Hudhoo) ፡- የኮኮሳ ሴት ከምታደርጋቸው የአንገት ጌጦች መካከል አንገትን አጥብቆ የሚይዘው ሁዶ/Hudhoo/ የሚባለው ነው። ይህንን ጌጥ ለመስራት ቀይና ሰማያዊ ቀለማት ያሏቸው ትልልቅ ጨሌዎች ያገለግላሉ።

ጆሞሬ(Jomore)፡- ከሁዶ በመቀጠል ከአንገት ትንሽ ወረድ ብሎ የሚንጠለጠል ጌጥ ነው፡፡ ይህ ጌጥ ሴቶች እቤት በሚውሉበት ጊዜ አንገታቸው ባዶ እንዳይሆን በማለትም የሚያደርጉት ነው፤ በአሁኑ ወቅት ሴቶች ወደ ገበያ ሲወጡም ያደርጉታል፡፡ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

ጆምቦላJ(ombollaa)፡- ከላይ መጠነኛ ውፍረት ያላቸው ጨሌዎች ለመስሪያነት ያገለግላሉ፡፡ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ጨሌዎችም ይደረጉበታል፡፡

ጨሌ ጃሪ/ጨሌ ፋጢሜ (Callle jaarii ወይም Callee Faaxime)፡- ጎናዊ ስፋቱ መጠነኛ የሆነ ጌጥ አለ፡፡ ይህ የጌጥ አይነት Callle jaarii Callee Faaxime (ጨሌ ጃሪ/ጨሌ ፋጢሜ) ያረጁ ሴቶች ጨሌ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህንን አይነት ጌጥ የሚያደርጉት በእድሜ የገፉ ሴቶች ናቸው፡፡ የዚህ ጌጥ አይነተኛ መለያው መሃል ለመሃል ከአንገት ተንጠልጥሎ ወረድ የሚል መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ክብ የጋሻ አይነት ቅርፅ ያለው ቆዳ መሃል ላይ ይደረግበታል፡፡

ሀዶፍቱ(Hadhooftuu)፡- "ወደ አንገት ዝቅ ካልን ብዙ አይነት ነው፡፡ የአዋቂዎችም ሀዶፍቱ ይሉታል፡፡ አረንጓዴ ነው፡፡"(ቦንሰሞ ሚያዚያ 6፣2000ዓ.ም) ይህ ጥቁር አረንጓዴ ቀለም ባላቸው ትልልቅ ጨሌዎች የሚሰራ ነጠላ ጌጥ ነው፡፡

ተፍሴ(Tafse)፡- ይህ ሁለት ወይም ሶስት ይሆንና ቀይ፣ ነጭ ወይም ሰማያዊ ነጭ ቀይ ቀለም ያላቸው ክብ ዶቃዎችን በረድፍ ቅርፅ በማስያዝ የሚሰራ ጌጥ አለ፡፡ ይህን የጌጥ አይነት ከሌሎቹ በተለይ በሚሰራበት የቀለም አይነት ተለይቶ ወይም ሳይለይ ሁለቱን ወይም ሶስቱን አንገታቸው ላይ ያደርጉታል፡፡ የዚህ ጌጥ ቁጥር መብዛትና ማነስም የሴቷን የኑሮ ደረጃ ያመለክታል፡፡

Darbata(ደርበተ)፡- እስካሁን ካየናቸው የጌጥ አይነቶች በቁመት የተለየውና በአንገት ተጠልቆ እስከታች ድረስ የሚንጠለጠለው የአንገት ጌጥ ደርበተ ይባላል፡፡ ደርበተ የሚጣል/የሚለቀቅ ማለት ነው፡፡ ከአንገት ተለቆ እታች ስለሚደርስም ይህንን ስያሜ አግኝቷል፡፡ ይህ ጌጥ በቀጫጭኑ በተሰነጣጠቀ ረጅም የከብት ጅማት ላይ ቢያንስ አራት ወይም አምስት ቀለማት ያላቸው ጨሌዎች ተደርገውበት የሚሰራ ነው፡፡ እነዚህ ጨሌዎች መለስተኛ መጠን ያላቸው ሲሆኑ በእያንዳንዳቸው የጅማት ክሮች ላይ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ተደርገው በስተመጨረሻ ዘርፋዊ ህብርን ይፈጥራሉ፡፡ "ተምሴ አለ፤ ከብረትና ከተለያዩ ጨሌዎች ይሰራል፡፡ የሚያደርጉበት ደግሞ የከብት ጅማት/ribuu/ ነው፡፡ ከብት ሲታረድ እንደ ሲባጎ

ከወገባቸው ላይ በሚያወጡት ጅማት ነው። ከዚያ በቀጭኑ አድርገው አሽተው ካለሰለሱት በኋላ ይሰነጣጥቁና ይሰሩበታል።"ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

ፎቶ ቁ. 9 የሴቶቹ ጌጣጌጦች በከፊል

የስካሁኖቹ ጌጦች ባብዛኛው የሚሰሩት የተለያየ መጠን ካላቸው ጨሌዎች ነው። ጨሌዎቹ በአካባቢው የሚሰሩ ሳይሆኑ ከገበያ የሚገዙ ናቸው። ከከብት ቆዳና ከጅማትም የሚሰሩ አሉ።

❖ የእጅ ጌጦች

ከአንገት በመቀጠል ሴቶቹ ጌጥ የሚያደርጉት እጃቸው ላይ ነው። የኮኮሣ ሴቶች በተለይ በቀድሞ ጊዜ እጅጌ አጭር የሆነችውን ቆሎ እና ቦንኮ ደርበው ሲወጡ በሶስት ደረጃዎች በእጃቸው ላይ ጌጥ ያደርጉ ነበር። አሁንም እያደረጉ ያሉ ሴቶች አሉ። በእጃቸው ላይ የሚያደርጓቸው ጌጦችም ከጣቶች ከፍ ብሎ እና ከክርን በላይ በሁለቱም አጆች የሚደረጉ ናቸው። "ወደታች ከወረድን ጌጥ የእጅ አለ፣ የብረት አለ፤ ሁለት አይነት ዘር አለው። ናሻ ወይም ደግሞ ወጫሳ የእጅ ብረት ይባላል። ላካ ደግሞ ነጭ ልጥፍ/ነጠላ/ ነው በጣም ወፍራም ቅርፅ አለው"። ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

ፎቶ ቁ.10 የእጅ ጌጦች

እነዚህ ሁለቱ ጌጦች መሠረታዊ ልዩነታቸው ለካ አንድ ወጥ መሆኑ ሲሆን ናሻ የሚባለው ደግሞ ባለብዙ እጥፍ መሆኑ ነው። ሁለቱም ግን በእናቶች የሚደረጉ ጌጦች ናቸው።

ሶስተኛው የእጅ ላይ ጌጥ ቢቶ(bito) የሚባለው ነው። ይህ ነጠላ ቅርፅ፣ ወፍራም መጠነኛ ክፍተት በአንድ በኩል ያለው የእጅ ጌጥ ነው። ቢቶ የተባለበት ምክንያት ቢቶ/ግራ ስለሆነና ጌጡም በግራ እጅ ላይ ስለሚደረግ ነው። በእጅ ላይ የሚደረግ ሚርጎ/ቀኝ/ የሚባልም እንደነበር መረጃ አቀባዮች ገልፀውልኛል።ገሼ ጢቃቆ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 5፣2000 ዓ.ም) በአሁን ጊዜ ግን በብዛት ሴቶቹ የሚያደርጉት ቢቶ የሚባለውን ነው። ይህንንም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሚያደርጉ ሴቶች አሉ። በተለይ በቀድሞ ጊዜያት ሴቶች የተለያዩ ጌጦችን ያደርጉ እንደነበር አሁንም አቶ ገሼ ጠቃቆ እንዲህ ይገልጹታል።

> እጅ ላይ ቢቶ ይባላል። ቢቶ ትንንሽም ሆነ ትልልቅ አለ። ድሮ እናቶች ቢቶ ጎርጃ የሚባል ያደርጉ ነበር። በቀኝ እጃቸው ወጫሳ/ናሻ/ ይባላል። እሱን ያደርጋሉ። በዚህ እጅ ሁለትና ሶስት ጌጦችን ያደርጋሉ። በግራ እጅ ላይ ደግሞ 6 እና 7 ድረስ ያደርጋሉ። እነዚህን ብረቶች የሚቀጠቅጡት ቀጥቃጮች ናቸው። (ሚያዚያ 5፣2000 ዓ.ም)

የቀረበው መረጃ የሚያመለክተው እነዚህን ጌጦች ሴቶቹ የሚገኟቸው ከገበያ ሲሆን የሚሰሩትና ለገበያ የሚያቀርቡትም "ቀጥቃጮች" መሆናቸውን ነው።

የጣት ቀለበት (Qubee):- በእጅ ጣት ላይ የሚደረግ ጌጥ ነው። ቁቤ ይባላል። ቁቤ ጣት ማለት ሲሆን በጣት ላይ የሚደረግ በመሆኑ የተሰጠው ስም ነው። በጣታቸው ላይ የሚያደርጉት ቀለበት ሁለቱ ሶስቱ አልያም አራቱ ጣታቸው ላይ ሊሆን ይችላል። በአንድ ጣት ላይ ሁለት ቁቤ የሚያደርጉበትም ጊዜም አለ።

❖ የእግር ጌጦች

የኮኮሳ ሴቶች የሚያደርጉት ሌላው የጌጥ አይነት በእግር ጣት ላይ የሚደረግ ነው። ይህም Qubee/lukaa/ ቁቤ ሉካ በመባል ይታወቃል። የድርብ ቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም የእግር ጣት ማለት ነው። ለጌጡ መጠሪያነት ሲውል ግን የእግር ጣት ቀለበት የሚል ትርጉም ይይዛል።በእግራቸው ላይ የሚያደርጓቸው ቀለበቶች ከሁለት እስከ አራቱ ጣቶች ላይ ሊሆኑ ይችላሉ።

> waan dirataniiin sibila didiqqaarraa kan hojjatamuu lukarra warri godhatantu jira.quba afuriratti qubee godhatan. Sibila maramee baxxaffamee, ka shiboo xixiqqoon maramuu gosa lama.isiin xixiqqoon gara maraa sadii maraa afurii kan qubee haqqee isii qabee kan guututu jira.ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

ከትንንሽ ብረት የሚሰሩትን የሚያደርጉ አሉ። አራቱ ጣታቸው ላይ ቁቤ ያደርጋሉ። ሁለት አይነት ነው።ብረቱ ተጠልምሞ የሚሰራና ከሽቦ የሚሰራ።ትንንሿ ሽቦ በሶስትና በአራት እጥፍ ተጣጠፋ ጣትን የምትሞላ ናት።

ቀለበቱ ከሽቦና ከብረት የሚሰራ ሆኖ በጣታቸው ላይ የሚያደርጉት መሆኑን የቀረበው መረጃ ይመለክታል። እነዚህ ቀለበቶች ጣት ላይ ጥብቅ ስለሚሉ በቀላሉ የመውለቅ ባህሪይ የላቸውም። በሌላ በኩል እነዚህን የጣት ቀለበቶች የሚያደርጉ ሴቶች ሌላ የሚጫሙት ነገር ስለሌለ ቀለበቶቹ በግልፅ ይታያሉ።

በኮኮሣ ያገቡ ሴቶች ጌጦች ባብዛኛው በማንኛውም ሃይማኖት/እምነት/ ተከታይ ሴቶች የሚያደርጓቸው ናቸው። ከእስልምና ውጭ የሆኑ ሴቶች ከእነዚህ ጌጦች በመጠኑ ልዩነት ያለው በራሳቸው ላይ የሚያደርጓቸው ጌጦች ናቸው። እነዚህ ሴቶች ፀጉራቸውን በሻሽ

አይሸፍኑም። ፀጉራቸውን በቀጫጭኑ ወደታች አይነት ስራ ይሰራሉ። የፀጉራቸው ጫፍም አይጎነጎንም።



ፎቶ ቁ.11 የኮኮሳ ሙስሊምና ክርስቲያን ሴቶች አለባበስና አጊያጌጥ

በዚህ ክፍል በገደብ ሀሳሳ ወረዳ የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ምን እንደሚመስሉ እንዲሁም የሰሪዎቹ ዳራ በቅደም ተከተል ይቀርባሉ።

4.3 የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ በገደብ ሀሳሳ

በዚህ ክፍል በገደብ ሀሳሳ ወረዳ የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ምን እንደሚመስሉና የሰሪዎቹ ዳራ በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

4.3.1 የሴቶች አልባሳትና ሰሪዎቻቸው በገደብ ሀሳሳ

ይህ ወረዳ የባህላዊውን ልብስና ጌጥ በዘመናዊ መንገድ በመስራትና ገበያ በማቅረብ ይታወቃል፡፡ በወረዳው እነዚህን አልባሳትና ጌጣጌጡን በመስራትና በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ ሚና ያላቸው የተወሰኑ ግለሰቦች ይገኛሉ፤ እነዚህም ሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች በገጠር ቀበሌዎች ይኖሩ የነበሩ፣ ይህንን ስራ ከጀመሩ በኋላ ግን ቤት ሰርተውና ተከራይተው በከተማ መኖር የጀመሩ ናቸው፡፡ ባህሉን በዘመናዊ መንገድ በማስተዋወቅ የሚሰሩ ሰዎች በሁለት ጎራ ይከፈላሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ በግል የሚሰሩት ሲሆኑ ሌሎቹ በማህበር ተደራጅተው የሚሰሩ ናቸው፡፡

4.3.1.1 በግል የሚሰሩ አልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎች

አልባሳትና ጌጣጌጦቹን በመስራት ላይ የተሰማሩት ጥቂት ናቸው፡፡ በመስክ ቆይታዬ የተገለጸልኝ በአካባቢው ሶስት የግል ሰሪዎች እንዳሉ ነበር፡፡ ነገር ግን አንዷ ወደባሌ በመሄዳቸው ያገኘኋቸው ሁለቱን ብቻ ነው፡፡

ወ/ሮ አንዮ በቲሳ በሀሳሳ የዘመናዊውን አሰራር በማስተዋወቅ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙ ናቸው፡፡ አንዮ ይህንን ስራ የጀመሩት በደርግ ዘመነ መንግስት መሬት በተወረሰባቸው ወቅት ኑሮን ለማሸነፍ ሲሉ ነበር፡፡ «ደርግ መሬት ሲወስድብን ምን ልስራ በሚል አስቤ እናቴም እቤት ውስጥ አስተማረችኝ እኔም እነዚህን ልጆች የማሳድግበት በማለት ተማርኩ፡፡» (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 2፣2000 ዓ.ም) ወይዘሮዋ ችግርን ለመፍታት በማሰብ ባደረጉት ጥረት የጥበቡ ባለቤት ለመሆን እንደቻሉ ነው የሚናገሩት፡፡ ትምህርቱንና ልምዱን ያገኙት በባህላዊ መንገድ ነው፡፡ ከእናት ወደ ልጅ በሆነው የፍላጎት ውርስ ዛሬ እሳቸውም ልጆቻቸውን ያስለጥናሉ፡፡

ከእናታቸው በማየት የቀሰሙትን ልምድና የግል ችሎታቸው ታክሎበት ዛሬ ላለው የቤተሰባቸው የኑሮ ደረጃ እንዲደርሱ አድርጓቸዋል፡፡ በመስክ ቆይታዬ ቤተሰቡ ከትንሽ እስከትልቅ በጌጣጌጥ ስራ ተጠምዶ ተመልክቻለሁ፡፡ ትዳር የያዙ ልጆቻቸው ሳይቀሩ በእናታቸው ቤት በመገኘት የጌጣጌጡን ስራ ይሰሩ ነበር፡፡ በዚህ ቤተሰብ ለገበያ የሚቀርቡ

ቁሶችና አልባሳት ከልብስ ዘር ኮቤ፣ ቦንኮ፣ ቆሎ፣ ሃርሰማ፣ ቂጣ፣ ጉፍታ ከጌጣጌጥ ዘር ጨሌ አዳ፣ ፎሮረ፣ የአንገት ጌጥ እና ቢቶ ናቸው።

4.3.1.2 በማህበር የሚሰሩ የጌጣጌጥና የአልባሳት ሰሪዎች

በወረዳው አንድ በአስተዳደርና በባህልና ቱሪዝም እንዲሁም በሴቶች ጉዳይ በኩል የተቋቋመ ማህበር አለ። ይህ ማህበር ስራውን የጀመረው በ1999 ዓ.ም. ነው። ማህበሩ16 ሴቶችን በአባልነት የያዘ ሲሆን (Faayitu Oromiyaa) ፋይቱ ኦሮሚያ በመባል ይታወቃል።

በማህበሩ በኩል እንደግሎቹ ሁሉ ለገበያ የሚቀርቡ አልባሳትና ጌጣጌጦች አሉ። የማህበሩ መቋቋም ሁለት አላማዎች አሉት። የመጀመሪያው ሴቶቹ እራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ማስተዳደር እንዲችሉ ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ተዘንግቶና ጠፍቶ የነበረውን ባህል በዘመናዊ መንገድ እንዲያስተዋውቁ በማሰብ ነው። እህተጊዮርጊስ ቢራቱ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 28፣2000ዓ.ም)

ወ/ሮ አያንቱ የ "ፋይቱ ኦሮሚያ" ማህበር ኃላፊ ናቸው። እኚህ ሴት ለብዙ አመታት በግላቸው ሲሰሩ የነበሩ ናቸው። ከ10 ዓመት በላይ በዚህ ሙያ ውስጥ የቆዩት ወይዘሮዋ ቤተሰቦቻቸው ባህሉን ለመጠበቅ ያደርጉት የነበረው ጥረት እሳቸውንም ለዚህ ስራ አነሳስቷቸው አሁን በቤታቸው በባህላዊ መንገድ በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት በማህበሩ አባላት ለገበያ የሚቀርቡት ቁሶች ከልብስ ቦንኮ፣ ቦኬ፣ ቆሎ፣ ቂጣ፣ ሀርሰማ እና ጉፍታ ናቸው። በጌጣጌጥ በኩል ደግሞ "ቆሪ"፣ ቦራቲ፣ ቡቄ ኡርጎ፣ ጡንጦ ይገኙበታል።

4.3.2 ለገበያ የሚቀርቡ ቁሶችና መስሪያዎቻቸው

4.3.2.1 አልባሳት

በግልም ሆነ በማህበር የሚሰሩ የሀሳሳ አልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎች አብዛኛው ስራቸው ቅርፅ ማስያዝና ማስዋብ ነው። አልባሳቱ በቅድሚያ በልብስ ሰፊዎች ተፈላጊውን ቅርፅ ይዘው ከተሰፉ በኋላ የመጨረሻውን ስራ የሚሰሩት እነሱ ናቸው። አልባሳቱ ስማቸው አንድ ይሁን እንጂ በኮኮሳው የአልባሳት ክፍል ካነሳናቸው ጋር ልዩነት አላቸው። እነዚህንም ቀጥለን እንመለከታቸዋለን።

ሀ. ጉፍታ(Guftaa)

ጉፍታ በሶስት ማዕዘን ቅርፅ የሚዘጋጅና ለሻሽነት የሚውል ነው።ለመስሪያ የሚመረጠው ቀለምም ደማቅ ቡኒ፣ቢጫ አልያም ደብዛዛ ቡናማ ሊሆን ይችላል።

ፎቶ ቁ. 12 በሀሳሳ በዘመናዊ መንገድ የሚሰራዉ ጉፍታ

ለ. ቦንኮ(Bonkoo)

ለዚህ የልብስ አይነት መስሪያ በብዛት ቡኒ ወይም ቢጫ ቀለማት ያሉት ብትን ጨርቅ ጨሌዎችና ዶቃዎች ያስፈልጋሉ። ብትኑ ጨርቅ በሚፈለገው ቅርፅ በልብስ ሰፊ እንዲሰፋ ይደረጋል። ከዚያም የተለያዩ ጌጦች ይደረጉበታል። ቦንኮ በካባ ቅርፅ የሚሰፋ የባህላዊውን የኮኮሣውን የቆዳ ቦንኮ በሚያህል ርዝመት የሚዘጋጅ ነው። ትከሻ ላይ በሚውለው በላይኛው ጫፍ የጥበብ ቅርፅ በሰማያዊና ነጭ አልያም ቀይ ቀለማት ባላቸው ትንንሽ ጨሌዎች ጌጥ ይሰራበታል። ጌጡ በፓራሹት ክር(ጅማት) ክር ለብቻው ተሰርቶ አላዩ ላይ የሚሰፋበት ነው። በዚያው የተገለበጠ ሶስት ጎን ቅርፅ ያለው እንዲሆን ተቆርጦ ይዘጋጃል። ቀጥሎ ከፍ ባሉ ጨሌዎች በክር ተደርጎ ዘርፍ ይሰራበታል። ከስርም እንዲሁ በተቆራረጠው መሃል መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ከፍ ያሉት ጨሌዎች ሁለት ረድፍ ሆነው ተሰርተው በአንድ ተሰፍተው ይንጠለጠሉበታል። አልፎ አልፎ ደግሞ ወደታች ሶስት ማዕዘን ቅርፅ በሚሰራው የጨርቁ ክፍል ላይ አንዳንድ ዶቃ ይሰፋበታል። ይህንንም ሰርቶ ለመጨረስ ሶስት ቀን ያህል ይፈጃል። አያንቱ ዱቤ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 1፣2000 ዓ.ም)።

ፎቶ ቁ. 13 ሀሳሳ የሚሰራዉ ቦንኮ

ሐ. **ቆሎ**(Qoloo)

ቆሎ በአርሲ ማህበረሰብ በሚሰጠው ትርጉም የቀለማትና የጨርቅ አይነቱን ይዞ በሀሳሳ አይገኝም። እዚህ የሚገኘው የቆሎ አይነት ከቦንኮው ጋር አንድ አይነት ቀለም ያለው የጨርቅ ዘር ነው። ይህ ልብስ እንደጉርድ ሆኖ መሃል ላይ ውሃ ሰማያዊና ነጭ ቀለም ባላቸው ትልልቅ ጨሌዎች ዘርፍ ይሰራበታል። ከስር የሚይዘው ቅርፅ እንደቦንኮ ሆኖ ዶቃዎች ሲቀሩ ባለሁለት የጨሌ ዘርፉ ግን ይሰራበታል።

ፎቶ ቁ. 14 ሀሳሳ የሚሰራው ቆሎ

መ. ቄጣ (Qeexxaa)

ቄጣ የቀሚስ አይነት ሆኖ ቁመቱ አጠር የሚል ነው። በቀሚስ ቅርፅ ይሰፋል። ከስር የኮንኮና ቆሎ አይነት ቅርፅ ተበጅቶለት ሁለት ሁለት ዘርፍ ያለው ጌጥ ይደረግበታል። ጌጡ ዘርፍ እንዲኖረው የሚደረገው ክር ውስጥ በማስገባት ነው።

ሠ. ሃርሰማ (Harsamaa)

ይህ የልብስ አይነት እንደ ቄጣ ተደርጎ የሚሰፋ ነው። መሠረታዊ ልዩነታቸው የርዝመት ሲሆን ሃርሰማ እስከጉልበት በሚደርስ ርዝመት ይዘጋጃል። የጌጡ ሁኔታም ከቄጣ ጋር ያመሳስለዋል።

ፎቶ ቁ.15 ሀሳሳ የሚሰራው ሃርሰማ

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ሰርቶ ለመጨረስ ከአንድ ሳምንት በላይ ጊዜ እንደሚወስድ ወ/ሮ ራሚያ አማን (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 23፣2000 ዓ.ም) ነግረውኛል።

4.3.2.2 ጌጣጌጦች

በዚህ የጌጣጌጥ ክፍል የሚካተቱት ሁለት አይነት ጌጦች ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ከአልባሳቱ ጋር የሚሄዱት ሲሆኑ ሌሎቹ በእጅ የሚያዙ ናቸው።

ሀ. ከአልባሳቱ ጋር የሚሄዱ ጌጦች

ከአልባሳቱ ጋ ተያይዘው የሚሰፉ ወይም ለብቻቸው ተሰርተው አብረው የሚደረጉ ጌጦች አሉ። እነዚህ ጌጦች በራስ፣ አንገትና እጅ ላይ የሚደረጉ ናቸው። በራስ ላይ የሚደረገው ጌጥ

ጨሌ አደ ጀሌ ይባላል፡፡ ይህም ከጨሌ የሚዘጋጅ ሲሆን ለቦንኮ በሚሰራው ቅርፅ ጥበብ ከተሰራበት በኋላ ጉፍታው ላይ ይሰፋበታል፡፡ ሌላው እዚሁ ራስ ላይ የሚደረግ ጌጥ ፎሮረ የሚባለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሻሹ ሲታሰር በጆሮ ኋላ እንዲንጠለጠል ተደርጎ የሚሰራ የተለያዩ ትንንሽ ጨሌዎች ህብር ነው፡፡

ጨሌ አዳ (Calle Addaa) ፡- ይህ ጌጥ በግንባር ላይ የሚደረግ ቅርፁ የተገለበጠ ሶስት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሲሆን ትንንሽ ጨሌዎች በተለያዩ ቀለማት ተሰባጥረው በክር ከተሰሩ በኋላ ግንባር ላይ የሚደረግ ነው፡፡

ወደ አንገት ዝቅ ስንል የምናገኘው ጌጥ ደግሞ ጨሌ ሁዶ (Callee Hudhoo) ይባላል፡፡ ይህ ቀጭን አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለውና በአንገት ላይ የሚጣበቅ ነው፡፡ ለዚህ የሚውሉት ቁሶችም ትንንሽ ጨሌዎች በተለያዩ ቀለማት፣ ጅማት ክር መርፌ ናቸው፡፡ ክሩ በመርፌ ከተደረገ በኋላ ጨሌዎቹ እንደአስፈላጊነታቸው በተለያዩ ቀለማት በክሩ እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ዲዛይን ከወጣለት በኋላ ለጌጥነት ይውላል፡፡

ከነዚህ ልብሶች ጋር የሚደረገው ሌላው ጌጥ ቢቶ(bitoo) ነው፡፡ ቢቶ በባህላዊው መንገድ ከብረት ተሰርቶ ግራ እጅ ላይ የሚደረግ ጌጥ ነው፡፡ ይህ አሁን በጨሌ አማካይነት የሚሰራ ጨሌ የተባለ ጌጥ ሆኗል፤ቢቶም ይሉታል፡፡(ቁራ ከድር ሚያዚያ 2፤2000 ዓ.ም)

በዚህ ወረዳ የሚገኙት ጌጦች ሁለት አይነት ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ከአልባሳቱ ጋር የሚደረጉ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ ደግሞ በእጅ የሚያዙ ናቸው፡፡ ከአልባሳቱ ጋር በተለያዩ አካላት ላይ የሚደረጉት ጌጦች እስካሁን ያየናቸው ናቸው፡፡ ቀጥሎ በእጅ የሚያዙ ጌጦች ቀርበዋል፡፡

ለ. በእጅ የሚያዙ ጌጦች

በዚህ ስር የሚገኙት ጌጦች በአርሲ ማህበረሰብ ዘንድ ከጌጥነታቸው ይልቅ መገልገያ ቁስነታቸው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ይህንንም ለማመልከት የቀደመና የአሁን አገልግሎታቸውን እንመከታለን፡፡

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት	አገልግሎት/የቀደመ	የዕቃው አይነት	አገልግሎት/የአሁን	ዋጋ
1	(Qorii) ቆሪ መስሪያ (እንጨት፣ ዘንባባ፣)	ለመንገድ ለሚሆን ስንቅ፣ለእንግዳ ገንፎ ማቅረቢያ፣ ባህላዊ ዕቃ የሚከፈት	ቆሪ - እንጨት ዘንባባ የቆዳ ማንጠልጠያ የተለያዩ ጨሌዎች	በሰርግና በተለያዩ መድረኮች ለጌጥነት በእጅ የሚያዝ የሚከፈትና የማይከፈት፣	ባህላዊ ው 80 ባለ ጌጥ 300-350
2	(Boraati) ቦራቲ	ሴቶች ከቤተሰብ ለሰርጋቸው ቀን የሚሰጣቸው የእንጨት ትራስ ብዙ ጨሌ የለውም	ቦራቲ	በሰርግና በተለያዩ መድረኮች ለጌጥነት የሚያዝ በጨሌዎች ጌጥ ያማረ	ከ100-150 ብር
3	(xunxoo) ጡንጦ (ከፍየል ቀንድ፣ ከቅልና ከዘንባባ)	የሚሰራ ለወተት ማስቀመጫነት የሚውሉ የልጃገረዶች የጋብቻ ቀን ስንቅ/ለእንግዳ የሚቀርብ	ከጡንጦ	የሚሰራበት አንድ ሆኖ በተለያዩ ዲዛይኖች ከጨሌ ጌጥ የሚሰራበት በእጅ የሚያዝ	ከ80-100 ባለ ጌጣጌጥ እስከ 200 ብር
4	ቡቄ ኡርጎ (Byqqee Urgoo)	መጠኑ ከጡንጦ ያንሰ ከቅል፣ የፍየል ቀንድና ዘንባባ ለማስቀመጫነት የሚሰራ የቀለጠ ቅቤና የሚሸቱ ቅጠሎች ተቀላቅለው ለሽቶነት የሚያገለግል ፈሳሽ መያዣ	ቡቄ ኡርጎ	መጠኑ ከጡንጦ ያነሰ የፍየል ቀንድ፣ ቅልና፣ ዘንባባ ለመስሪያነት የሚያገለግሉ ናቸው። በተለያዩ ጨሌዎች ዘርፍና ተለጣፊ ጌጥ ተሰርቶበት በእጅ የሚያዝ	እስከ150 ድረስ ይሸጣል ጌጥ ያልበዛበት እስከ 50ብር ይሸጣል

4.3.3 የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ይዞታና የህዝቡ አስተያየት

በሀሳሳ ኑሮአቸውን ለማሻሻልና ባህሉንም በማሳደግ ረገድ ሴቶቹ እየሰሩት ያለውን ስራ በተመለከተ በነሱም ሆነ በሌሎች የማህበረሰቡ ክፍሎች የሚሰጡ አስተያየቶች አሉ። ቀደም ሲል እንዳየነው የቀደመ ባህላዊ አገልግሎታቸውን ትተው ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ቁሶች አሉ። ይህንን በሚመለከት የማህበሩ አባላትም ሆኑ በግል የሚሰሩት የሚሰጡት ሀሳብ አንድ ነው። ስሙ መኖሩ በራሱ ባህሉን ማሳደግ ነው ይላሉ።"eeyye hinguddata aadaa duritii

jechuu.kan bakka durii bu'ee dalagamaa jira jechuu dha.amma dur durbillee Yoo heerumte kunnin hafaa hin jiru.aadaa dha jechuu dha."መካ ያመታ(ቃለመጠይቅ ፤30 መጋቢ.ት ፤2000) " ... ባህሉ የድሮው ነው፡፡ የድሮውን ተክቶ እየሰራ ነው፡፡ ድሮ ሴት ልጅ ስትዳር የሚደረገው ነገር ሁሉ አለ፤ባህል ነው ማለት ነው፡፡»

በግላቸው አልባሳቱን በማስጌጥና ጌጦችንም በማዘጋጀት የሚታወቁት መረጃ አቀባይ አሁንም ቢሆን ባህሉን የጠበቀ ነው የሚል ሃሳብ አላቸው፡፡፡፡

ወይዘሮ አንዮ የተባሉት ሌላዋ የግል አልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪ ይህንን የሚመለከቱት ከለውጥና መሻሻል ጋር ነው፡፡ "ከበፊቱ ባህል ተነስቶ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ የተለያየ ቡታም ይወሰዳል ቦንኮ ከቶሎ በላይ ይለበሳል፤ ከቶሎ በታች ጉርድ ይለበሳል፤ ይህ ኬሰሴኒ ይባል ነበር፡፡ ድሮ ፤ቄጣም ይባል ነበር፡፡ ያ ቄጣ አሁን ጨርቅ ሆኗል፡፡ የድሮ ባህል አልቀረም፡፡" (ቃለመጠይቅ፤ሚያዚያ 2፤2000) ይላሉ፡፡

እንደመረጃ አቀባዮቹ ገለፃ በተገኘው መንገድ ባህልን ለማሳደግ መጣር አንደኛ ህይወትን ለመለወጥ ሁለተኛ ባህልን እንዳይጠፋ ለማድረግ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ የቁሶቹ አገልግሎት መለወጥ (shift) ማድረግ ከመጥፋታቸው ጋር ሲነፃፀር ምንም ጉዳት የለውም፡፡ ዋናው ነገር ቁሶቹ በስማቸው መኖራቸው ነው የሚል ሃሳብ አላቸው፡፡

በአካባቢው የሚኖሩ የማህበረሰብ አባላትም ይህንን ሃሳብ ይደግፉታል፡፡ ነገር ግን በተለይ የአገልግሎት ለውጥ በተደረገባቸው ቁሶች ላይ ልክ አይደሉም የሚሉ አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ አቶ አብዱል ቃድር ናቸው፡፡ ሴቶቹ/ሰሪዎቹ ባህሉን ለማሳደግ የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ቢሆንም አንዳንድ ችግሮች ያሉባቸው መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

> ይኼ ተሻሽሎ ተጨምሮ የሚሰሩ አሉ፡፡ አሁን በዚህ ማህበር ውስጥ እንዲያስተካክሉ እንዲያሻሽሉ የምንፈልገው ነገር አለ፡፡ ቆሪ የሚሉት አለ፡፡ የሚበሉበት፤ ገንፎ፤ ሚጨራ ፊኒን ወዘተ. የሚበላበት አለ፡፡ ይህንን ቆሪ አሁን አካሉን ሁሉ በጨሌ ሸፍነው ጥለትም አለው፡፡ የማይከፈት ሆኖ እየተሰራ ነው፡ አለመከፈቱ እንዳይከፈት መደረጉ ማሳመር አይደለም፡፡ ክዳኑ ተዘግቶ ተመልሶ አለመከፈቱ በእውነት የሚበሉበትን ማጣት ነው፡፡አብዱል ቃድር ገልሞ (ቃለመጠይቅ፤መጋቢ.ት 28፤2000 ዓ.ም)

የቀረበው ሃሳብ ቁሱ ባህላዊነቱን እያጣ ነው ከሚል ስሜት የመነጨ ነው፡፡ ማሳመሩና ማስጌጡ ተገቢ ቢሆንም በባህሉ ውስጥ የሌለን ነገር ማምጣት ለመጪው ትውልድ ብዥታን መፍጠር ይሆናል የሚል መልእክትም አለው፡፡ የሰሪዎች ጥበባዊ ልምድ በየጊዜው መሻሻል

መለወጥን ያመለክታል የሚሉት ደግሞ ሌላው መረጃ አቀባይ «waan dur hin jirre tokko uumuuf oromoon danadetti isaa mullisuu fi fooyessuun nama gammachiisa; bifa duritiin garuu hin fakkatu.» ሀጂ አደም ሀጂ አምዳ (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 30,2000) (የእጅ ሰው በልምድ የተማረውን አውቆ አዲስ ነገር በመፍጠር በመሳየቱ ረገድ ያስደስታል። ነገር ግን አሁን እንደምናየው ከድሮው የሚቃረን ነገር ያለም ይመስለኛል።)ይላሉ፡፡

ሀጂ አደም ባለቤታቸው እየሰሩ በሚያቀርቡት የጥበብ ውጤት ሴት ልጅ ስፌት ከመስፋት አልፋ እንዲህ የተወሳሰበ የጥበብ ደረጃ ላይ መድረሷን ያደንቃሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አንዳንዱ ነገር ከባህላዊው ጋር የሚጣረስ ሁኔታ እየታየበት ነው የሚል ፍራቻ አላቸው።

በሀሳሳ የአልባሳቱና ጌጣጌጡ ሻጮች ቁሶቹን በሁለት አይነት መንገድ ለገበያ ያቀርባሉ። የመጀመሪያዎቹ በገበያ ዕለት ገበያ ወጥተው የሚሸጡት ሲሆኑ ሌሎቹ በእቤታቸው በትዕዛዝ የሚሰሯቸውና የሚሸጧቸው ናቸው።በመስክ ቆይታዬ በአደረግኩት ምልከታ ለገበያ የሚቀርቡት በእጅ የሚያዙ ባህላዊ እቃዎች ናቸው። እነዚህም ቆረ፣ ቡቄ ኡርጎ፣ (ቡቹመ) ወዘተ. የሚባሉት ሲሆኑ ብዙም ጌጥ አይደረግባቸውም። እነዚህን የሚገዙትም ለከተማዋ በቅርበት ላይ የሚገኙ የአጎራባች ቀበሌ ነዋሪዎች ናቸው። በዋጋ ረገድም ከ50-180 ብር ይደርሳሉ። አልባሳቱና ሌሎቹ ጌጦች ገበያ ወጥተው አይሸጡም።

በዚያኑ ወቅት የአልባሳቱና ጌጣጌጡ ወጥተው ለገበያ አለመቅረብ ምክንያት መረጃ አቀባዩ ወ/ሮ ቄራ ከድር እንዲህ ብለውኛል "እነዚያ ከቤት አይወጡም፤ እነዚያን ማግኘት የፈለገ እቤት መጥቶ ይገዛል ወይም ይከራያል።"(ቃለመጠይቅ ሚያዚያ2፣2000 ዓ.ም)

አልባሳቱም ሆኑ ጌጣጌጡ በአብዛኛው የሚዘጋጁት በትዕዛዝ ስለሆነ እንደባህላዊዎቹ ቁሶች ቀድመው ተሰርተው ለገበያ አይቀርቡም። በገበያ ቀርበው ከሚሸጡት ጋር ሲነፃፀሩ የሚያወጡት ዋጋ ከፍተኛ ነው። እነዚህን ቁሶች በብዛት የሚገዙትም ሆኑ የሚያዙት የከተማው ወይም የገጠሩ ሰዎች ሳይሆኑ ከሌላ አካባቢ የሚመጡ ናቸው። "Namonni nurraa bitu. Kadhunfaan bituullee hin jira.ka warri waajjiraa batalayyii nurraa bita. Yoo badhaasa ta'ee waan adda addaa yoo itti dhufteellee... nurraa bitan."አያንቱ ዱቤ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 1፣2000 ዓ.ም) በግልም ሆነ በመንግስት መስሪያ ቤቶች እነዚህን አልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎቹ እንዲያዘጋጁ ይጠየቃሉ፤ ይገዟቸዋልም።

እነዚህ አልባሳትና ጌጣጌጡ ተሟልተው ለሽያጭ ወይም ለኪራይ ይቀርባሉ። የኪራዩ ሁኔታ እንደዝግጅቱ ሁኔታና እንደሚወስደው ጊዜ ይለያያል። ለባዛር ከሆነ 50 ብር፣ ለሠርግ ከሆነ ደግሞ 100 ብር ድረስ እንደሆነ ወ/ሮ አያንቱ ነግረውኛል። በትዕዛዝ አማልቶ ለመግዛት

ደግሞ እስከ 1200 እና ከዚያ በላይ ይጠይቃል። ራሚያ አማን (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 29፣2000ዓ.ም)

በእቤት ውስጥ ተሰርተው የሚሸጡት አልባሳትና ጌጣጌጥ በዋጋ ረገድ ከፍተኛ ናቸው። ይህ ሁኔታ በገዢዎቹ በኩል ምን ቦታ እንደሚሰጠው በግልም ሆነ በማህበሩ የሚሸጡት የሚሉት አላቸው። በገዢዎች በኩል የሚመጣ ምንም የቅሬታ ሃሳብ የለም። ባህላችንን የሚያንፀባርቁ ቁሶችን ማግኘታችን በራሱ በገንዘብ የሚቆጠር በመሆኑ በርቱ ይሉናል። የሚል መልስ ሰጥተውኛል። የአካባቢው ሰውም ቢሆን ሁሉንም አሟልቶ መግዛት ባይችል ለመከራየት የሚችል በመሆኑ በዋጋ ረገድ እምብዛም ችግር እንደሌለባቸው ይናገራሉ።

ባጠቃላይ በሀሳሳ አልባሳቱና ጌጣጌጦቹን የሚሰሩ ሰዎች የሚያዘጋጁት በትዕዛዝ በመሆኑ እንደተፈለገው መጠንና ብዛት ያቀርባሉ። የአልባሳቱም ሆነ የጌጣጌጦቹ ሰያሜ ባብዛኛው ባህላዊውን መንገድ የተከተለ ነው። ቁጣ የሚባለው የልብስ አይነት በቁመት አጠር ያለ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ይህን የሚለብሱት ወጣቶች ናቸው። ወጣቶችም ይለብሱታል። ሃርሰማ የተባለው ደግሞ የሚለብሱት ወጣቶች ሲሆኑ፣ በትልልቅ እናቶች ብዙም አይዘወተርም። እነዚህ አልባሳት ለህፃናት በሚሆን መጠንም ተሰርተው ለገበያ ይቀርባሉ።

4.3.4 የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰራተኞች የለመዳ ሂደትና የጥበቡ እድገት

በማህበርም ሆነ በግል ከሚሰሩት ዘመናዊ የቴክኒክ ትምህርትን የተማረ የለም። በልምድ ብዛት ዘወትር እያሻሻሉ ግን የተለያዩ ዲዛይኖችን ይፈጥራሉ።

በአሁኑ ወቅት በሀሳሳ ከሚታወቀው የአልባሳትና ጌጣጌጦች ረዘም ያለ ልምድ ያላቸው የማህበሩ ሃላፊ አሉ። እሳቸውም ይህንን ጌጥ የመስራትና ልብስ የማስጌጥ ስራ እንዴት እንደተማሩት ሲገልፁ፡- “ይህን ሙያ እኔ እራሴ ሳገባ ቦኬና ቁጣ አድርገው የሚያገቡትን ደርሼባቸዋለሁ። ከእሱ አይቼ እናቴና አባቴም እኔን ሲድሩኝ ባህሉን ለመጠበቅ ያደርጉ የነበረውን ጥረት በማየት የቆዳውን አይቼ እራሴው መስራት ጀመርኩ።” አያንቱ ዱቤ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 1፣2000 ዓ.ም) ሙያውን ከቤተሰባቸው በማየት የተማሩት እኚሁ ሴት በአሁኑ ወቅት ሙያውን በማስተማር የታወቁ ናቸው። አንድ ሰው ወደ ማህበሩ መግባት ሲፈልግ፣ ይመዘገብና የሚሰሩትን በማየት እንዲማር ያደርጉታል። በመስክ ቆይታም አምስት ሰዎች ለልምምድ ተመዝግበው በስልጠና ላይ ነበሩ።

ሙያው እያደር እየተሻሻለና እያደገ መሆኑን ነው መረጃ አቀባዮች የሚገልፁት። ከጥቂት አመታት በፊት ወ/ሮ አያንቱ ለልጆቻቸው ያሳዩአቸው የነበረው ዲዛይን ስራ አሁን የተወሳሰበና

ጥልቅ የጥበብ ውጤት ላይ ደርሷል፡፡ "እናታችን ድሮ እኛን አስተምራን ነበር፡፡ አሁን ግን እኛ መልሰን እያስተማርናት ነው፡፡" ትላለች ልጃቸው ወ/ሪት ሞሚና ደማ፡፡

ዲዛይኖቹን የሚያገኙባቸውንና የሚያቀናጁበትን መንገድ ሰሪዎቹ በተለያየ መንገድ ይገልጹታል፡፡ ልክ እንደቀለማቱ ሁሉ ዲዛይኖቹም በሰሪዎቹ የሙከራ ስራ አልያም በአሰሪዎች ትዕዛዝ የሚከናወን ነው፡፡ "በፊት ጀምሬ የሚባለውን በሶስት አይነት ቀለም ስሰራው አይን ይስባል፡፡ ያምራል፡፡ ዲዛይኑንም በዚያን ጊዜ ስለማውቅ በዚህ አይነት ሞክሬ ሳይ ይህ አንድ ላይ ቢደረግ አይን ይስባል በማለት መስራት ጀመርኩ፡፡" ወ/ሮ አያንቱ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 1፣2000 ዓ.ም) የዲዛይኑ ማማርና መሻሻል ከልምድ እና ከሙከራ የሚመጣ መሆኑን የቀረበው ሀሳብ ያመለክታል፡፡ ይህንኑ የዲዛይን ስራ በተመለከተ የሚገልፁት ሌላዋ መረጃ አቀባይ እንዲህ ይላሉ፡፡ "በአእምሮኣችን ውስጥ የመጣልንንም አዳዲስ ዲዛይን ልጆች ትምህርት እንደሚገባቸው ሁሉ አስበን ይሄ ይሁን ይህ ደግሞ ነገ ቢሰራ ብለን አሻሽለን መስራት ችለናል፡፡"አንዮ በቲሳ (ቃለመጠይቅ ሚያዚያ 2፣2000 ዓ.ም)

ለአልባሳቱ በይበልጥ ደግሞ ለጌጣጌጦቹ የሚዘጋጁ ዲዛይኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል እየታየባቸው ነው፡ ይህንንም መረጃ አቀባዮቹ በዘመናዊ ትምህርት ሳይሆን በልምድ ያገኙት መሆኑን ነው የሚናገሩት፡፡ በተጨማሪም ሙያው ከእናት ወደ ልጆች እየተላለፈ ያለበት ሁኔታ መኖሩ ልጆቹ በሚያደርጉት ጥረትም መሻሻሉ በየጊዜው እየተስተዋለ ያለ ጉዳይ ነው፡፡

እነዚህን ዲዛይኖች ወደባህሉ ማምጣቱ ባህሉን ከማሳደግ አንፃር ምንም አሉታዊ ተፅእኖ እንደሌለውም ሰሪዎቹ ይናገራሉ፡፡ የባህሉ እቃ በስሙና በቅርፁ ያለ በመሆኑ በተለያዩ ዲዛይኖችና ቀለማት ተሰርቶ መቅረቡ መልካም ነው፡፡

የድሮው ይምጣ ማለቱ በአፍ እንጂ በተግባር ስለሚከብድ እነዚህ ቁሶች በጌጥነት መጥተው በተለያየ ዲዛይን መሰራታቸው ተገቢነት አለው፡፡የሚሉት ደግሞ አቶ ቦንሰሞ ናቸው፡፡ በግልም ሆነ በማህበር ተደራጅተው በልዩ ልዩ ጌጦች ያማሩ ልብሶችና ጌጦችን የሚያቀርቡት የዕደ ጥበብ ሰዎች ከላይ እንደተገለጸውም የጥበብ ችሎታቸው በየጊዜው እየተሻሻለ ነው፡፡ ከቤተሰቦቻቸውና ከልምድ የያዙትን እውቀት መሠረት አድርገው የተሻለ ለማድረግ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ለአልባሳቱና ጌጣጌጡ የሚያገለግሉት ቁሶች(ጨሌ፣ብትን የፋብሪካ ጨርቅ፣መስፊያ ክር ወዘተ) ዘመናዊ ቢሆኑም የአሰራር ሂደታቸው ባህላዊ ነው፡፡ የጥበቡ ውርስ በቤተሰብ ውስጥ ከእናት ወደ ልጆች የሚደረግ ነው፡፡ ወ/ሮ አያንቱ ልጆቻቸው ይህንን ጥበብ እንዲማሩ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ባህል በመሆኑ እንዲቀጥል የበኩላቸውን ማድረግ እንዳለባቸው እንደሚነግሯቸው ይገልጻሉ፡፡ "የተወሰኑት ወደውት የተሰማሩበት በመሆኑ

የሚማሩበትና የሚበሉበት በመሆኑ እየሰሩ ነው፡፡ ከቤት ሳይወጡ እቤታቸው ሆነው መስራት እንዳለባቸው እነግራቸዋለሁ፡፡ ሰው ቋሚ ስላልሆነ አንዱ ካንዱ መማር አለበት፡፡ ባህላችን የኦሮሞ ባህል ነው፡ በሚል ልጆቼም እየሰሩ ይገኛሉ፡፡»አያንቱ ዱቤ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 1፣2000 ዓ.ም)

በምልከታዬም ወቅት የማህበሩንም ሆነ የግል ስራ ልጆቻቸው ከትልቅ እስከ ትንሽ እቤት ውስጥ ቁጭ ብለው ይሰሩ ነበር፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የማህበሩ የግል የመስሪያ ቦታ ስለሌለ ስልጠና መስጫውም ስራ መስሪያ ቦታውም የማህበሩ ተጠሪ መኖሪያ ቤት ነው፡፡ የማህበሩ አባላትም እንዲሁ በማይመቻቸው ሰዓት ልጆቻቸውን እየላኩ በዚህ ስራ እንዲሰማሩ ያደርጓቸዋል፡፡

4.4 የሴቶቹ አልባሳትና ጌጣጌጦች ከማንነት ጋር ያላቸው ቁርኝት

የአርሲ ህዝብ በመተጋገዝና በመረዳዳት የሚያምን በባህልና ቋንቋው የተሳሰረ ነው፡፡ የተቸገረን መርዳት፣ የታመመን መጠየቅና አቅም በፈቀደ መጠን ለወገኑ መድረስን 'arsooma' ይሉታል፡፡ አርሲ መሆን ማለት ነው፡፡ "Arsoomai-garagaarsa nama deegeef (hiyyoomef) idaan itti galeef, gumaa itti galeef, kkf godhamu ykn kenna kennamuudha." (2000፣ 13) አርሲ መሆን መረዳዳት ነው፡፡ ለተቸገረ/ለደኸየ፣ እዳ ላለበት፣ ጉማ ላለበት ወዘተ. የሚደረግ ወይም የሚሰጥ ስጦታ ነው፡፡

በድሮ ጊዜ አንድ እንግዳ አንድ አርሲ ቤት ከመጣ በቀላሉ አይሸኝም ነበር፡፡ እንደውም "Dhibbiin bishaan haa unnattu" ሼክ ከድር ሚያዚያ 29፣2000 ዓ.ም) 'ችግር/አስቸጋሪ ውሃ ትጎንጭ' የሚል በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደ አባባል አለ፡፡ እንግዳ ቤታቸው ሲመጣ አንድ ወይም ሁለት ከሆኑ ፍየል አርደው፣ ከዚያ በላይ ከሆኑ ደግሞ ጊደር አርደው ያስተናግዱ ነበር፡፡ እንግዳ ቤት ሲመጣ ወተት ይሰጠዋል ይላሉ ሼህ ከድር፡፡ በዚህን ጊዜም ለእንግድነት የመጣው ሰው ችግር የደረሰበት ከሆነ ላምና ጊደር ሰጥቶ ወተት አልቦ እንዲጠጣና እንዲመልስ ይደረግ እንደነበረ እኚሁ ሰው ይናገራሉ፡፡ አሁን ከሁኔታዎች መለዋወጥ ጋር እንደድሮው ባይሆንም ይህ ባህል በማህበረሰቡ ዘንድ ይስተዋላል፡፡

በአርሲዎች ዘንድ መተጋገዝና መረዳዳት በእንግድነት ተቀብሎ ማስተናገድ ብቻ አልነበረም፡፡ በአልባሳትና ጌጣጌጥ ስራ መተጋገዙ ነበር፡፡ አቶ ቦንሶሞ ድሮ ለገንዘብ ተብሎ አልባሳቱና ጌጣጌጡ በማይሰራበት ዘመን ያለውን ሁኔታ እንዲህ ይገልጹታል፡፡ ድሮ እንደዚህ

ያለውን ነገር አንዱ ለሌላው ያደርጋል። አንዷ የምታውቀውን ትሰራለች የሚያውቁትን ይለዋወጣሉ። የአልባሳቱ ስራ በባህላዊ በመተጋገዝና በመረዳዳት ላይ የተመሰረተ ነበር።

በማህበረሰቡ ዘንድ መተጋገዝና መረዳዳቱ እንዳለ ሆኖ በአልባሳትና በጌጣጌጦች ረገድ በሴቶች መካከል ልዩነት አለ። እነዚህ ልዩነቶች በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል።

> ... በሴቶች ላይ የምናየው ልዩነት ምንድነው? ድሃ እንኳን ሆና ጥንቁቅ/ባለሙያ አለች እራሷን የምትጠብቅ አለች። ሰውነታቸው ላይ እጥፍ እቃ/ጌጥ መኖሩ ሃብታምነታቸውን ያሳያል። ጌጡ ከላይዋ ላይ ማንፀባረቁ የእጅ የእግር የአንገት የሚያደርጉትን በማየት ይህቺ ሃብታም ነች ይህቺ አላት ማለት እንችላለን። በሴቶች ላይ የሚታየው ሁለተኛው ልዩነት ምንድነው ባለሙያ እና መሃይም(ግዴለሽ) በመሆን ነው። ቦንሰሞ ሚኤሶ(ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

አልባሳቱ ህዝቡ በብዛት ይጠቀምበት በነበረበት ወቅት በሴቶች መካከል ያለው ልዩነት ሁለት አይነት እንደነበር መረጃው ያመለክታል፤ ይህ አሁንም ያለ ነው።

በፊት በፊት በተለይ በኮኮሳ አካባቢ አንዲት ሴት በቅቤ ተነክሮ ባማረው ቦንኮዋ ላይ በጌጥ የተሸቆጠቆጠች ቦኬ ትደርብ ነበር። ይህ ደግሞ ሴቷ ሃብታም መሆኗን የሚያመለክት ነበር። በጌጥም በኩል በእጃቸውና በእግራቸው ጣቶች ላይ የሚያደርጓቸው ጌጦች ብዛት የሴቷን ማን መሆን በማየት ለመገመት የሚያስችሉ ነበሩ።

ይህ ሁኔታ አሁንም በኮኮሳ ይስተዋላል። ለሚሊኒየም አከባበር በከተማው አስተዳደር አማካይነት ወደ ከተማው የመጡት ሴቶች በባህላዊው ልብስና ጌጥ ልዩነት ይታይባቸው ነበር። ይህም ብቻ ሳይሆን በእጃቸውና በእግራቸው በአንገታቸውና በራሳቸው ላይ ያደረጓቸው ጌጦች የተለያየ ገፅታ ነበራቸው። ከሁሉም በላይ ግን በቦንኮዋቸው ድምቀት የነበረው ልዩነት ግልፅ የሆነ መልዕክት ነበረው፤ ብዙ ከብትና የወተት ላም ያለው ቅቤ እንደልብ ያገኛል ቅቤውም ለቦንኮው ውበት ይሰጥ ዘንድ በብዛት ይነከርበታል። የልዩነቱ ምስጢርም አንዱ ይህ ነው።

ለብሰው የሚወጡት ልብስና አድርገው የሚታዩባቸው ጌጦች የሚናገሩት መልዕክት አላቸው። "በአይን በማየት የአለባበስ ሁኔታቸው የኑሮ ሁኔታቸውን ይገልፃል። ባህሉን የማይከተሉና የሚከተሉትን በማየት መናገር ይቻላል። በጌጥ አይነትም ካየን ድሮ ሃብት ከሌላት መረጬ እንኳን አታደርግም። የእግር ቀለበት እግሯ ላይ አታደርግም። በቂ ሃብት ያለው ቤተሰብ ልጅ ከሆነች መረጬ፣ ሆቃ ታደርጋለች፤ ቀለበት በእግሯ ጣት ላይ ታደርጋለች።"አብደላ ሉገማ (ቃለመጠይቅ መጋቢት 30፣2000 ዓ.ም)

ይህ የሚያመለክተው በአይን በማየት የማንና ምንነት ጥያቄን ተመልካቹ ለራሱ ሊመልስ እንደሚችል ነው፡፡

እስካሁን ባየናቸው ጉዳዮች ላይ በአርሲ ማህበረሰብ የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ከማንነታቸው ጋር ያለውን ቁርኝት ለመመልከት ሞክረናል፡፡ ባጠቃላይ የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ከኮኮሳ ሴቶች ጋር ብቻ ሳይሆን ከኦሮሞ ህዝብ ማንነት ጋር ቁርኝት ያለው ነው፡፡ ህዝቡ በግብርናና ከብት እርባታ ተጠቃሚ ቢሆንም በከብቶች እርባታ የቀደመ ታሪክ ያለው ከብቶች በመሆኑ ለእርሻ አገልግሎት ከመዋል ሌላ ለብዙ ተግባራት ይውላሉ፡፡ ከነዚህ መሃከል ለአልባሳቱ እና ለጌጣጌጡ መስሪያነት የሚያገለግለው ጅማት ክር(ribuu) ይጠቀሳል፡፡

ከላይ በቀረቡትና በመሳሰሉት ምክንያቶች አንዲት የኮኮሳን የባህል ልብስ የለበሰችን ሴት በማየት ከየት ማህበረሰብ እንደወጣች መገንዘብ ያስችላል፡፡ በሀሳሳ ያለው ሁኔታ ከኮኮሳው ጋር ሲተያይ ከማህበረሰቡ ጋር ብዙም የሚያቆራኘው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በዘመናዊ መንገድ የተሰራውን ልብስ በውበቱ የተማረከና የተደሰተበት ማንኛውም ሰው ሊለብሰው ይችላል፡፡

4.5 የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ መቀነስ/መጥፋት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች

በነዚህ በሁለቱ ወረዳዎች የሃገር ሽማግሌዎችና በተለያዩ መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ መረጃ አቀባዮች አልባሳቱና ጌጣጌጡ የድሮ ይዞታቸውን ይዘው እንደማይገኙ ይናገራሉ፡፡ በአካባቢዎቹ በቀድሞ ጊዜ የነበሩ አሁን ግን ጭራሽ የጠፉ አልባሳት አሉ፡፡ በገደብ ሀሳሳ በቀድሞ ጊዜ የነበሩ አሁንም የሚስተዋሉት ጭራሽ የማይገኙበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

ባህላዊ አልባሳቱና ጌጣጌጡ የጠፉባቸው ወይም ቁጥራቸው የቀነሰበትን ምክንያት በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ተፈጥሮአዊ ሲሆን ሁለተኛው ሰው ሰራሽ ምክንያት ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ ምክንያት የሚባለው ከአየር ንብረት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

> ዝናብ ጠፋ፤ መሬት ደረቀ፤ ይህ ሁሉ ጠፍቶ የምንቀባው ቅቤ ጠፋ ድሮ ቅቤ እንቀባለን፡፡ ፀጉራችንን እናበጥራለን፡፡ ሴቶች ኡርጎ ይቀቡናል፡፡ ... ሴቶቻችን ሲለብሱ ልዩ ሽታ ነበራቸው፤ ብብታቸው ስር ይቀባሉ፡፡ ከብቱም የለበሱትን ቆዳ ይልሳል፤ ብብታቸውን ይልሳል፡፡ በዚህም ወተት ይሰጣል፡፡ ይህንን ሁሉ ያጣን ጊዜ ቆሌአችን ተገፈፈ ድርቅ ደረሰብን፡፡ ገሼጢቃቆ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 5፣2000 ዓ.ም)

ከዚህ መረዳት የሚቻለው የቅቤ እንደልብ አለመገኘት ቦንኮው ንፅህናውን የጠበቀ ሆኖ ለመልበስ አስቸጋሪ መሆኑን ነው፡፡ "እውነትም ነው አንድ ቦንኮ 150 ብር ቅቤ ይፈልጋል፤ አሁን የከብቶች ድህነት አለ፡፡ ከብቶች ሣር በማጣት መሬቱም ታርሶ ስላለቀባቸው አሁን ትንሽ ዝቅ አለ፡፡"ደሜ ቱፋ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 4፣2000 ዓ.ም)

የከብቶች እንደልብ ሣር ማግኘት አለመቻል ቅቤ እንደልብ ለማግኘት አያስችልም፡፡ ከዚያም አልፎ ከብቶች እንዳይራቡና ብዙ ዘር እንዳይሰጡም ምክንያት ይሆናል፡፡ ከቆዳ የሚሰሩት ባህላዊ አልባሳት በስም ብቻ የሚገኙ አሉ፡፡ ከእነዚህ ሌላ በቁጥር አነስተኛ የሆኑት ብቻ በኮኮሳ ይገኛሉ፡፡ በፊት ከሶስት እስከ አራት አይነት የነበሩት አልባሳት አሁን አንድ ወይም ሁለት አይነት ብቻ ናቸው፡፡ በኮኮሳ የሚገኙት አልባሳት የካባ ዘር የሆኑትና ከላይ የሚለበሱት ናቸው፡፡ ቁጣ፣ ሀርሰማ የሚባሉት ጭራሽ የሉም፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት አልባሳት የጠፉበት ሌላው ምክንያት ሰው ሰራሽ ነው፡፡

ህዝቡ የለመደውን የአለባበስ ባህል ባንድ ጊዜ እንዲተዉ ተደርጎ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ገበያ ውስጥ ጥቁር የከብት ቆዳ የተንጠለጠለባት እንጨት ወደ ላይ አድርገው እንደዚህ አይነት ልብስ ለብሶ የመጣ እንደሚቀጣ ይነገር ነበር፡፡ ሼክ ከድር (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 28፣2000 ዓ.ም) ህዝቡ ያንን በቀላሉ መተው ስላልቻለም እስከመታሰር የደረሱ፣ በላያቸው ላይም የለበሱት በመቀስ የተቀደደ እንደነበሩ የመረጃ አቀባዮቹ ይናገራሉ፡፡

በአልባሳቱ ብቻ ሳይሆን በፀጉራቸው ላይም የሚያደርጓቸውን ጌጦች እንዲተዉ የተለያዩ እርምጃዎች ተወስደውባቸው ነበር፡፡ "ባለፉት መንግስታት ፀጉራችንን ቆርጠው ልብሳችንን እንድናወልቅ አድርገው እራቁታችንን ቀርተን ነበር፡፡ ጌጣጌጡንም ሆነ አልባሳቱን ከላያችን ላይ አውልቀን ሸጠን ነበር፡፡" ደሜ ቱፋ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 4፣2000 ዓ.ም)

በጊዜው አንዳንዶቹ ለመሸጥ ሲችሉ ያልቻሉት ደግሞ በላያቸው ላይ ተቀዳደባቸዋል፡፡ በፀጉራቸው ላይ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ጌጦችም እንዲቀሩ በማለት ፀጉራቸውን እስከመላጨት የደረሰ በደል እንደነበረባቸው መረጃው ያመለክታል፡፡

"ለውጥ አለ፡፡ እንደስልጣኔ ደረጃ ኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ተስተጋብሮ ትምህርት የመሳሰሉት ሲለወጡ ባህሉም ይለወጣል፡፡ ለውጥ ይኖራል፡፡ "... ለውጡ አይምጣ አይባልም ለውጡ ለውድቀት የሚሆን ለውጥ መሆን የለበትም፡፡" (አብዱልቃድር መጋቢት 29፣2000 ዓ.ም)

በሀሳሳ ባህሉ እንዳይጠፋ ለማድረግ እየተደረገ ያለው ጥረት ከፍተኛ እና አስደሳች ነው። ነገር ግን አዲስ ነገር ለመፍጠር ሲባል ትውልዱ የቀደመ ማንነቱን ሊዘነጋ የሚያደርግ መሆን የለበትም። አብዱልቃድር ገልሞ (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 29፣2000 ዓ.ም)

የህዝቡ ፋሽን ለመከተል ያለው ፍላጎት ሌላው አልባሳቱ እንደልብ አለመገኘት ምክንያት ነው። የህዝቡ ፍላጎት ከቀደመው ይልቅ ፋሽን መከተልን መምረጡ ማህበረሰቡ ባህሉን በነፃነት ለትውልዱ እንዳያስተላልፍ ምክንያት ሆኗል። ብርሀኑ በሪሶ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 4፣2000 ዓ.ም)

ጌጣጌጦቹም ሆኑ አልባሳቱ አሁን እንደልብ አይሰሩም። በአሁን ጊዜ በአካባቢው የተሟላ ሃርሰማና ቁጣን ሳይጨምር ማግኘት የሚቻለው በጥቂት ሰዎች እጅ ነው። ይህም የሆነው አልባሳቱን በኃይለስላሴ ዘመን ደብቀው ስላስቀመጡ መሆኑን ተጠቃሚዎች ይናገራሉ።

4.6 የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ባህላዊነትን ለመጠበቅ ምን መደረግ አለበት?

በኮኮሳና እና በገደብ ሀሳሳ ወረዳዎች የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ጥናት የማህበረሰቡ ባህል ምን አይነት ይዞታ ላይ እንዳለ ለመመርመር ተሞክሯል። በሁለቱ ወረዳዎች የታየው የተለያየ ገፅታ አለው። በኮኮሳ ባህላዊነቱ ጠብቆ ባለበት ሁኔታ የታየበት ነው። የሀሳሳው ባህልን በዘመናዊ መንገድ ማስተዋወቅና ማሳደግ በሚል አላማ እየተሰራበት ያለ ነው። እነዚህን ሁለት ወረዳዎች መሠረት በማድረግ በሁለቱም ወረዳዎች ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ባህልን ከመጠበቅ ረገድ መደረግ አለበት የሚሏቸው ሃሳቦች አሉ።

መረጃ አቀባዮቹ በተለያየ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች እየተመናመነና እየጠፋ ያለው የአለባበስና የአጊያጌያጥ ባህል የቀድሞ ይዞታውን መያዙ ችላ መባል የሌለበት መሆኑን ይናገራሉ። ባህላዊው ልብስ ፣ለልብስነቱ ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ ጉዳዮች ጠቀሜታ እንደነበረው ሃጂ ከድሮ ይናገራሉ። ድሮ ሴቶች በቅቤ የረሰረሰውን የቆዳ ልብስ ሲለብሱ ብርድ የሚባል የበሽታ አይነት አልነበረም። ብርድ ወደ ሰውነታቸው ስለማይገባ ጤንነት ነበራቸው። አሁን ግን ጣቃ የሚባል ዘመናዊ ጨርቅ ወደማህበረሱ በመግባቱ በሽታም አብሮ እንደገባ ነው የሚገልፁት።ሀጂ ሞሀመድ ጃርሶ (ቃለመጠይቅ፣መጋቢት 30፣2000 ዓ.ም)

የአንድን ህዝብ ባህል ለመጠበቅ በየዘመኑ የሚመጣ ትውልድ የራሱን ድርሻ መወጣት አለበት። ያንን ማድረግ የሚችለው የቀደመውን ወይም የጥንቱን ብቻ በመጠበቅ ሳይሆን በዘመኑ በሚያገኘው ነገር በመጠቀም መሆን አለበት። እህተ ጊዮርጊስ ቢራቱ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 28፣2000 ዓ.ም) በሀሳሳ ባህላዊውን የአርሲ አልባሳትና ጌጣጌጥ

በዘመናዊ መንገድ በማቅረብ እየተደረገ ያለ ጥረት አለ፡፡ ከነዚህም መሃል የቆዳውን ልብስ በጨርቅ በመለወጥ የተለያዩ ጌጦችን አድርጎ መሸጥ አንዱ ነው፡፡ ሌላውና አብዛኛዎቹ የሀሳሳም ሆነ የኮካሣ መረጃ አቀባዮች ያላቸው ቅሬታ የቁሶች ባህላዊ አገልግሎታቸውን ትተው ለሌላ አገልግሎት/ለጌጥ መዋላቸው ነው፡፡

> … እቤት ለማሳመሪያ ብቻ ተብሎ የሚሰራ ከሆነ ይሄ የራሱ የሆነ ጉዳት አለው፡፡ ማህበረሰቡ በአሁኑ ወቅት ቤቱን በምን ያሳምራል፤ ቤቱን ማሳመር የለበትም ማለት ሳይሆን እኛ የምንለው የማይከፈት ቆሪ በባህላችን ውስጥ የለም ነው፡፡ ቆሪያችን የበለጠ አምሮ ባልና ሚስት ከአንድ ቦታሲበሉ እንግዳም ሲመጣ ተከፍቶ ገንፎ ሲወጣበት፤ ሚጪራ ከውስጡ ወጥቶ ሲበሉ ነው፡፡የአሁኑ ደረቁ ይሸፈናል ከሆነ ጥሩ ነገር አይመስለኝም፡፡አብዱልቃድር ገልሞ (ቃለመጠይቅ፣ መጋቢት 29፣2000 ዓ.ም)

በሀሳሳ በተለይ በተለያዩ ጌጦች አምረው ለገበያ የሚቀርቡት ቁሶች ባብዛኛው ለምግብ፣ ለወተት ማቅረቢያ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ከቀረበው መረጃም መረዳት የሚቻለው እነዚህን ማስጌጡና ማሳመሩ እንዳለ ሆኖ ከባህላዊ ይዞታቸው ባይቀየሩ መልካም መሆኑን ነው፡፡

መረጃ አቀባዮቹ ባህሉ ቀጣይነት እንዲኖረው እያንዳንዱ የሚመለከተው አካል በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት ይናገራሉ፡፡ በተለይ በኮካሳ የሚታዩትና ከመጥፋት የተረፉት ጌጦችና አልባሳት ልዩ ትኩረት ያሻቸዋል፡፡ ባህልን እንወዳለን በአፍ ብቻ አይበቃም የሚሉም አሉ፡፡ ከግለሰብ እስከመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ባህሉን በማሳደግ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው፡፡ ያለውን ለመጠበቅም ከወረዳ ጀምሮ ዞን እያለ በኦሮሚያ ደረጃ መዚየም ቢከፈት መልካም ነው፡፡ቦንሰሞ ሚኤሶ (ቃለመጠይቅ፣ ሚያዚያ 6፣2000 ዓ.ም)

ባህልን ለመጠበቅ አስፈላጊው ትብብር ቢደረግልን እኛ ዝግጁ ነን የሚሉት ደግሞ የኮካሳ ነዋሪ የሆኑት መረጃ አቀባይ ናቸው፡፡ «መንግስት ረድቶን የድሮ ባህላችን ቢመለስ እኛም ቆርጠን እንነሳለን፡፡ የተቸገርነው ይህንን ባህል አጥተን ነው፡፡ ድሮ ሴቶቻችን ሲንቄ ይዘው ይወጣሉ፡፡ ወደ ወንዝ እንኳን ሲወርዱ የከብቶች ከሎ አስረው ይወጡ ነበር፡፡» ገሼ ጢቃቆ (ቃለመጠይቅ፣ሚያዚያ 5፣2000 ዐ.ም)

የኮኮሳ ባህልና ቱሪዝም ሃላፊም እንዲህ ይላሉ፡፡ «ከግለሰብ እስከ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጎናችን ቆመው ካበረታቱንና ከረዱን ባህሉን ጠብቀን ለመጭው ትውልድ ማውረስ እንችላለን፡፡»ብርሀኑ በሪሶ (ቃለመጠይቅ ሚያዚያ 4፣2000 ዓ.ም) ባህሉን ለመጠበቅ በባህል ቢሮዎች ላይ ብቻ የሚተው አይደለም፡፡ በመሆኑም የሚመለከተው አካል እነዚህ በመጥፋት ላይ ያሉ የባህል ቅርሶች ከመጥፋታቸው በፊት መታደግ አለበት፡፡

ባጠቃላይ መረጃ አቀባዮቹ የሰጧቸው ሀሳቦች ባህልን መጠበቅ ለአንድ አካል ወይም ግለሰብና ድርጅት የሚተው አይደለም፤ ስለዚህ ሁሉም የበኩሉን ማድረግ አለበት የሚሉ ናቸው፡፡

5. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

በዚህ ክፍል እስካሁን በቀረቡ ምዕራፎች የተነሱ ጉዳዮችና ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳት ለባህሉ እድገት የሚጠቅሙና ቢሆኑ ቢደረጉ የሚሉ ሀሳቦች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

5.1 ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በቀደሙት ምዕራፎች የቀረቡትን ገለጻዎችና ትንተናዎች መሰረት በማድረግ የጥናቱ ማጠቃለያና ወደፊት ምን መደረግ እንዳለበት የሚጠቁሙ ሀሳቦች ይቀርባሉ፡፡

በዓለም ላይ የሚኖሩ የተለያዩ ህዝቦች የየራሳቸው ባህልና ባህላዊ መገለጫ አላቸው፡፡ እንደሚኖሩበት አካባቢ፣ የአየር ንብረትና የእርስ በርስ ተራክቦ የተለያዩ መለያዎች ይኖሯቸዋል፡፡ ባህል አንድን ማህበረሰብ በጋራነት ሊያቆራኝ የሚችል የማንነት መለያ ነው፡፡ ይህም ሰፊ ፅንሰ ሃሳብን የያዘ ጉዳይ በየማህበረሰቡ በተለያየ መንገድ ይገለፃል፡፡ ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ አንዱ የሆነው ቁሳዊ ባህል ተጨባጭ የሆነ የማህበረሰብ መገለጫ ጥበብ መሆኑን በዚህ ጥናት በተለያዩ ክፍሎች ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

በተለያዩ ዘመናት በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ የሚያልፉ የዓለም ህዝቦች አንዱን ከሌላው መለያ የራስን ወገን ማወቂያ ቁሶች አሏቸው፡፡ ከነዚህ የቁሳዊ ባህል ንዑስ አካላት ውስጥ አልባሳትና ጌጣጌጦች ይጠቀሳሉ፡፡

አልባሳት ከጌጣጌጦች ጋርም ሆነ ለብቻቸው ለተለያዩ ተግባራት ይውላሉ፡፡ ከብርድ ለመከላከል፣ ለጌጥነት እና ከሃይማኖት እንዲሁም ከማህበራዊ ደረጃ ጋር ተያይዘው ለልዩ ልዩ ተግባራት ይውላሉ፡፡ እነዚህም እንደየባህሉን እንደየማህበረሰቡ ሁኔታ የሚለያዩበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ጌጣጌጦችም ለመዋቢያት የሚውሉ ማህበረሰቡ የሚያበጃቸው የጥበቡ ውጤት መሆናቸውን ቀደም ባሉት ክፍሎች ተገልጿል፡፡

ይህም ጥናት በአርሲ ሁለት ወረዳዎች ማለትም በኮኮሳና ገደብ ሀሳሳ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ትኩረቱን ሲያደርግ የአልባሳቱን ጠቀሜታ፣ ታሪክና ይዘታ ማጥናት መሆኑ በዓላማው ተጠቅሷል፡፡ ይህንንም መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ማጠቃለያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- በሁለቱ ወረዳዎች በተደረገው የአልባሳትና ጌጣጌጦች ጥናት በኮኮሣ የሚገኙት የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ጥንታዊው የአርሲ ኦሮሞ ሴቶች የአለባበስ ስርዓት የሚንፀባረቅባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- በኮኮሳ ከሴቶች አልባሳት ውስጥ ጨርሰው የጠፉና አሁን እንኳን መልሰው ለመስራት ያልቻሉ የልብስ አይነቶች አሉ። እነዚህም ከስር በቀሚስ መልክ የሚዘጋጁ የወጣትና የእናቶች የቆዳ ልብሶች ናቸው።
- በኮኮሳ ያለውን ባህል ለመጠበቅ ሲባል በአስተዳደሩም ሆነ በባህልና ቱሪዝም ቢሮ በየቀበሌዎቹ ወርደው በማስተማር ሴቶቹ ልብሳቸውንና ጌጣቸውን እንዳይሸጡና፣ ጠብቀው እንዲጠቀሙ፣ ለትውልድም እንዲያስተላለፉ ትምህርት በመስጠት ላይ መሆኑ በመስክ ስራ ወቅት ለማወቅ ተችሏል።
- በኮኮሳ የባህል አልባሳቱንና ጌጋጌጡን ዳግም እንዳይጠፉ በማሰብና በሌሎች ባህላዊ ጉዳዮች በወረዳ ደረጃ አንድ ሙዚየም በግንቦት 1፣ 2000 ተከፍቶ ስራ ጀምሯል፤ ይህም ባህሉን በመጠበቅ ረገድ ጥሩ ጅምር ነው።
- አልባሳቱ በዕድሜና በትዳር መያዝ አለመያዝ የተለያየ ስም ወይም አንድ ስምና የተለያየ ይዘት ያላቸው ናቸው።
- አልባሳቱ የሴቶቹን ከየት አካባቢና ከየትኛው ማህበረሰብ የወጡ እንደሆኑ ያመለክት እንደነበር ከሃገር ሽማግሌዎች የተገኘ መረጃ ቢኖርም በምልከታ ወቅት የታየው ከዚህ የተለየ ነበር። ጥቂት ሙሉውን ልብስና ጌጥ ያደረጉ ቢኖሩም በአብዛኛው የፋብሪካ ውጤት የሆኑ ልብሶችን ለብሰው ይታዩ ነበር። ይህም አስቸኳይ የባህል መጠናከር እንደሚያስፈልገው የሚያመለክት ነው። በሌላ በኩል ጌጣጌጦቹን ያገቡ ብቻ ያደርጓቸዋል የሚባሉትን ልጃገረዶችም አድርገው ለመመልከት ተችሏል።
- አሁን ባሉበት ደረጃም አንዲት ሴት አንድ እንኳን ቢሆን ጌጥ ከአንገቷ ማጣት የለባትም የሚለውን መረጃ አቀባዮቼ የሰጡኝን መረጃ በመስክ ቆይታዬ ለማየትና ለማረጋገጥ ችያለሁ። በገበያ ቀናት ሙስሊሞቹ በሌላው ልብስ ላይ ትንሽ ከሎ(kal'oo) ደርበው፣ ጉፍታ (Guftaa) ና ሰንዳባ (sandaaba) የተባለውን የግንባር ጌጥ አንገታቸው ላይም አንድም ቢሆን ጌጥ አድርገው ይታያሉ። ሌሎቹም ቢሆኑ ፀጉራቸውን ወደታች ተሰርተው ጫፉን በመተው የአንገት ጌጥ እንዲሁም ከሎዋን ደርበው ገበያ ይወጣሉ።
- በዘመናዊ መንገድ አልባሳቱንና ጌጣጌጦቹን በመስራት ገበያ ላይ የሚያውሉ ሰዎች ባህሉ የስም ቅርስን ተቶ እንዳይጠፋ እያደረጉ ያሉት ጥረት የሚበረታታ ነው። በሌላ በኩል አንዳንድ ቁሶች ላይ የአገልግሎት ለውጥ ከባህሉ ውጭ

በማድረግ ሲያቀርቡ ለማየት ተችሏል። ከነዚህም መሃከል ቆሪ የተባለውና ለምግብ ማቅረቢያ የሚውለው ቁስ ለጌጥነት አገልግሎት ብቻ ይውላል።

- ጠፍተዋል የተባሉት አልባሳት ባህላዊ ስማቸውን ይዘው በመስራት ላይ ናቸው። እነዚህ አልባሳት ብዙ ወጪ የሚጠይቁና የአካባቢው ማህበረሰብ ደፍሮ የማይገዛቸው ናቸው።
- የፋብሪካ ውጤት የሆኑ ልብሶችን መጠቀም መጀመሩ በገጠሩም ሆነ በከተማው እየተስፋፋ መምጣቱን ለመታዘብ ተችሏል።
- በኮኮሳ በቀድሞ የነበሩትን ባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ በአብዛኛው አሁን ለማግኘት የተቻለው ሴቶቹ ከእናት ወይም ከአያት በውርስ አግኝተው ማስቀመጥ በመቻላቸው ነው።
- በሀሳሳ ያለው ደግሞ የመስራት ጥበቡ ነው። በባህላዊ መንገድ ከእናትና አባታቸው የለመዱትን ከዘመኑ ጋር በማጣጣም የፋብሪካ ውጤት በሆነው ልብስ ላይ የማጌጥና ቅርፅ የመስጠት ስራ የሚሰሩት ባለሙያዎች ለልጆቻቸው እያስተማሩ ይገኛሉ። ከዚህም ጥበቡ ከእናት ወደልጅና የእርስ በርስ ተራክቦ ከአንዱ ወደ አንዱ የሚተላለፍ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

5.2 የመፍትሄ ሀሳቦች

በሁለቱ ወረዳዎች የሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ሁኔታ ላይ የሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች ቀርበዋል።

- በኮኮሳም ሆነ በሀሳሳ በባህልና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም በአስተዳደር መስሪያ ቤቶች ባህሉን ለመጠበቅ እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።
- በኮኮሳ ከህዝቡ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር የልብሱና ጌጡ ተጠቃሚዎች/ባለቤቶች ቁጥር ዝቅተኛ ነው። የአልባሳቱና ጌጣጌጦቹ ባለቤቶች ትምህርት ቤት የገቡ ተማሪዎች ብዙም ፍላጎት እንደሌላቸው ይናገራሉ። ይህም በመሆኑ በትምህርት ቤት ተማሪዎች የአልባሳቱንና ጌጣጌጦቹን ባህላዊነት ተረድተው እንዲጠብቁ ቢደረግ ወይም አልባሳቱና ጌጣጌጡ ተሰብስበውና ተመሳሳያቸው ተሰርቶ በሙዚየም የሚቀመጡበት ሁኔታ ቢመቻች ለታሪክ ማስታወሻነት ጉህል ድርሻ ይኖረዋል።
- በሀሳሳ በግልም ሆነ በማህበር የሚሰሩ ሰሪዎች እንዲሰሩ ከማድረግ ውጭ ምንም የተደረገላቸው ተጨማሪ ነገር የለም። በመሆኑም በራሳቸው ወጭ ሁሉንም ሸፍነው

ስለሚሰሩ ጌጣጌጦቹም ሆኑ አልባሳቱ ከፍተኛ ዋጋን የሚጠይቁ ሆነዋል። በአስተዳደር በኩል መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እነዚህ የግሎቹም ሆኑ የማህበሩ አባላት ድጋፍ የሚያገኙበት አጋጣሚ ቢመቻች በማህበረሰቡ ዘንድ አቅምን ያገናዘበ ፍላጎት እንዲፈጠር ያደርጋል።

- በግልም ሆነ በማህበር የሚሰሩ ባለሙያዎች በአብዛኛው በተለይ ቀደምቶቹ የዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ አይደሉም፤ በልምድ ያዳበሩት እውቀት አሁን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና በሰፊው በተስፋፋበት ወቅት ያንን ትምህርት የሚያገኙበት ሁኔታ ቢመቻች ካሁን የበለጠ ሊሰራ ይችላል።
- እንደአገር ሽማግሌዎቹና ተጠቃሚዎቹ ገለፃ በአሁኑ ወቅት ተማሪዎች ስለባህላዊው ጉዳይ ብዙም ትኩረት አይሰጡትም። በመሆኑም በትምህርት ቤቶች የባህል ኮሚቴ ተቋቁሞ (የበለጠ ተጠናክሮ) ተማሪዎቹ ስባህሉ ጥሩ አመለካከትና ፍላጎት እንዲኖራቸው ሁኔታዎች ቢመቻቹ መልካም ነው።
- ከፋብሪካ በወጡ አልባሳት የሚሰሩ አልባሳት እንዲሁም ጌጣጌጦች ቅርጻቸውና ስማቸው ብቻ ሳይሆን በአገልግሎትም ባህላዊ የሚሆኑበት መንገድ ቢመቻች ባህሉን ከመዘከር አኳያ ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል። ይህንንም የባህል ቢሮዎች በየጊዜው ቢከታተሉ መልካም ነው።
- አልባሳቱና ጌጣጌጦቹ በሁለቱ ወረዳዎች ያለውን ሁኔታ የህዝቡን በዘመናት ውስጥ ያጣውን ለመተካት ያደረገውን ጥረትና ችሎታውን የሚያሳዩ በመሆናቸው አልባሳቱ ከጊዜ ብዛት ጠፍተው ባዶ እንዳይሆን በጋራ ሊይዝ የሚችል ሙዚየም በዞኑም ይሁን በወረዳ ደረጃ ቢቋቋም የውጭ ሃገርም ሆነ የሃገር ውስጥ ቱሪስቶችን ለመሳብ ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፤ ህዝቡንም በማስተዋወቅ ረገድ ከፍተኛ ቦታ አለው።

ዋቢ ምንጮች

Abas, Haji."The History of Arsi. (1880-1933)".Addis Ababa University: BA Thesis Submitted to the Department of History,1982.

"Aadaa Ummata Godina Arsii Lixaa." ከዞኑ አስተዳደር ቢሮ የተገኘ የጽሁፍ መረጃ፣2000.[1]

Aanaa Gadab Hasaasaa Hamisoomsinuu.የታተመበት ቦታ የለውም፣አሳታሚ የለውም፣2000.

Daniel Deressa. Continuity and Change in The Status of Women: The case of Arsi Oromoo Living Adjacent to Upper Wabe Valley(Dodolaa) School of Graduate Studies ,2002.

Dundes, Alan. The Study of Folklore. University of California at Berkeley Prentic.Hall, INC, 1965.

Dorson, Richard M.Folklore and folk Life: An Introduction. London, University press of Kentucky,1972.

The Encyclopedia Americana. USA: Grolier International,INC.V.7,1983.

The New Encyclopedia Britannica. Chicago: Encyclopedia Britanica INC.V.17,1993.

Entwistel, Joanne and Elizabeth Wilson. Body Dressing USA: New York, 2001.

Evans,Joan. A History of Jewellery: (1100-1870). USA: Boston Book, and Publisher,1970.

Ezra Ayele. "Object Language used by Arsi Oromoo People". Addis Ababa: University BA Thesis Submitted to the Department of Linguistics. 1982.

Fekade Azeze. Teaching Material Selected and Compiled; Reader for ELti 621".Department of Ethiopian Languages and Literature MA in Ethiopian Literature and Folklore,2003."

__________ The State of Oral Literature Research in Ethiopian: Retrospect and Prospects A paper presented to the plenary session of XIV International Conference Ethiopian Studies, November 6-11, Addis Ababa, Ethiopia, published in JES, 2001.

Georges, Roberts .A &Michael Own Jones. Folklorstics: An Introduction. USA: Indiana University,1995.

Glassie,Henry. Material Culture. Chicago and London:The University of Chicago press, 1999.

Hirut Terefe. "A Study of Female Genital Mutilation and Reproductive Health: case of Arsi Oromo Ethiopia."Submitted for Doctoral grade in Ethnology(Social Anthropology) to the Faculty of Social Science University of Göttingen,2001.

---

[1] የኦሮምኛና የአማርኛ መረጃዎች ዐመተ ምህረታቸው በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው።

http://links.Jstor org."Mind in Matter:an Introduction to Material Culture Theory and method."

http://Wekpedia.org.wiki/color "Symbolism and Psychology."

Lurie, Alison. The Language of Clothes.New York:Random House Inc,1981.

Mathisen, Stein R. "Folklore and Cultural Identity." Fekade Azeze.2003."Teaching Material Selected and Compiled;Reader for ELti 621".Department of Ethiopian Languages and Literature MA in Ethiopian Literature and Folklore.

Roberts,Warren."Field Work:Recording Material Culture."In Dorson.(ed). Folklore And Folk Life. An Introduction,The University of Chicago Press :Chicago and London,1972.

"Socio-economic Profile of West Arsi Zone."ከዞኑ አስተዳደር ቢሮ የተገኘ የጽሁፍ መረጃ፣ 2000.

Wilcox,R.Turner.A Dictionary of Costume. USA: New York, 1969.

ሀገሬ። የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ፕሮግራም። አዲስ አበባ፣ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል፣2000

ሄለን አላምረው።1999።" ባህላዊ ሽመናና ቆዳ ሥራ በደንበጫና አካባቢ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ።

ብርሀኑ ለሜሶና ታቦር ያሚ።የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ።ማተሚያ ቤት የለውም፣1993።

አያል አድማሱ። "የጎጃም አልባሳት ስያሜ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ፣ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣1992።

ከተማ ጅማ።የአርሲ ጋልኛ ግጥሞች። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ፣ ኤዱኬሽን ፋኩሊቲ፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣1963።

ዋልተንጉስ መኮንን። "የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ለኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣2000።

ውብሸት አሰፋ።"የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ በአማራው ባህል"።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣1978 ።

የኔዓለም አረዶ። "የጥዮ አካባቢ ሴቶች የስራ ላይ ግጥሞች ትንተና"።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣1997።

ያለው እንዳወቀ። የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። ባህርዳር፣ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣1998።

ፊቃደ አዘዘ። የስነቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ቤት፣1991።

አባሪ1

የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

ተ.ቁ	ስም	ዕድሜ	ሃይማኖት	መኖሪያ	የቤተሰብ ሁኔታ	መተዳደሪያ/የስራ አይነት	መረጃው የተሰበሰበበት ቀን
1.	አቶ ታምራት ተካልኝ	38	ክርስቲያን	ሻሸመኔ	ያገባ	የምዕራብ አርሲ ዞን እቅድና ፕላን ክፍልሀላፊ	መጋቢት 25፤2000
2	ቦንሰሞ ሚኤሶ	51	ሙስሊም	ሻሸመኔ	ያገባ	የምዕራብ አርሲ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የባህል ኤክስፐርት	ሚያዚያ 6፤2000
3	አቶ አብዱልቃድር ገልሞ	43	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የሀሳሳ ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊ	መጋቢት 28፤2000
4	ብርሃኑ በሪሶ	45	ክርስቲያን	ኮኮሳ	ያገባ	የኮኮሳ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊ	ሚያዚያ 4፤2000
5	ታምራት ገመዳ	44	ክርስቲያን	ኮኮሳ	ያገባ	በኮኮሳትምህር ት ቢሮ የ፩ኛ ፪ደረጃ ሳይክል ሱፐር ቫይዘር	ሚያዚያ 6፤2000
6	ጀሚላ ከድሮ	27	ሙስሊም	ኮኮሳ	ያገባች	በኮኮሳ የሴቶች ጉዳይ ምክትል ሀላፊ	ሚያዚያ 4፤2000
7	ደሜ ቱፋ	30	ክርስቲያን	ኮኮሳ	ያገባች	በኮኮሳ የአቅም ግንባታ ተላላኪ	ሚያዚያ 4፤2000
8	እህተጊዮርጊስ ቢራቱ	33	ክርስቲያን	ሀሳሳ	ያገባ	የሀሳሳ ወረዳ ሴቶች ጉዳይ ምክትል ሀላፊ	ሚያዚ 28፤2000
9	ሀጂ ሞሀመድ ጃርሶ	72	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የሀገር ሽማግሌ	መጋቢት 29፤2000
10	ሼክ ከድር ሀያቶ	67	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የባህል ሀኪም	ሚያዚያ 29፤2000
11	አመሹ ሀጣቱ	75	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የቤት እመቤት	መጋቢት 30፤2000
12	አያኔ ገነሞ	72	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የቤት እመቤት	መጋቢት30፤2000
13	አያንቱ ዱቤ	58	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የአልባሳትና የጌጣጌጥ ስሪ	ሚያዚያ1፤እና ሚያዚያ29፤2000
14	አንዮ በቲሳ	45	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የአልባሳትና የጌጣጌጥ ስሪ	ሚያዚያ 2፤ እና28፤2000
15	ቂራ ከድር	20	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባች	የአልባሳትና ጌጣጌጥ ስሪ	ሚያዚያ 2፤2000
16	ኢሳ ከድር	27	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የአልባሳትና ጌጣጌጥ ስሪ	ሚያዚያ 2፤2000
17	መካ ያመታ	27	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የአልባሳትና ጌጣጌጥ ስሪ	መጋቢት 30፤2000
18	ደሚቱ ሮቤ	37	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባች	የአልባሳትና	ሚያዚያ

						የጌጣጌጥ ስራ(ጀማሪ)	22፣2000
19	ሞሚና ደማ	22	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያላገባች	የአልባሳትና የጌጣጌጥ ስራ	ሚያዚያ 22፣2000
20	ሰፊያ ሁሴን	35	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባች	የአልባሳትና ጌጣጌጥ ስራ	ሚያዚያ 23፣2000
21	ራሚያ አማን	37	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባች	የአልባሳትና ጌጣጌጥ ስራ	ሚያዚያ 23፣2000
22	ሀጂ አደም ሀጂ አምዳ	47	ሙስሊም	ሀሳሳ	ያገባ	የግል የልብስ የደረቅ እጥበት	መጋቢት 30፣2000
23	አብደላ ሉገማ	31	ሙስሊም	ዶዶላ	ያገባ	በባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነጻ አገልግሎት	መጋቢት 30፣2000
24	ነጌሶ ዲዶ	32	ሙስሊም	ኮኮሳ	ያገባ	ግብርና	ግንቦት 2፣2000
25	አባ ጀቦ ጨውቻ	78	ክርስቲያን	ኮኮሳ	ያገባ	ግብርና	ግንቦት 2፣2000
26	ፋጢማ ጃርሶ	40	ሙስሊም	ኮኮሳ	ያገባች	ግብርና	ግንቦት 2፣2000
27	ሄለሜ ነጋሶ	40	ክርስቲያን	ኮኮሳ/ቦሮ	ያገባች	ግብርና	ግንቦት 2፣2000
28	ሀልከሜ ሀጃፊሮ	35	ክርስቲያን	ኮኮሳ/ሀቦቦ	ያገባች	ግብርና	ግንቦት 2፣2000
29	ፉሬ ቱራ	40	ክርስቲያን	ጃፊረ/ኮኮሳ	ያገባች	ግብርና	ግንቦት 2፣2000
30	ገሼ ጢቃቆ	60	ክርስቲያን	67	ያገባ	ግብርና	ሚያዚያ 5፣2000
31	ኢሚሹ ኬቄ	67	ክርስቲያን	ኮኮሳ	ያገባ	ግብርና	ሚያዚያ 5፣2000
32	ከድሮ ገነሞ	58	ሙስሊም	ኮኮሳ	ያገባ	ግብርና	ሚያዚያ 5፣2000

አባሪ 2
የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች

በአካባቢው ለታወቁ ሰዎች እና ለአልባሳትና ጌጣጌጦች ሰሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

- ግላዊ መረጃ
  1. ሙሉ ስም________________________
  2. ዕድሜ__________________________
  3. ፆታ____________________________
  4. የቤተሰብ ሁኔታ____________________
  5. ሃይማኖት________________________
  6. የትምህርት ደረጃ___________________
  7. መተዳደሪያ________________________
  8. የመኖሪያ ስፍራ (ገጠር፣ከተማ)

- አካባቢያዊና ባህላዊ መረጃ
  1. አካባቢው ይህን ስም እንዴት አገኘ? ትርጉሙስ ምንድነው?
  2. በዚህ አካባቢ ታዋቂ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች ምን ምንድናቸው?
  3. በአካባቢው የተለመደው የሴቶች አለባበስ ምንድነው?
  4. በእድሜዎ አልባሳትና ጌጣጌጥን በተመለከተ የተለወጠ ነገር አለ ?ካለ ምክንያቱስ ምንድነው?
  5. ሴቶች ከአልባሳቱ በተጨማሪ የሚያደርጓቸው ጌጣጌጦች አሉ?
  6. አልባሳቱ ከምን ከምን ይሰራሉ?
  7. ጌጣጌጡ ከምን ከምን ይሰራሉ?
  8. አልባሳቱንና ጌጣጌጦቹን ማን ይሰራቸዋል?
  9. የሚለበሱ ልብሶች በሃይማኖት፣ በዕድሜና በኑሮ ደረጃ የሚለዩበት ሁኔታ ካለ ቢገልጹልኝ?

10. እርሶም ሆኑ ቤተሰብዎ የባህላዊ አልባሳቱንና ጌጣጌጡን ይጠቀማሉ? መቼ?

11. በዘመናዊ መንገድ እየተሰሩ ስለሚሸጡ የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጥ ምን አስተያየት አሎት?

12. በአካባቢዎ የባህላዊ አልባሳትና ጌጣጌጥ የመለበሻ አጋጣሚ ምን ይመስላል?

    መቼ ይለበሳሉ?

13. የአልባሳቱና የጌጣጌጦቹ የስም አሰጣጥ ምንን መሰረት ያደረገ ነው?

14. የአርሲ ሴቶች አልባሳትና ጌጣጌጦች ባህላዊነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ለማድረግ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

15. ባህላዊ አልባሳቱንና ጌጣጌጡን የለበሱና ያደረጉ ሴቶችን በማየት ብቻ የኑሮ ደረጃቸውን መገመት የሚቻልበት አጋጣሚ ነበር? አሁንስ?

- ለአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

- ግላዊ መረጃ

1. ሙሉ ስም______________________________
2. ዕድሜ______________________________
3. ፆታ______________________________
4. የቤተሰብ ሁኔታ________________________
5. ሃይማኖት____________________________
6. የትምህርት ደረጃ________________________
7. መተዳደሪያ____________________________
8. የመኖሪያ ስፍራ(ገጠር፣ከተማ)________________

    - ከስራ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች

1. በአካባቢዎ በምን ስራ ይታወቃሉ?
2. ይህንን ስራ መቼ ጀመሩ?

3. ሙያውን ከማን ተማሩት?

4. በምን አይነት መንገድ ተማሩት (በፍላጎት፣በቤተሰብ አስገዳጅነት፣ሌሎችን በማየት)

5. የሚሰሩባቸውን ቁሶች ከየት ያገኟቸዋል?

6. አንዱን ቁስ ሰርቶ ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?

7. አንዱ ቁስ ምን ያህል ዋጋ ያወጣል?

8. አልባሳቱን የሚሰሩአቸው ለምን አላማ ነው (ለንግድ፣ለግል መጠቀሚያ)?

9. የ8ኛው መልስ ለንግድ ከሆነ ስራውን የሚሰሩት በምን አይነት መንገድ ነው?

10. አልባሳቱም ሆኑ ጌጣጌጡን የሚገዙት ምን አይነት ሰዎች ናቸው?

11. በምን አይነት መንገድ ለገበያ ያቀርቧቸዋል?

12. ይህ ስራ በህይወትዎ ላይ ያመጣው ለውጥ አለ? ካለ ቢገልጹልኝ?

አባሪ 3

ኮኮሳ ገበያ

አቶ ነጌሶ ዲዶ የኮኮሳ መረጃ አቀባይ

አቶ ደምሴ ዱቤ የኮኮሳ ወረዳ
አስተዳደር ምክትል አስተዳዳሪ

አቶ ከዲሮ ገነሞ
የኮኮሳ የአገር
ሽማግሌ

ኮኮሳ ገበያ ውስጥ

አቶ ኢምሹ ኬቁ የኮኮሳ የአገር ሽማግሌ

አልባሳትና ጌጣጌጥ የለበሱ የኮኮሳ
ሴቶች

ከዶዶላ ወደኮኮሳ ተጓገሮች

አቶ ብርሃኑ በሪሶ የኮኮሳ ባህልና ቱሪዝም ሀላፊ

ወ/ሮ ደሜ ቱፋ የኮኮሳ መረጃ አቀባይ

ወ/ሮ ጀሚላ ከዲሮ የኮኮሳ ሴቶች ጉዳይ ም/ሀላፊ

አቶ ገሼ ጢቃቆ የኮኮሳ የአገር ሽማግሌ

አባ ጀቦ ጩውቻ የኮኮሳ የአገር ሽማግሌ

አቶ መሃመድ ጃርሶ የሀሳሳ ሀገር ሽማግሌ

የሀሳሳ ተጓገሮች

ባህላዊ የምግብና የቅቤ መያዣ ቁሶች

ጉዞ ወደ አልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎች ቤት

ለገበያ የሚቀርቡ ቆሪና ጡንጦ

ወ/ሮ እህተጊዮርጊስ ቢራቱ የሀሳሳ ሴቶች ጉዳይ ም/ሀላፊ

ጉዞ ወደ አልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎች ቤት

የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪዎች በስራ ላይ

እቤት ውስጥ የሚሸጥ ቆሪ

ወ/ሮ መካ ያመታ የግል የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪ

አቶ አብዱልቃድር ገልሞ የሀሳሳ ባህልና ቱሪዝም ሀላፊ

ወ/ሮ አያንቱ ዱቤ
የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪ

ወ/ሮ አመሹ ሀጣቱ መረጃ አቀባይ

ወ/ሮ አንዮ በቲሳ የአልባሳትና ጌጣጌጥ ሰሪ(የግል)

አቶ አብደላ ሉጉማ

አቶ ቦንሰሞ ሚኤሶ ቁልፍ መረጃ
አቀባይ

አቶ ታምራት ተካልኝ የምዕራብ አርሲ ዞ
እቅድና ፕላን ክፍል ሀላፊ